# ጉዞው…



በአሜኬላ የታጠረው
በጥበብና በጽናት የታለፈው

# ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት
## ታህሳስ 2013 ዓ.ም

# ጉዞው...

## በአሜኬላ የታጠረው ፤ በጥበብና በጽናት የታለፈው

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከ2010 ለውጥ ዋዜማ ጀምሮ ያጋጠሙትን ሀገራዊ ፈተናዎች፤በመረጃና ደህንነት ተቋሙ እንዲሁም በመከላከያ ሠራዊቱ የነበረው የተዛባ አካሄድ ያስከተለውን መዘዝ፤ የህወሓት ጁንታ በሰሜን እዝ ላይ ስለፈጸመው ጥቃትና ስለተወሰደው የህግ ማስከበር ዘመቻ እንዲሁም በሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ ልዩ ስብሰባ ተገኝተው የሰጡት ማብራሪያ

በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት
የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ
ስልክ ፡- 011 558 45 37

# ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አንደበት

< <በመደለያ በኢትዮጵያ ህልውና የሚደራደር ኢትዮጵያዊ አትጠብቁ፤ ስህተት ነው። ሰላም ወዳድ መሆናችንን ለሰላም የምንተጋ መሆናችንን ተገንዝባችሁ የእኛን ነገር አውቃችሁ በትብብር መንፈስ እንስራ እንጂ የድህነት ድህነት ቢመጣ ክብሩን አሳልፎ የሚሰጥ ኢትዮጵያዊ የለም። እንግዲህ ይህንን ነገር እንዳትፈርዱብን የእኛ ጥፋት አይደለም። አባቶቻችን ናቸው በደም ውስጥ ያስተላለፉብን፤ አንችልም ! > >

< <ጦርነቱን በከፍተኛ ጀግንነት በብቃት አሸንፈናል። ነገር ግን ይሄ ነገር ወደ ትዕቢትና እብሪት ከወሰደን ጥፋት ነው። በእኔ እምነት ያሸነፈው እውነት ነው። ያሸነፈው የኢትዮጵያ እናቶች እንባና ጸሎት ነው > >

< <የትግራይን ህዝብ ሚና፤ የትግራይን ህዝብ ጀግንነትና ሀገር ወዳድነት የተከበረው ምክር ቤት በትክክል እንዲገነዘበው እፈልጋለሁ። ግጭቱ ገና ሲጀመር መከላከያን አትንኩት በማለቱ ባንዳ ተብሎ የተመታ አለ፤ ወደ ኤርትራ ከወጣው ጦር ጋር አብሬ እወጣለሁ፤ እናት ኢትዮጵያ ስትወጋ አብሬ አልቀመጥም ብሎ የወጣ የትግራይ ተወላጅ አለ> >




ክቡር ዶ/ር አብይ አህመድ
H.E Dr. ABIY AHMED

# ማውጫ


እንደ መነሻ ........ 7
የጽሁፉ አቀራረብ ........ 7
ተጠየቅ? ........ 8
**ዋዜማ ........ 10**
የዋዜማው ምጦች ........ 10
መፈንቅለ ሰው ........ 12
አሻንጉሊት የማስቀመጥ ሽኩቻ ........ 14
**ማግስት ........ 17**
አዲስ መንገድ ........ 17
ማግስቱን በጥበብ ........ 19
‹‹እስረኛው›› ጠቅላይ ሚኒስትር ........ 20
የ‹‹ሳንድዊች አጥሮች›› እነ ማንን አስደነገጠ? ........ 22
‹‹ወይ አንተ፤ ወይ እኛ›› የደህንነት ሹሞቹ ቀይ መስመር ........ 26
‹‹ከሀገር የሚበልጥ የለም›› የለውጥ አመራሩ ቀይ መስመር ........ 28
የቤተሰብ ማህበሩ ገመና ........ 30
በኢትዮጵያ ልክ ያልተገነባው ተቋም ........ 32
ከ113 ግጭቶች በስተጀርባ ........ 38
**አዲስ ቀን ........ 43**
የዛሬን ድል ትናንት የሠራው የመከላከያ ሪፎርም ........ 43
ምስጢራዊ ሪፎርም ........ 46
የሚስጢራዊ ሪፎርም በረከት ........ 48
የጎደለን ........ 52
ፖለቲካዊ ሪፎርም ለፖለቲካዊ ሽፍጥ ........ 54
የኢኮኖሚ ሪፎርሙ እና አንገት የያዘው የብር ኖት ለውጥ ........ 56
አፈናን ታሪክ ያደረገ የፍትህ ዘርፍ ሪፎርም ........ 58
ክፉ ቀንን የዋጀ የዲፕሎማሲ ሪፎርም ........ 60
**ነገረ ሰሜን እዝ ........ 63**
የመጨረሻው መጀመሪያ ........ 63
ክብር ለቁርጥ ቀን ልጆች ........ 68
እነ ድል ቁርሱ ........ 72
እናት ኢትዮጵያ ስትወጋ ከማየት ........ 78
**ይድረስ ........ 80**
ለቅን ወዳጆቻችን ........ 81
በተለይ ድብቅ አጀንዳ ላነገባችሁ ........ 82
ለኢትዮጵያውያን እናቶች እንባና ጸሎት ........ 84
**እንደ ማጠቃለያ ........ 90**

# እንደ መነሻ

መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የማይዘነጋ ቀን ነው። በሀገሪቱ ከሶስት አመታት በላይ ያዝ ለቀቅ እያደረገ ሲካሄድ የቆየው ተቃውሞ ወደማይቀለበስበት ደረጃ በመሸጋገሩ፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በገዛ ፈቃዳቸው ስልጣናቸውን መልቀቃቸውን ተከትሎ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ቃለመሃላ የፈጸሙበት ታሪካዊ ዕለት ነበርና።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በበዓለ ሲመታቸው ያስተላለፉት መልዕክት ያለፈው ዘመን ሰቆቃ እንዲያበቃ መጪው ጊዜ የይቅርታ፣ የሰላም፣ የአንድነትና የፍቅር እንዲሆን ተስፋ የሚለግስ ነበር። ከብዙዎች የአዕምሮ ማህደር የማይጠፉትን እናስታውስ ...

<<ኢትዮጵያ ማህፀነ ለምለም ናት። ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር መንፈስ ሰርክ የሚተጉ ልጆችን አፍርታለች። ልጆቿም ወደቀድሞ ክብሯ እንድትመለስ፣ የሕዝቧ ሰላምና ፍትህ እንዲጠበቅ፣ ብልፅግና ያለ አድልኦ ለመላው ዜጎች ይዳረስ ዘንድ አጥብቀው ይመኛሉ፤ ይደክማሉ ...

<<አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንዳሉት እኛ ስንኖር ሰዎች፣ ስናልፍ ሀገር እንሆናለን። የየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ክቡር ስጋና ደም በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ አፈር ሆኖ ታገኙታላችሁ። ኢትዮጵያውያን ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ እንሆናለን።

<<ኢትዮጵያ የሁላችን ሀገር ፤የሁላችን ቤት ናት። በአንድ ሀገር ውስጥ የሀሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ። የሀሳብ ልዩነት እርግማን አይደለም። ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ መደማመጥና በመርህ ላይ ተመስርተን መግባባት ስንችል የሀሳብ ልዩነት በረከት ይዞልን ይመጣል። በሀሳብ ፍጭት ውስጥ መፍትሄ ይገኛል። በመተባበር ውስጥ ኃይል አለ። ስንደመር እንጠነከራለን። አንድነት የማይፈታው ችግር አይኖርም፤ ሀገር ይገነባል። የኔ ሀሳብ ካላሸነፈ ሞቼ እገኛለሁ ማለት ግን እንኳን ሀገርን ሊያቆም ቤተሰብን ያፈርሳል። ያለችን አንድ ኢትዮጵያ ነች ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት በላይ ሀገራዊ አንድነት ይበልጣል። አንድነት ማለት ግን አንድ አይነትነት ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። አንድነታችን ልዩነቶቻችንን ያቀፈ ብዝሃነታችንን በህብረ ብሔራዊነት ያደመቀ መሆን አለበት ...>>

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ወርቃማ ሃሳብ ሰላም፣ብልጽግና፣ አንድነት፣ ፍትህና እኩልነት የሚረጋገጥባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ አሻግሮ የተመለከቱ ዜጎች በሙሉ በተስፋ ሀሴት አድርገዋል። ለለውጥም ተነሳስተዋል። ይሁንና ጥቂት የሚባሉ አገዛዙን ለራሳቸው ብቻ እንዲበጅ አድርገው ጠፍጥፈው የሰሩ የስግብግቡ ህወሓት ጁንታ አባላትና ግብረአበሮቻቸው ወደ ቀደመ መንበራቸው ለመመለስ በመሻት በሀሳብ ልዕልና ከመታገል ይልቅ የሃይል አማራጭን ወስደዋል።

ጁንታው ቡድን የመረጠውን መንገድ ለማሳካት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ <<የኔ ሀሳብ ካላሸነፈ ሞቼ እገኛለሁ ...>> በሚል መንፈስ ሀገራዊ ህልውናን የሚፈታተኑና ለውጭ ጥቃት የሚዳርጉ በርካታ ሴራዎችን ሲያቀነባብር ከረመ፤ ሁሉንም ክልሎች ባዳረሰው የጥፋት ስራው የበርካታ ንጹሃን ዜጎች ህይወት ተቀጠፈ፤የአካል ጉዳት ደረሰ፤ ሰው ካደገበት ቀዬ እንደ ዋዛ የሚፈናቀልበት አጋጣሚ ተፈጠረ፤ ኢኮኖሚውም ክፉኛ ተጎዳ። በስተመጨረሻም በእብሪት ተወጥሮ በቀቢጸ ተስፋ ቃታውን ወደ ራሱ በመሳብ በትግራይ ክልል በሚገኘው የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የሰሜን እዝ ላይ እጅግ አሳፋሪ ጥቃት ፈጸመ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ህዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ ልዩ ስብሰባ ላይ በመገኘት በወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ በሰጡበት መድረክም፤ ጁንታው የለውጥ ሃይሉ ወደ አመራርነት እንዳይመጣ ሲሰራ ከነበረው ደባ ጀምሮ በሰሜን እዝ ላይ ጥቃት ፈጽሞ የተሰጠውን አጸፋ በተመለከተ፤ ከመነሻው እስካሁን የተመጣበትን በአሜኬላና በእሾህ የታጠረ ጉዞ እንዲሁም የታለፈበትን ትዕግስት፣ ጥበብና ጽናት አስረድተዋል። የአንደበታቸውንም ፍሬ በጽሁፍ ለማስፈር ሞክረናል ...

# የጽሁፉ አቀራረብ

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በወቅታዊ ጉዳይ ላይ በምክር ቤት ቀርበው የሰጡትን ማብራሪያ ከጥቂት ማስተካከያ ውጪ ቃል በቃል፣ ፍሰቱንም ጠብቆ ለማቅረብ ሙከራ ተደርጓል።

በተሰጠው ምላሽ ላይ ማብራሪያ የሚፈልጉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከምላሹ ጋር ከመቀላቀል ይልቅ በግርጌ ማስታወሻ (foot-note) ተጨማሪ ሃሳቦች ተካተዋል። እነዚህ የግርጌ ማስታወሻዎች ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ማብራሪያ ላይ ይበልጥ ግልጽነት ለመፍጠር እንዲያግዙ የተካተቱ መሆናቸው ሊጤን ይገባል። ለአቀራረብ እንዲመች ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ በንዑስ ርዕስ ለመከፋፈል ተሞክሯል፤ መሸጋገሪያ የሚሆኑ አንቀጾችም ተካተዋል።

# ተጠየቅ?

ህዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም ማለዳ ነው። የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ያቀረበውን ጥሪ ተከትሎ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በሚገኘው አዳራሽ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ ልዩ ስብሰባ ላይ ለመታደም የምክር ቤቱ አባላትና ሌሎችም በርካታ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉ ሰዎች ተገኝተዋል።

በኢፌዴሪ የመንግሥት አወቃቀር ከፍተኛውን የስልጣን እርከን የያዘው የህግ አውጪው አካል አፈጉባኤ ክቡር አቶ ታገሰ ጫፎ መድረኩን በተለመደው የምክር ቤቱ ደንብ መሰረት አስጀምረው መርተውታል። አባላቱም የህወሓት ስግብግብ ጁንታ በትግራይ በሚገኘው የሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ በህብረተሰቡ ዘንድ ለሚመላለሱ ሃሳቦች በቂ መረጃ እንዲተላለፍ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አንስተዋል። ድርጊቱ በመላው ዜጋ ያቀጣጠለውን የቁጭት መንፈስ በሚመጥን መልኩ የስራ አስፈጻሚውን ቁንጮ <<ተጠየቅ?>> በማለት ሞግተዋል።

በምክር ቤቱ አባላት የተነሱት ጥያቄዎች፤ ስግብግቡ የህወሐት ጁንታ በትግራይ ክልል መሽጎ በርካታ ሀገራዊ ቀውስ ሲፈጥርና ለጦርነት ሲዘጋጅ በመንግሥት በኩል የተወሰደው እርምጃ ለምን ዘገየ? ከተካሄደው የህግ ማስከበር ዘመቻ ጋር በተያያዘ የነበረው ሂደት ምን ይመስላል? በመከላከያ ሚኒስቴር ዘንድ የተፈጠረው ክፍተት ለጥቃት የሚዳርግ አልነበረም፤ይህም የሠራዊቱን ሪፎርም ውጤታማነት አጠያያቂ አያደርገውም? አጋጣሚውን በመጠቀም የሚከሰቱ ውጫዊና ውስጣዊ ጫናዎችን ለመመከት ያለው ዝግጁነት እንዴት ይገለጻል ? በሚሉ ቁልፍ ጉዳዮች ይጠቃለላሉ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተቀብለው የሰጡት ማብራሪያ የኋላውን የቃኙ፤ ዛሬ ላይ ላጋጠሙት ፈተናዎች መነሻ የሆኑ ነባራዊ ሀቆች የተተነተኑበት፤ በአመንክዮም የተደገፉ ነበሩ። እነሆ ምላሻቸውን ከእንደበታቸው ...





















# ዋዜማ

## የዋዜማው ምጦች

በለወጡ ዋዜማ የነበረው ፖለቲካዊ ሽኩቻ ምን ድባብ ነበረው ? ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሩቁን ትተው አይቀሬው ለውጥ እውን ሊሆን ጥቂት ጊዜያት ሲቀሩ በትዕቢትና በግፍ ከደነደነው ስርዓት ጋር የተደረገውን የመጨረሻ ትንቅንቅ አስታውሰዋል። የህወሓት ጁንታ የለውጡን መሪዎች ያሳድድ የነበረበት ሁኔታ፤ በኢህአዴግ ሊቀመንበር ምርጫ እኩይ አላማውን የሚያስቀጥሉለትን ሰዎች ወደ ፊት ለማምጣት ሲያደርግ የነበረውም ሴራ ተብራርቷል፤ ሌሎችም በዋዜማው የነበሩ አስጨናቂ ትዝታዎች ተነስተዋል...



< < የተነሱት ጥያቄዎች ዛሬ ከምንገኝበት ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በቀጥታ የሚያያዙ ቢሆኑም፤ ላለፉት ሁለት ዓመታት ተከቱል በዘለቀው የለውጥ ጉዞ የነበሩትን ፈተናዎች በተወሰነ መልኩ መለስ ብሎ ማብራራትና አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ አስከትሎ መግለጽ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

አብዛኛው ጥያቄ የመንግሥትን ቁመናና የማድረግ አቅም፣ ሀገርን ከመፍረስ፣ ዜጎችን ከሞት ከመታደግ ጋር ስለሚያያዝ፤ ይህ የህልውና ጥያቄ ወደፊትም ለሚገጥመን ፈተና ወሳኝ መሆኑን በማመን በተወሰነ ደረጃ ሁሉንም ባይሆን ከመሰረቱ ምን መልክ እንዳለው፣ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ሙከራ አደርጋለሁ።

በለውጡ ዋዜማ የነበረው በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የማፈናቀል፣ በርካቶችን በአንድ ጉድጓድ የመቅበሩ ነገር አሁን ከምናየው  ልምድ ጋር መመሳሰሉ ከአንድ ኮሌጅ የተመረቁ ሰዎች ያኔም ዛሬም ድርጊቱን የሚፈጽሙ መሆኑን ስለሚያመለክት ሊታወስ የሚገባው ዳራ ነው።"

1 ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

< < ከ2010 ሀገራዊ ለውጥ በፊት በነበሩት 27 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን ግርፋት፣ አፈና፣ ስቃይ፣ የህዝቦች የዴሞክራሲና የእኩል ተጠቃሚነት ጥማትን በተመለከተ ጊዜ ወስጄ መግለጽ አልፈልግም - የተከበረው ምክር ቤት በደንብ የሚያውቀው ጉዳይ ስለሆነ። የኢትዮጵያ ህዝብም ያለፈበትን ህይወት አልፎ አልፎ የመዘንጋት ችግር ቢኖርም ማስታወስ ስለሚችል፤ ያንን አስቸጋሪ ዘመን በተመለከተ ጠለቅ ብዬ ለማብራራት ጊዜ አልወሰድም።

ነገር ግን ከለውጡ ዋዜማ ጥቂት ወራት ወደ ኋላ መለስ ብዬ ከመሰረቱ የነበሩ ሂደቶችን ማሳየቱ አስፈላጊ ይሆናል። ታስታውሱ እንደሆነ የዛሬ ሁለት ዓመት ተኩል ገደማ በለውጡ ዋዜማ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆኑ ግጭቶች፣ መፈናቀሎች፣ በአንድ ጉድጓድ በርካታ ሰዎችን የመቅበር፣ የማስለቀስ፣ የማሳዘን፣ የማስጨነቅ በእሮሮ የተመላ ህዝብና ሀገር የማድረግ ሁኔታ በስፋት ይታይ ነበር።

በለውጡ ዋዜማ የነበረው በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የማፈናቀል፣ በርካቶችን በአንድ ጉድጓድ የመቅበሩ ነገር አሁን ከምናየው  ልምድ ጋር መመሳሰሉ ከአንድ ኮሌጅ የተመረቁ ሰዎች ያኔም ዛሬም ድርጊቱን የሚፈጽሙ መሆኑን ስለሚያመለክት ሊታወስ የሚገባው ዳራ ነው።

በዚያ ዘመን ብዙ እሮሮና ብዙ ጭንቀት ነበር። ህዝቡን በገፍ በማሰርም የመብት ጥያቄዎችን ለማፈንና ለማስታገስ ተሞክሯል። ለምሳሌ የኢሬቻ በዓል ሲከበር የኢትዮጵያን ደህንነት እንዲያስከብር የተቋቋመው ተቋም[1] በርከት ያሉ የኦነግን መለያዎች ያሳትምና የፈለገውን ሰው አስይዞ ስነስርዓቱ የሚከናወንበት ስፍራ ካስገባ በኋላ ያሻውን ለማሰር፣ ያሻውን ለመግደል የአሸባሪ ድርጅት ባንዲራ በማለት ይጠቀምበታል። ሌላም ቦታ ኮከቡ የሌለውን ባንዲራ ያዛችሁ በማለት በጣም በርካታ ሰዎችን ያስራል፤ ያንገላታል፤ ያስጨንቃል፤ ያፍናል።



## መፈንቅለ ሰው

በህወሓትና በግብረአበሮቹ የሚመራው አፈናና ግድያ የለውጥ ፍላጎቱን ሊገታው አልቻለም። ይህ እንደማያዋጣ ሲረዱ የመፈንቅለ መንግስት ሴራ መጠንሰስ ጀመሩ። ከፊል የኢህአዴግ አመራሮች <<ይህማ መፈንቅለ መንግስት ሳይሆን መፈንቅለ ሰው ነው መባል ያለበት>> በማለት ሞገቱ፤ ለምን ይህን አሉ? እቅዱስ ተሳካ ...?

<< ይህ ጉዳይ ህዝብ ለለውጥ የነበረውን ፍላጎት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው አስተዳደር መልክና አሠራር እንዲቀይር የነበረውን መሻት ሊያስቆም አልቻለም። በመሆኑም ግፊቱ እየበረታ በመምጣቱ ከለውጡ ጥቂት ቀደም ብሎ የመፈንቅለ መንግሥት ውይይቶችና ድርድሮች ተጀምረው ነበር።

ይህ ሴራ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ[2] ዘንድ በመድረሱም <<እኔ እኮ እዚህ ያለሁት ለማገልገል ነው፤ መፈንቅለ መንግሥት አያስፈልግም። ኃይለማርያም አያስፈልግም ካላችሁ በማንኛውም ሰዓት ስልጣኔን ለመልቀቅ ዝግጁ ስለሆንኩ መፈንቅለ መንግሥት ምን ያደርጋል?>> በማለት በግልጽ በዚህ ጉዳይ ከሚመክሩ ሰዎች ጋር ተወያይተዋል።

2 ከመስከረም 2005 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩ።



*ሌሎቻችን ደግሞ < < መፈንቅለ መንግሥት ሳይሆን መፈንቅለ ሰው ነው መባል ያለበት > > ስንል ነበር። መንግሥት እንዴት ራሱን ይፈነቅላል፣ መንግሥት ማለት መከላከያ፣ መንግሥት ማለት ደህንነት ነው። መንግሥት ራሱ የሚመራውን ሀገር እንዴት ይፈነቅላል፤ መፈንቅለ ሰው ነው የሚሆነው። መፈንቅለ ሰው ደግሞ ብዙ ማቀድ፣ መወያየት ላያስፈልገው ይችላል የሚሉ አስተያየቶችም ተሰንዝረዋል።*

*ከመፈንቅለ መንግሥቱ ጋር በተያያዘ ሃሳቡን የማይደግፉ ሰዎችም በመካከላቸው ነበሩ።[3] በዚህም የመፈንቅለ መንግሥቱ ሃሳብ ቀርቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣናቸውን ሲለቁ ስለሚያስቀምጡት ግለሰብ ማሰብ ተጀመረ።*

ይህ ሴራ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ዘንድ በመድረሱም ‹‹እኔ እኮ እዚህ ያለሁት ለማገልገል ነው፤ መፈንቅለ መንግሥት አያስፈልግም። ኃይለማርያም አያስፈልግም ካላችሁ በማንኛውም ሰዓት ስልጣኔን ለመልቀቅ ዝግጁ ስለሆንኩ መፈንቅለ መንግሥት ምን ያደርጋል?›› በማለት በግልጽ በዚህ ጉዳይ ከሚመክሩ ሰዎች ጋር ተወያይተዋል”

3 የኢፌዴሪ ጦር ሃይሎች ኤታማዦር ሹም የነበሩት ጀነራል ሳሞራ የኑስ ከሪፎርሙ በኋላ በክብር ከሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መሰናበታቸው ይታወቃል። በሰኔ 2012 አውሎ ሚድያ ከሚባል በዩቱዩብ ከሚሰራጭ ገጽ ጋር ባደረጉት ቆይታ የሰነዘሩት አስተያየት በአገዛዙ ከነበሩ ሌሎች ግለሰቦች ጋር ተመሳሳይ አቋም በመያዝ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ የሚደረግ ምክክር ተቀባይነት እንደሌለው መቃወማቸውን ይጠቁማል። ጀነራል ሳሞራ የኑስ በቃለ መጠይቁ ወቅት ካነሱት ሀሳብ የሚከተለው ይገኝበታል ‹‹ኢህአዴግ በለውጡ ዋዜማ ሲያካሂድ በነበረው ጥልቅ ተሃድሶ ለበርካታ ቀናት ሁሉም አባል በስብሰባ ላይ ነበር። በወቅቱ ሀገረን ማፍረስ የሚፈልግ ደግሞ ብዙ ነው። ለምን መፈንቅለ መንግስት (ኩዴታ) አታደርጉም ባይ መዓት ነበር። ፖለቲከኞች የፈለጉትን ይበሉ፤ ህጋዊ በሆነ መንገድ ውሳኔዎች ወስነው ሠራዊቱ ግን ‹እኔ እሻላለሁ› ካለ አደጋ ነው። እኔ ወታደር ነኝ፤ በፖለቲካ ውሳኔ እጄን አላስገባም ማለት ነው። ወታደር ከፖለቲካ ነጻ መሆን አለበት … ››

## አሻንጉሊት የማስቀመጥ ሽኩቻ

‹‹ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ተነስተው የሚቀመጠው ሰው በእኛ ፍላጎትና መሻት መሆን አለበት›› የሚለው አመለካከት የመፈንቅለ መንግስቱን እቅድ የሰረዘውና የሀገሪቱን ስልጣን በቀጥታም በተዘዋዋሪም የተቆጣጠረውና በኋላም ወደ መቀሌ በመሸሽ ለበርካታ ሀገራዊ ቀውስ መነሻ የሆነው ስግብግቡ የህወሓት ጁንታ መሆኑ ይታወቃል። የቡድኑ አባላት ግባቸውን ለማሳካት ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ብቁ የሆኑ ግን የማይፈልጓቸውን ሰዎች ማሳደድ እንዲሁም በእነርሱ ሃምሳል ተቀርጾ በመንበረ ስልጣኑ ላይ እንዲቀመጥ የሚፈልጉት አሻንጉሊት ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲመረጥ በተለያዩ የኢህአዴግ ስብሰባዎች ማሴር ጀመሩ ...

እነርሱ ከሚፈልጉት ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትር›› ውጪ ወደ አመራርነት ሊመጣ ይችላል ብለው የገመቱት ግለሰብ ላይ በደህንነት ተቋማት አማካኝነት ‹‹አክቲቭ ሰርቪላንስ›› ማድረግ ጀመሩ። የደህንነት ተቋማት ተደብቀው ሳይሆን በግልጽ እኛ (የለውጡ መሪዎችና በቀጣይ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ተወዳድረው ሊያሸንፉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ግለሰቦች) እያወቅን ክትትል ያደርጉብናል። ለምሳሌ እኔ ከቤቴ ስወጣ መኪና ቆሞ ይጠብቀኛል፤ እስከ ቢሮ ይከተለኛል። በምንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ በተደበቀ መንገድ ሳይሆን በግልጽ ክትትል ይደረጋል። ይህ በእኔም በሌሎች ጓዶችም የሚተገበር ነው።

ይህንን በወቅቱ በመድረክ አንስተነው ነበር። ብዙ መጨነቅ አያስፈልግም፣ ለእኛ ጊዜና ነዳጅ አታባክኑ፤ ሀገር የሚያስጨንቁ ብዙ ጉዳዮች አሉ የሚልም ሃሳብ አንስተናል። ግን በዚህ አልቆመም፤ ውጠራ ነበር። ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት፣ በኦህዴድ ጽህፈት ቤት እና በሌሎችም የክልሉ ቢሮዎች አካባቢ የነበሩ ፎቶች ሁሉ በብሬል ተወጥረዋል። በማንኛውም ሰዓት ልንገድላችሁ እንችላለን፤ እረፉ! የሚል መልዕክት በግልጽ ማስተላለፍ ነበር አላማው።

በዚያ ጊዜ ጥቂት ሰዎች ተመካክረን በማንኛውም ሰዓት ግድያ ሊያጋጥም ስለሚችል የተጀመረው ትግል እንዳይቋረጥ ልክ እኛ እንደታሰርን፤ እንደተገደልን ታሳቢ አድርገን መልዕክት አዘጋጅተን በቪዲዮ ተቀረጽን። ለኢትዮጵያ ህዝብ ትግሉ እንደዚህ ነው፤ እኛን ቢያፍኑን ወይም ቢገድሉን ትግሉ እንዳይቋረጥ የሚል ዝርዝር መልዕክት የያዘውን ቪዲዮ ከሰዎች ዘንድ በምስጢር አስቀመጥነው። በጽሑፍ አንዳንድ መረጃዎችን ጭምር አዘጋጅተን ነበር። በማንኛውም ሰዓት አደጋ ሊያጋጥም እንደሚችል ግልጽ ስለነበር እኛ ብንታሰር፣ ብንገደል ወይም ችግር ቢደርስብን በምስጢር ሰዎች ጋር የተቀመጠው ቪዲዮ ወዲያው እንዲወጣ በሚል ነበር።

> “እነርሱ ከሚፈልጉት ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትር›› ውጪ ወደ አመራርነት ሊመጣ ይችላል ብለው የገመቱት ግለሰብ ላይ በደህንነት ተቋማት አማካኝነት ‹‹አክቲቭ ሰርቪላንስ›› ማድረግ ጀመሩ። የደህንነት ተቋማት ተደብቀው ሳይሆን በግልጽ እኛ እያወቅን ክትትል ያደርጉብናል...”




ሲደረግ ከነበረው ከትትል በኋላ በኢህአዴግ ስብሰባ ላይ ጉዳዩን አንስተን ውይይት ሲደረግ፤ አንድ ደረጃ ከፍ አደረጉና ልንመረጥ ጥቂት ቀናት ሲቀሩ እንድንታሰር የእስር ትዕዛዝ ወጣብን።[4]

ይህ ሁሉ በዚህ ኃይል የማይፈለጉ ሰዎችን ማስቆምና ሌላ መንግሥት የሚመስል ግን መንግሥት ያልሆነ አካል ማስቀመጥ ፍላጎት ስለነበር ነው። እኛ በእርግጥ የተቀናጀ የትግል ስልት ስለነበረን፤ ብዙዎች ለውጡን የመሩ ሰዎች ጉዳዩን በቅርበት ስለሚከታተሉትም አብዛኛው ጉዳይ የሚሳካ አልነበረም። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ ምክትሉ (አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝና አቶ ደመቀ መኮንን) በውስጣቸው ለውጥ እንዲመጣና ለውጡ እንዲፋፋም ፍላጎት ነበራቸው። እዚያና እዚህ ሲመላለሱ የነበሩና መሃል ላይ የሚዋዥቁ ሰዎች ቢኖሩም፤ እኛ መስማት የሚፈልጉትን መረጃ እየላክንላቸው፤ እነርሱም ምን እያሰቡ እንደሆነ እያወቅን እንድንዘጋጅ ዕድል የሚሰጥ ጊዜ ነበር።

> በኢህአዴግ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለሳምንታት የአባላቱን ቀልብ ለመግዛትና መልክ ለማስያዝ ግምገማ ሲባል ሲጀመር ሲበተን  የሚጨበጥ ነገር ሳይያዝ ቆየ... ሌሎች ወደ ስልጣን የሚመጡት በመቃብራችን ላይ ብቻ ነው ብለው በየመሸታ ቤቱ በግልጽ ሲፎክሩ ቢቆዩም፤ በፖለቲካው መድረክ የመጀመሪያው ያልተጠበቀ አደገኛ ሽንፈት አጋጠማቸው..."

ይህንን ይዘን ወደ ምርጫ ስንገባ የመጀመሪያው የኢህአዴግ ሊቀመንበር ምርጫ (ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ የስልጣን መልቀቂያ ካቀረቡ በኋላ መጋቢት 11 ቀን

4 በኢትዮጵያ እየተባባሰ በመጣው ቀውስ የተነሳ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲኖር በሚል የካቲት 8 ቀን 2010 ዓ.ም ከኢህአዴግ ሊቀመንበርነት እንዲሁም ከጠቅላይ ሚኒስትርነት ለመነሳት ጥያቄ ማቅረባቸውን ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል። ይህን ተከትሎ ከመጋቢት 11 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው የኢህአዴግ ምክር ቤት ስብሰባ፤  የአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ጥያቄ  በሙሉ ድምፅ ተቀብሎ መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም ዶክተር ዐቢይ አሕመድን አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀ-መንበር አድርጎ በመሾም ተጠናቋል።  በተካሄደው የግንባሩ ሊቀመንበር ምርጫ ኦህዴድን ወክለው በእጩነት የቀረቡት ዶክተር ዐቢይ አሕመድ 108፣ ደኢህዴንን ወክለው በእጩነት የቀረቡት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ 59 እንዲሁም ህወሓትን ወክለው በእጩነት የቀረቡት ዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል 2 ድምፅ አግኝተዋል። ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ሌሎችም የለውጡ መሪዎች የእስር ትእዛዝ የወጣባቸው ይህ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት በነበሩት ቀናት ነው።



> ድምጽ መስጠት ከሚችሉ ሰዎች ከአንድ ሰው በስተቀር ድምጽ ሰጥቶ መርጧል። ያቺ አንድ ድምጽ የእኔ ነበረች...”

2010 ዓ.ም ተጀምሮ መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም የተጠናቀቀው) በኢ.ህአዴግ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለሳምንታት የአባላቱን ቀልብ ለመግዛትና መልክ ለማስያዝ ግምገማ ሲባል ሲጀመር ሲበተን የሚጨበጥ ነገር ሳይያዝ ቆየ።

ከዚያ ምርጫውን ያደረግን ዕለት ሙሉ ቀን በምርጫው መስፈርት ላይ ስንወያይ ውለን፣ አጨቃጫቂ፣ ከአሁኑ ጦርነት ያልተናነሰ ሂደት ታልፎ የተደራጀው የጁንታው ስብስብ በቀጥታ ሳይሆን በጎን ማዋጋት በሚችልበት መንገድ ሁሉ ሰፊ ሥራ ከሠራ በኋላ ከምሽቱ አራት ተኩል አካባቢ ምርጫውን አሸንፈናል ብሎ የጁንታው የውጪ ክንፍ በየመጠጥ ቤቱ መጨፈር ጀመረ።

ይህ ከመሆኑ በፊትም እኛ የማንፈልጋቸው ሰዎች አይመጡም፤ ሌሎች ወደ ስልጣን የሚመጡት በመቃብራችን ላይ ብቻ ነው ብለው በየመሸታ ቤቱ በግልጽ ሲፎክሩ ቢቆዩም፤ በፖለቲካው መድረክ የመጀመሪያው ያልተጠበቀ አደገኛ ሽንፈት አጋጠማቸው። ይህ እንዲሆን በወቅቱ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ የኢ.ህአዴግ ምክር ቤት አባላት ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል።

በመጋቢት 2010 ዓ.ም አንድ ሰው ለማስመረጥ ያን ያህል ፈተና የነበረበት የኢ.ህአዴግ ምክር ቤት በኋላ ሃዋሳ በተደረገው ምርጫ አስር ደቂቃ ባልፈጀ ሂደት ድምጽ መስጠት ከሚችሉ ሰዎች ከአንድ ሰው በስተቀር ድምጽ ሰጥቶ መርጧል። ያቺ አንድ ድምጽ የእኔ ነበረች። ሦስት ተጠቁመናል እኔ ራሴን ትቼ ጓደኞቼን መረጥሁ።[5] ይሄ በመጋቢት ያን የሚያክል ሁከት ፣ ያን ያክል ጭቅጭቅ አላስፈላጊና መሰረት አልባ እንደነበር ያሳያል። ይህንንም የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ እፈልጋለሁ።

---

5 በሃዋሳ ከተማ ከመስከረም 23 እስከ 25 ቀን 2011 ዓ.ም በተካሄደው የኢህአዴግ 11ኛ መደበኛ ጉባኤ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ሆነው በድጋሚ መመረጣቸው ይታወሳል። በወቅቱ ዶክተር ዐቢይ ከጠቅላላው 177 ድምፅ 176ቱን በማግኘት ተመርጠዋል። እኔ ራሴን ትቼ ጓደኞቼን መረጥሁ ያሉትን የሚያስረዳ አሃዛዊ ማረጋገጫ ነው።

# ማግስት




## አዲስ መንገድ ...

ለውጡ እውን ሆነ። በለውጡ
ማግስት ፊት መሪዎቹ
ሰላምን፣ይቅርታን፣ አንድነትን፣
እኩልነትንና ፍቅርን
ለኢትዮጵያውያን አበሰሩ፤ በሂደት
በተግባርም አስመሰከሩ። አዲስ
መንገድ አመላከቱ ...



ለውጡ እውን ከሆነ በኋላ፤ የለውጡ ኃይል በግድያ ሙከራ፣ በአፈና ፍላጎት፣ በክትትልና በመሳሰሉት በግሉ የተበደለ እንደነበር ይታወቃል። የኢትዮጵያ ህዝብም እንደ ህዝብ የተጨቆነ የተገፋ በመሆኑ ከፍተኛ የጥላቻና የመገፋት ስሜት ይንጸባረቅበታል። በዚያ ሁኔታ ውስጥ በኢትዮጵያ ታሪክ በተለመደ መልኩ የመንግሥት ለውጥ የምናደርግ ከሆነ እንጠፋፋለን። የማንፈልገው ኃይል በበቂ ደረጃ የታጠቀ፣ ሌላው ደግሞ የተበደለ ነገር ግን በደልና ግፍ ቢጠላም፤ ያልተደራጀ፣ ትጥቅ የሌለው በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ እልቂት ያጋጥማል። ይህ እንዳይሆን የተረክ ለውጥ እናድርግ፤ የከረረ ጥላቻ ይዘን ከታጠቀ ኃይል ጋር የሚደረግ ጭቅጭቅና ንትርክ ወደ ከፋ ደረጃ ሊወስድ ስለሚችል ያጠፉ ሰዎች ስላጠፋችሁ እናጥፋችሁ አንበላቸው፤ የሚለው የይቅርታ መንገድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር።

አንድ ሰው በደሉ በሁለት መንገድ ሊሽር ይችላል። አንድም በይቅርታ፤ አልያም በፍትህ ወይም በበቀል። እኛ በይቅርታ በደሎቻችንን ረስተን በመደመር፣ በወንድማማችነት፣ በፍቅር፣ በይቅርታ እንሻገር ፤ ያለፈውን በደል እንተወው ይቅር እንባባል አልን። ያለፈውን በደል ካነሳን እግሩ የተቆረጠ፣ ጥፍሩ የተነቀለና አባት ያጣ አለ፣ እናትም ያጣች አለች። በመንግሥት ምሬት ተሰድደው በየባህሩ የቀሩ ሰዎች አሉ። ይህ ሁሉ በደለኛ በየአካባቢው የበቀል ዕርምጃ ከወሰደ መተላለቅ ስለሚመጣ በደሉን አፍነን እርቅ፣ ሰላምና ፍቅር እንዲኖር ብንሠራ ይሻላል።

> “እኛ በይቅርታ በደሎቻችንን ረስተን በመደመር፣ በወንድማማችነት፣ በፍቅር፣ በይቅርታ እንሻገር፤ ያለፈውን በደል እንተወው ይቅር እንባባል አልን። ያለፈውን በደል ካነሳን እግሩ የተቆረጠ፣ ጥፍሩ የተነቀለና አባት ያጣ አለ፣ እናትም ያጣች አለች። በመንግሥት ምሬት ተሰድደው በየባህሩ የቀሩ ሰዎች አሉ። ይህ ሁሉ በደለኛ በየአካባቢው የበቀል ዕርምጃ ከወሰደ መተላለቅ ስለሚመጣ በደሉን አፍነን እርቅ፣ ሰላምና ፍቅር እንዲኖር ብንሠራ ይሻላል...”

የመጠፋፋት ፖለቲካ አልጠቀመንም፤ መንግሥታት ሲቀየሩ ከዜሮ መጀመር ኢትዮጵያን ወደ ኋላ እያስቀራት ነው። የይቅርታን ሃሳብ ይዘን በብዙ መድረኮች በብዙ መንገዶች ለህዝባችን፤ ለዚህ ኃይልም ገለጽን። ቀጣይ ሥራ መሆን ያለበት በሁሉም፣ ለሁሉም ከሁሉም የሆነ ሀገረ መንግሥት መገንባት ነው የሚለውን ለማስረዳት ሞከርን።

በሁሉም ሲባል እያንዳንዱ ሰው አስተዋፅኦ የሚያደርግበት፤ ለሁሉም ስንል ተጠቃሚና የማይጠቀም፣ ባለቤትና ባዕድ፣ ጎረቤትና ዋነኛ የሚባል ሳይኖር ሁሉም በእኩል የሚሳተፍበት፤ ከሁሉም ሲባል ደግሞ ሁሉም እኩል የሚገለገልበት ማለት ነው።

በሁሉም፣ ለሁሉም ከሁሉም የሆነ ሀገረ መንግሥት እንገንባ የሚል ጥያቄ ስናነሳ ይህ ስብከት ነው፤ ሰባኪዎች ናችሁ። ሀገርን በስብከት መምራት አይቻልም፤ ሀገር መምራት እንደ እኛ ፊት ለፊት የምንለውን እያልን ከኋላ ማፋጀት ካልሆነ በስተቀር ስለ ፍቅርና መደመር እየተናገሩ ሀገር መምራት አይቻልም አሉ። መንግሥትም ደካማ ነው አሉ። በእርግጥ መንግሥት ደካማ ነው ! መንግሥት ማለት የግለሰቦች የግል ብቃት፣ የግለሰቦች የግል እውቀት ማለት ሳይሆን የተቋማት ጥንካሬ ማለት ነው። ተቋሙን እንዳይሆን አድርገን ከሠራን በኋላ <<መንግሥት ደካማ ነው>> የሚል ክስ ማምጣት እምብዛም ውሃ አይቋጥርም። ግለሰቦች ምንም ቢሆኑ ምን ተቋም የሌለው ማንኛውም መንግሥት ደካማ ነው።

## ማግለቱን በጥበብ

**ሀገራዊ ለውጡን ሲገዳደር የነበረው ሃይል አዲሱን የለውጥ መንገድ በየሰበቡ ያጣጥል ጀመር። <<የለውጡ ሃይል ሰባኪ እንጂ ሀገር መሪ አይደለም>> የሚል ትችት መሰንዘር ቀጠለ። ለትዕግስት የተሰጠው ዕድልም የለውጡን ተቀናቃኞች የልብ ልብ እንዲሰማቸው አድርጎ በየስፍራው ግጭትና ሁከት እንዲጠነስሱ በር ከፈተ፤ ወዲህ ደግሞ ከተለያዩ አካላት እርምጃ አይወሰድም እንዴ? የሚለው ግፊት በረታ። የለውጡ ሃይል ግን መስቀለኛ መንገድ ላይ ነች የምትባለውን ኢትዮጵያ ቀጣይ ጎዳና ለማቅናት ከለውጡ ማግለት የነበረውን ጉዞ አቅሙን ፈትሾ የኃይል አሰላለፍና የሁኔታ ትንተና ሰርቶ በጥበብ ለመምራት ወስኖ ነበር...**

በተከበረው ምክር ቤት፣ በብዙ የፖለቲካና የሚዲያዎች ሰዎች ለምን ቀድሞ ዕርምጃ አልተወሰደም? አልዘገየንም ወይ? በዚህስ ዋጋ አልከፈልንም? ወዘተ... የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ይህ ጉዳይ በመፈለግና በማድረግ መካከል ያለን ልዩነት ካለመገንዘብ የመነጨ ነው። መሻት፣ ማለምና መፈለግ ይቻላል። ያንን መከወን ግን ተቋማዊ ብቃት ይፈልጋል።

የኢትዮጵያ ቀንደኛ የፖለቲካ ችግር የገዘውም የተፎካካሪውም ፓርቲዎች ወይም የፖለቲካ ሰዎች አንድን ነገር ከማድረጋችን በፊት ጥንቅቅ ያለ የኃይል አሰላለፍ ትንተና ማድረግ አለመቻል ነው። አንድ መንግሥት፣ አንድ ፓርቲ በማንኛውም ሥራ ውስጥ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ የሚያስችለው በበቂ እውቀትና በእውነተኛ መረጃ ግብዓትነት የተመሰረተ የኃይል አሰላለፍ ትንተና ሲያደርግ ነው። በውስጥ ያለው ኃይል ምን ይመስላል? በውጪ ያለው ኃይል ምን ይመስላል? ይሄ ኃይል ግጭት ቢፈጠር ምን ዓይነት ሽንፈት፤ ምን አይነት ድል ሊያጋጥመው ይችላል? ብሎ መተንተን በእጅጉ ያስፈልጋል።

የኃይል አሰላለፍ ትንተና ስለማይሠራ ሰው ይነሳና በሦስት ወር መንግሥት እሆናለሁ ይላል። መንግሥት ለመሆን ጠላትን በትክክል ማወቅ፣ ራስን ማወቅ፣ የጠላትን የማድረግ አቅም መለየት ፣ የራስን አቅም መለየት፣ እንዴት ጠላትን ማዳከምና ማሸነፍ እንደሚቻል መገንዘብ ያስፈልጋል። ዝም ብሎ ሰብሰብ ብሎ ፓርቲ ነን፤ እናሸንፋለን፣ በስድስት ወር መንግሥት እንሆናለን ማለት ምኞት ነው። ለዚህም ነው ባለፉት 40 ዓመታት ብዙ ፓርቲዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጠሩ ማሸነፍ ያልቻሉት። ስለዚህም የኃይል አሰላለፍ ትንተና በደንብ ካልተሠራ ድል የምንመኘው እንጂ የምናረጋግጠውና የምንጨብጠው አይሆንም።

ከዚህ በተጨማሪ የሁኔታ ትንተና በራሱ አስፈላጊ ነው። ምንድነው ያለው ሁኔታ መንግሥት የሚባለው አካል ምን ይመስላል? ተቃዋሚ የሚባለው አካል ምን ይመስላል? አካባቢ ሀገራት ምን ይመስላሉ? እዚህ ውስጥ ምን ዓይነት ኦፕሬሽን ብናካሂድ ስኬታማ ልንሆን እንችላለን ተብሎ የሁኔታ ትንተና ይሠራል።

## <<እስረኛው>> ጠቅላይ ሚኒስትር

**ነገሮችን በስኬት ለመቋጨት በብልሃት መጓዙ ከወሰደው ጊዜ ባሻገር፤ ለውጥ ያመጣሉ ተብለው የተሾሙት ጠቅላይ ሚኒስትር <<እስረኛ>> መሆን መንግሥት በተለያዩ አካባቢዎች ከሚያጋጥሙ ግጭቶችና ሁከቶች ጋር በተያያዘ ለምን በፍጥነት እርምጃ አልወሰደም የሚለውን ትችት ለማንሳት ድፍረት ያሳጣል፤ እንዴት?**

እነዚህን ጉዳዮች በዝርዝር የተገነዘበ ሰው ዕርምጃው ዘገየ የሚል ሃሳብ አያነሳም። ለምን ያላችሁኝ እንደሆነ እኔ በግሌ እንኳን ሀገሬን፣ እንኳን የሰጣችሁኝን ኃላፊነት በብቃት ልወጣ ይቅርና ራሴንና ቤተሰቤን መከላከል የማልችልበት ሁኔታ ላይ ነበርኩና።


ለምሳሌ ... እናንተ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነህ በህገ መንግሥቱ መሰረት ሀገር አገልግል ብላችሁ የሾማችሁኝ ቀን የደህንነት ሹሙ[6] ከእኔ ጋር በጥበቃ ሥራ ላይ የነበሩትን ሦስት ግለሰቦች ይዘህ ቤተመንግሥት መግባት አትችልም አለኝ። እኛ የሰጠንህ ጠባቂ ብቻ ነው የሚጠብቅህ ተብሎ እንዳይገቡ ተከለከሉ። ይሄ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኜ በተሾምኩበት የመጀመሪያ ቀን ያጋጠመኝ ነው። እኔ የግል ጥበቃዎቼ ላይ ማዘዝ የማልችል ሰውዬ እንዴት ነው ሀገር አትጠብቅም ተብዬ የምጠየቀው።

የምሠራበት ቢሮ ቁልፍ ያለውም በእነዚህ የደህንነት ጠባቂዎች እጅ ነው። ከፍተው የሚያስገቡኝ፣ አስወጥተው የሚቆልፉብኝም እነርሱ ናቸው። ቢሮዬ ውስጥ ካሜራ፣ ድምፅ መቅረጫ ወይም ሌላ ማንኛውም ጉዳይ ቢኖር በሌሎች ሀገራት እንደተለመደው ቢሮዬን <<ካውንተር ሰርቪላንስ>> አሰርቼና አጽድቼ ሥራ ልሠራ አልችልም። ምክንያቱም ጠዋት ሳልገባ ገብተው የፈለጉትን አስተካክለው በፈለጉት ሰዓት መጥተው ነው ግባ የሚሉኝ። ስለዚህ በስልክም ልወያይ አልችልም፤ አቶ ደመቀ  መኮንንም (ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን) ጠርቼ መወያየት አልችልም። ቢሮዬ ከእኔ ቁጥጥር ውጪ ነበር።

ከቢሮ በተጨማሪ የቤቴ ዋና ቁልፍ በእነርሱ እጅ ነው። አስገብተው የሚቆልፉብኝ እነርሱ ናቸው፣ ጠዋት ቁልፍ ከፍተው የሚያስወጡኝም እነርሱ ናቸው። እዚህ ውስጥ ነው እናንተ ዕርምጃ አልወሰደም፤ አልተከላከለም የሚል ጥያቄ የምታነሱት። የእናንተን ደህንነት ሳይሆን የራሴንና የልጆቼን ደህንነት ማረጋገጥ የምችልበት ደረጃ ላይ አልነበርኩም።

በዚህ አያበቃም። ቢሮዬና ቤቱ በእጄ አለመሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ፤ ወታደር ስለነበርኩኝ ሮጬ ለማምለጥ እንኳን የምችልበት መንገድ ካለ በማለት  የግቢውን ዙሪያ ለማየት ፈለኩኝ። በአካባቢው ያሉ ሰዎችን ግቢውን ልመልከት አልኳቸው። መልሱም  ይህ እኮ የተለመደ አይደለም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር  ከቢሮ ወደ ቤት፤ ከቤት ወደ ቢሮ ብቻ ነው መመላለስ የሚችለው። ስለዚህ ዓርብ ወደ ቤትህ አስገብተንህ ሰኞ እስክንወስድህ መውጣት አይቻልም

6 የደህንነት ሹሙ ጌታቸው አሰፋ ግንቦት 1993 ዓ.ም  የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ኃላፊ የነበሩት አቶ ክንፈ ገብረመድህን መገደልን ተከትሎ  የደህንነት ቢሮ ኃላፊ ሆነው  በመሾም  በጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሥልጣናቸው እንዲነሱ እስከተደረጉበት ዕለት ተቋሙን ለ17 ዓመታት ያህል መርተዋል።  በስልጣን ዘመናቸው በተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ግጭቶችን በማቀነባበር የፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ  የወጣባቸው ሲሆን፤ በቅርቡ ደግሞ በሰሜን እዝ ከተፈጸመው ጥቃት ጋር በተያያዘ ህዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም በድጋሚ በሀገር ክህደት ወንጀል የፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ወጥቶባቸዋል።




> ከቢሮና ከቤት ቢታለፍ ከግቢ አይቻልም፤ ከግቢ ቢታለፍ ዙሪያው እንዳልኳችሁ ነው። በአጭሩ ዘመናዊ እሥር ቤት ውስጥ ያለ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆኔን አወኩት...”

ተባልኩ። ቤት ሲባልም ቤት ውስጥ ብቻ እንጂ በረንዳውን የሚያካትት አልነበረም።

አይ እኔ እንደዚያ ዓይነት ጠቅላይ ሚኒስትር አይደለሁም። አካባቢዬን በደንብ ካላየሁ እቸገራለሁ ብዬ በግድ ግቢ ወጣሁ። ይህ ግቢ የታወቀ ክፍለ ከተማ የለውም፤ የታወቀ ቀበሌ የለውም። ግን ደንበኛ መንደር አለው። በየአጥሩ ሥር ልክ እንደ ጎዳና የላስቲክ ቤት አለ። ደሳሳ ጎጆ፣ መጸዳጃ ቤትና  የጭቃ ቤትም ይታያል። ግቢው መንደር ይሁን ቤተመንግሥት ግልጽ አይደለም። ትልልቅ ሰዎች፣ ሕፃናትና ሴቶች አሉ። ዙሪያው በሙሉ ሰው ነው። እነዚህ ሰዎች የሥራ ድርሻቸው ምንድነው ? ምን ያደርጋሉ? የሚለው ጉዳይ ግልጽ አይደለም። ስለዚህ ቢሮና ቤት ብቻ ሳይሆን ግቢም ሮጦ ለማምለጥ በፍጹም የማይቻልበት መሆኑን፤ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንዳለሁም በግልጽ ተገነዘብኩ።

አንድ ደረጃ ከግቢ ውጪ ወጣ ብዬ ስመለከት ደግሞ፤ በአንድ በኩል ጥይት ቤት የሚባል በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያሉበት፤ በአንድ በኩል የፓርላማው ጥበቃ ተብለው የተቀመጡ ሰዎች ያሉበት፤ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የቤተመንግሥት ገራጅ ተብሎ በርካታ ሰዎች ያሉበት፤ ዝቅ ሲባል ደግሞ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በህግና በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ልዩ ትጥቅ ያላቸው ወታደሮች  ይዞ ይጠብቃል። ስለዚህ ከቢሮና ከቤት ቢታለፍ ከግቢ አይቻልም፤ ከግቢ ቢታለፍ ዙሪያው እንዳልኳችሁ ነው። በአጭሩ ዘመናዊ እሥር ቤት ውስጥ ያለ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆኔን አወኩት።

ከዚህ እሥር ቤት ራሴን ነፃ ለማውጣትና ሀገር የሰጠኝን ኃላፊነት ለመወጣት በተለይ የተከበረው ምክርቤት የሚጠብቃቸውን ሪፎርሞች ለማሳካት የመጀመሪያው ሥራ ከቤተሰብ ጋር መመካከር ነበር። ቤተሰብ ስደት ላይ ስለነበር ይህ  ዘመናዊ እሥር ቤት ነው። ከዚህ እየወጣን በቲቪ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን አንችልም። ስለዚህም ተስማምነት ቤተሰብን ወደመጣበት መልሰን፤ በየቀኑ መታፈንም፣ መታገትም፣ መገደልም ሊያጋጥም እንደሚችል በማሰብ ነው የመጀመሪያ ሁለት ወር ሥራ የተሠራው።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳይሆን በእሥርቤት እንዳለ አንድ ሰው ነበርኩ። ነገር ግን ወጥቶ በሚድያ መታየት የሚችል። በዚህ ሰው የሚመራውን መንግሥት ነው ለውጥ አታመጣም ወይ? የሚል ጥያቄ የሚነሳው።

ከዚያ በኋላ ከጓደኞቻችን ጋር የነበረው ምክክር በተለይ ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ጋር ህዝቡ ይህንን ይህንን ይፈልጋል እኛ ያለንበት ሁኔታ ይህንን ይመስላል። ሃሳብ ማመንጨትና መጻፍ እንችላለን። ነገር ግን ወደ ሥራ አስፈጻሚ ካቢኔ ወርደን ብናወያይ ሃሳባችንን የሚያሳካ ሳይሆን የሚያደናቅፍ ኃይል ነው። እንዴት አድርገን ነው ህዝቡ የሚጠብቀውን ለውጥ ልናመጣ የምንችለው በሚል ተወያይተን <<ሳንድዊች አፕሮች>> እንከተል በሚል ተስማማን።

## የ<<ሳንድዊች አፕሮች>> እነ ማንን አስደነገጠ ?

**የለውጥ አመራሮቹ ከነበሩበት አጣብቂኝ በመላቀቅ ህዝቡ የሚፈልገውን ለውጥ እንዲያጣጥም <<ሳንድዊች አፕሮች>> የሚል አቀራረብን እንደ መላ ዘየዱ። የለውጥ ሀሳብና ህዝብን ተገን በማድረግ ለውጡን ለማስቀጠል የተጀመረው <<ሳንድዊች አፕሮች>> ግን ጥቂቶችን ድንጋጤ ውስጥ ከተተ፤ እነማን ይሆኑ? ለምንስ ደነገጡ?**

ሥራ አስፈጻሚውን እንተወውና ከላይ ሃሳብ እንለይ ፤ ከታች ህዝባችን እንዲገነዘብ እናድርግ መሀል ላይ ያለውን አመራር በዚህ እያፈንን ለውጡ ወደ ኋላ እንዳይቀለበስ የህዝብንም ስሜት የምንገነዘብበት መንገድ እንፍጠር ብለን ተስማማን። በዚሁ አግባብ ከህዝባችን ጋር እንገናኝ፤ ከህዝቡ ጋር እንምከር፣ ለህዝቡ ሃሳባችንን እንሸጥ፣ ህዝቡ ወታደራችን ይሁን፣ ጠባቂያችን ይሁን፣ ህዝቡ ለውጥ እንዳይቀለበስ የሚቆም ይሁን፤ እኛ ደግሞ በድፍረት ወደ ህዝብ እየወጣን ሃሳቦቻችንን እናካፍል አልን።

ይህንን ብለን የመጀመርያው ጉዞ ወደ ሱማሌ ክልል እንዲሆን ወሰንን። ቅድሚያ ወደዚያ የሄድንበት ምክንያት አሁን ያያችሁት አደጋ መጀመርያ የተዘጋጀው በሱማሌ ክልል ስለነበር ነው። የሰለጠነና የታጠቀ ከሠላሳ ሺ በላይ ልዩ ኃይል ተደራጅቶ ከላይ እስከታች



“ከጓደኞቻችን ጋር የነበረው ምክክር በተለይ ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ጋር ህዝቡ ይህንን ይህንን ይፈልጋል እኛ ያለንበት ሁኔታ ይህንን ይመስላል...
እንዴት አድርገን ነው ህዝቡ የሚጠብቀውን ለውጥ ልናመጣ የምንችለው በሚል ተወያይተን ‹‹ሳንድዊች አጥሮች›› እንከተል በሚል ተስማማን...”



ተቀናጅቶ፣ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ህልሙ የመጀመርያው ዒላማ በዚያ ክልል ነበር የተሞከረው። ከዚያ በተጨማሪ ከለውጡ በፊት ከፍተኛ መፈናቀልና ግድያ የነበረበት ሁኔታ ስላጋጠመ ያንን ማከም ያስፈልጋል ብለን ሱማሌ ክልል ለመሄድ ስንነሳ የደህንነት ሹሙ መሄድ አትችልም አለኝ። ለምን? የሚል ጥያቄ ሳነሳ አልሸባብ ሊገድልህ ስለሆነ መሄድ አትችልም የሚል ሆነ ምላሹ።

ይህ ተቀባይነት አልነበረውም። አንደኛ እንዳጋጣሚ ሆኖ የፈጠራ መረጃ እንዴት እንደሚሠራ በትንሹም ቢሆን ልምድ ስለነበረኝ፤ ሁለተኛ የመረጃ የተቋማት ሥራ ለውሳኔ ሰጪ አካል ውሳኔ የሚደግፍ መረጃ ማቅረብ እንጂ መወሰን አልነበረም። ይሄኛው ግን አትሄድም ብሎ ከውሳኔ ነው የሚጀምረው። እንደዚህ አይነት ጉዳይ አለ፤ ሳይሆን አትሄድም ብሎ ይወስንና ለምን? ስትለው ምክንያቱም አልሸባብ ሊገድልህ ስለሆነ ነው የሚለው።

እናም መልሴ የነበረው ሁለት ነገር ነው። አንደኛ አትወስን፤ ለውሳኔ የሚያበቃ መረጃ አምጣ፤ ሁለተኛ ዋናው ሊገድለኝ የሚፈልግ ኃይል መኖሩን ማወቅ ነው። ስለዚህ ዋናውን ነገር ሠርተኸዋል። ትልቅ ሥራ ነው የሠራኸው፤ ባታውቅ ኖሮ ድንገተኛ አደጋ ያጋጥመኛል፤ አሁን ስላወቅክ ይህንን ኃይል ተከላከል። እኔ ደግሞ ሥራዬን ልሥራ ብዬ ወደ ሱማሌ ክልል ሄድኩ። እንደምታስታውሱት ሱማሌ ክልል ጥሩ ጊዜ ነበረን። ከህዝብ ጋር ተወያይተን መጣን።

ከሱማሌ ክልል ከመጣሁ በኋላ ሁለተኛው ጉዞ ወደ መቀሌ ነበር። የትግራይ ህዝብም በነበረው ሁኔታ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ የተጎዳ ህዝብ ነው፤ ነገር ግን ከለውጡ ጋር ተያይዞ አደናጋሪ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ህዝቡን በማግኘት በራሱ ቋንቋ ያለንን ቅርበት ብናሳይ መልካም ነው ብለን ነበር ወደ ትግራይ ክልል የሄድነው። በእርግጥ ትግራይ ስሄድ ሊገድልህ የተዘጋጀ ኃይል አለ አልተባልኩም። ሄጄ ከተወያየን በኋላ የጁንታው ኃይል በጣም ከፍተኛ ድንጋጤ ተፈጠረበት።

ሱማሌ ያልተጠበቀ ነገር ተፈጠረ፤ የትግራይ ህዝብም በነበረው ውይይት ከፍተኛ አቀባበል አደረገ። ወጣቱም ለውጥ ፈላጊ ስለነበረ ደጋፊ ሆነ። እናም የሳንድዊቹ ሃሳብ ከመቀሌ በኋላ ገባቸው። ስለዚህ ይህንን ነገር ማስቆም አለብን። በዚህ ከቀጠልን ህዝቡን ይነጥሉብንና አደገኛ ነገር ይፈጠራል፤ ከቁጥጥር ውጪ ይወጣል የሚል ውይይት አደረጉ



ሱማሌ ክልል ለመሄድ ስንነሳ የደህንነት ሹሙ መሄድ አትችልም አለኝ። ለምን? የሚል ጥያቄ ሳነሳ አልሸባብ ሊገድልህ ስለሆነ መሄድ አትችልም የሚል ሆነ ምላሹ... እናም መልሴ የነበረው ሁለት ነገር ነው። አንደኛ አትወስን፤ ለውሳኔ የሚያበቃ መረጃ አምጣ፤ ሁለተኛ ዋናው ሊገድለኝ የሚፈልግ ኃይል መኖሩን ማወቅ ነው። ስለዚህ ዋናውን ነገር ሠርተኸዋል፡፡ ትልቅ ሥራ ነው የሠራኸው፤ ባታውቅ ኖሮ ድንገተኛ አደጋ ያጋጥመኛል፤ አሁን ስላወቅክ ይህንን ኃይል ተከላከል። እኔ ደግሞ ሥራዬን ልሥራ ብዬ ወደ ሱማሌ ክልል ሄድኩ።



ቀጥሎ ወደ አምቦ ነበር የምንሄደው። አምቦ ላይ ጠበቅ ተብሎ አትሄድም ኦነግ (የኦሮሞ ነጻነት ግንባር) ይገድለሃል ተባልኩ...
የሚገድለኝ ኦነግ ወይም አልሸባብ ሳይሆን በጉያዬ ያለ ኃይል መሆኑ ስለገባኝ፤ በሌሎች ኃይሎች ተጨማሪ የረድፍ ጥበቃ አድርገን አምቦ ሄድን። አምቦ በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረን...



ወደ ባህርዳርና ጎንደር እቅድ ስንይዝ የወልቃይት ኮሚቴ፣ የቅማንት ኮሚቴ የሚባሉ ሊገድሉህ እቅድ ይዘዋል፤ እቅዱም በእጃችን ላይ ስላለ አትሄድም ተባልኩ። እዚያ ያለውን ሥራ የአማራ ክልል አመራሮች እንዲሠሩት አድርገን ሄድን። ከሄድን በኋላ ህብረተሰቡን ማነጋገራችን ሳይሆን ከወልቃይት እና ከቅማንት ኮሚቴዎችን ጋር መወያየታችን በእኛና በደህንነት ተቋሙ መካከል ከሚጠበቀው በላይ መካረር ፈጠረ

ቀጥሎ ወደ አምቦ ነበር የምንሄደው። አምቦ ላይ ጠበቅ ተብሎ አትሄድም ኦነግ (የኦሮሞ ነጻነት ግንባር) ይገድለሃል ተባልኩ። እኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ከመሆኔ ከአንድ ወር በፊት አምቦ ሄጄ ነበር። በዚያን ወቅትም እንደምናሸንፍ፤ ለማሸነፍ እንደምንታገል እና ከህዝቡም ጋር ምን ማድረግ እንዳለብን ያወያየሁበት ቦታ ነው። በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ነው የሚገድልህ ኃይል ስላለ አትሄድም የተባልኩት፤ከዚያ ገባኝ። የሚገድለኝ ኦነግ ወይም አልሸባብ ሳይሆን በጉያዬ ያለ ኃይል መሆኑ ስለገባኝ፤ በሌሎች ኃይሎች ተጨማሪ የረድፍ ጥበቃ አድርገን አምቦ ሄድን። አምቦ በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረን።

> "የትግራይ ህዝብም በነበረው ውይይት ከፍተኛ አቀባበል አደረገ። ወጣቱም ለውጥ ፈላጊ ስለነበረ ደጋፊ ሆነ። እናም የሳንድዊቹ ሃሳብ ከመቀሌ በኋላ ገባቸው። ስለዚህ ይህንን ነገር ማስቆም አለብን። በዚህ ከቀጠልን ህዝቡን ይነጥሉብንና አደገኛ ነገር ይፈጠራል፤ ከቁጥጥር ውጪ ይወጣል የሚል ውይይት አደረጉ..."

ከዚያ ስንመለስ ወደ ባህርዳርና ጎንደር እቅድ ስንይዝ የወልቃይት ኮሚቴ፣ የቅማንት ኮሚቴ የሚባሉ ሊገድሉህ እቅድ ይዘዋል፤ እቅዱም በእጃችን ላይ ስላለ አትሄድም ተባልኩ። እዚያ ያለውን ሥራ የአማራ ክልል አመራሮች እንዲሠሩት አድርገን ሄድን። ከሄድን በኋላ ህብረተሰቡን ማነጋገራችን ሳይሆን ከወልቃይት እና ከቅማንት ኮሚቴዎችን ጋር መወያየታችን በእኛና በደህንነት ተቋሙ መካከል ከሚጠበቀው በላይ መካረር ፈጠረ። አለመነጋገር፤ ከፍ ሲልም አለመደዋወል ተጀመረ።[7]

የወልቃይትና የቅማንት ኮሚቴን የሚያናግር ሰው ከኛ ጋር መነጋገር የለበትም የሚል ትንሽ ጠንከር ያለ አቋም ያዙ። ከዚህ በኋላ በሰሜንም፣ በምሥራቅም፣ በምዕራብም፣ በደቡብም በአዲስ አበባ አካባቢም ህዝብን ስላነጋገርንና ስሜቱንም ስለተረዳን ፈጠን ፈጠን ያለ ውሳኔ በመወሰን ከለውጡ የሚጠብቀውን ነገር እያሳየን መሄድ አለብን በሚል እንደምታስታውሱት በየቀኑ በሰበር ዜና እንትና ተፈታ፣ እንደዚህ ሆነ ... እንደዚህ ሆነ ወዘተ... ትላልቅ ውሳኔዎች መወሰን ጀመሩ።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በመቀሌ ጉብኝታቸው በትግሉ ወቅት የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች ሲጎበኙ፤

7 የወልቃይት ኮሚቴ ‹‹የወልቃይት ሕዝብ አማራ ነው፣ በትግራይ ክልል ሊተዳደር አይገባም›› የሚል አቋም የሚያራምዱ አባላትን አሰባስቧል። የቅማንት ኮሚቴ ደግም በአማራ ክልል በቀድሞው የጎንደር ክፍለ ሃገር፤ በአሁኑ ማዕከላዊ ጎንደር ዞን በሚገኙ የተወሰኑ ወረዳዎች የሚኖሩ የቅማንት ማህበረሰቦች የማንነትና የራስ አስተዳደር ጥያቄ ሊመለስ ይገባል የሚል እንቅስቃሴ በሚያስተባብሩ ግለሰቦች ይመራል። የደህንነት ተቋሙ የወልቃይት ኮሚቴ አባላት ላይ ክትትል በማድረግ እንቅስቃሴውን ለመግታት እንዲሁም የቅማንት ኮሚቴን በመደገፍ በአካባቢው አለመረጋጋት እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋል የሚሉ ተደጋጋሚ ክሶች ይቀርቡበት ነበር።

## <<ወይ አንተ፤ ወይ እኛ>> የደህንነት ሹሞቹ ቀይ መስመር

የለውጥ አመራሩ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል። እስረኞች ተፈተዋል ፣ የዴሞክራሲ ምህዳሩ እንዲሰፋ የሚያስችሉ ውሳኔዎች ተላልፈዋል። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እንዲፈቱ ያሳለፈው ውሳኔ ግን ከደህንነት ተቋሙ ከረር ያለ ተቃውሞ አስከትሏል። <<ወይ አንተ፤ ወይ እኛ>> በሚልም የደህንነት ሹሞቹ ቀይ መስመር እንዲያስቀምጡ አስገድዷል ...

እነዚህ ውሳኔዎች እየተወሰኑ ሲሄዱ ሁለት ሦስት ቦታ ችግር ገጠመን። አንደኛው በዚያው ሰሞን የተፈቱ የፖለቲካ እስረኞች ከወጡ ከአራት ከአምስት ቀን በኋላ አዲስ አበባ ላይ አንድ ስብሰባ አድርገው ነበር። ኮከብ የሌለውን ልሙጡን ባንዲራ ይዛችኋል ተብለው ተመልሰው እስር ቤት ገቡ፤ሳምንት አልሞላቸውም ከተፈቱ። አይ ፍቷቸው፤ ይህ ትክክል አይደለም። ባንዲራ ይዛችኋል ብለን ሰው አስረን ለውጥ አናመጣም፤ የሚለው ጉዳይ አጨቃጫቂ ሆነ። ተጨቃጨቅን፤ ነገር ግን ተፈቱ።

ቀጥሎ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ[8] ይፈቱ የሚል ጥያቄ ሲመጣ ከፍተኛ ግጭትና ጦርነት ተፈጠረ። አንዳርጋቸው ጽጌ አገር የሚፈነቅል፤ እንደዚህ ያደረገ ... የሞት ፍርድ ፍርደኛ የሆነ ሰው ... ወዘተ ... <<ሊፈታ አይችልም ! >> የሚል ጠንከር ያለ አተካራ ገጠሙ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማን እንደሆነ አይታወቅም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያዛል፣ የደህንነት ሹሞች አይቻልም ይላሉ። ከህግ ጋር አያይዘው ህገመንግሥት፣ አዋጅ የሚል ነገር ስላነሱ አቃቤ ህግ ከህግ አንጻር ክፍተት እዳይፈጠር የቤት ሥራውን እንዲሠራ ካደረግን በኋላ አንዳርጋቸው ጽጌ ሲፈቱ ግልጽ በሆነ መንገድ ከተራ ክርክርና ጭቅጭቅ ያለፈ “ወይ አንተ፤ ወይ እኛ” የሚል ከረር ያለ ፀብ ውስጥ ገባን።

8 አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በአስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ ተሳታፊ ነበሩ። የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ወድቆ ደርግ ስልጣኑን ሲይዝ ኢህአፓን ተቀላቅለዋል። በግንቦት 2000 ዓ.ም ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋር በመሆን ግንቦት ሰባት ንቅናቄን የመሰረቱ ሲሆን፤ የድርጅቱ ዋና ጸሃፊ ሆነው ተመርጠው ነበር። ሚያዚያ 2001 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት ግንቦት ሰባትን በአሸባሪነት ከፈረጀ በኋላ፤ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በሌሉበት የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸዋል። ሰኔ 2006 ዓ.ም አንዳርጋቸው የግንቦት ሰባትን ሥራ ለማካሄድ ከዱባይ ተነስተው በየመን በኩል ወደ ኤርትራ ሊጓዙ ሲሉ ሰንዓ ላይ በየመን የጸጥታ ኃይሎች ተይዘው ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፈው ተሰጥተዋል፡ ፡ መንግሥት ባደረገላቸው ይቅርታ ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም ከእስር ተለቀዋል።

“አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ይፈቱ የሚል ጥያቄ ሲመጣ ከፍተኛ ግጭትና ጦርነት ተፈጠረ...
እስከዚህ ጊዜ ድረስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማን እንደሆነ አይታወቅም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያዛል፣ የደህንነት ሹሞች አይቻልም ይላሉ። ከህግ ጋር አያይዘው ህገመንግሥት፣ አዋጅ የሚል ነገር ስላነሱ አቃቤ ህግ ከህግ አንጻር ክፍተት እዳይፈጠር የቤት ሥራውን እንዲሠራ ካደረግን በኋላ አንዳርጋቸው ጽጌ ሲፈቱ ግልጽ በሆነ መንገድ ከተራ ክርክርና ጭቅጭቅ ያለፈ “ወይ አንተ፤ ወይ እኛ” የሚል ከረር ያለ ፀብ ውስጥ ገባን...”


ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ እና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፤



## < <ከሀገር የሚበልጥ የለም> > የለውጥ አመራሩ ቀይ መስመር

የደህንነት ሃይሎች የአንዳርጋቸው ጽጌን የመፈታት ጉዳይ ቀይ መስመር አድርገው ቢያስቀምጡም፤ በአቋሙ የጸናው የለውጥ ሃይል ግለሰቡ ከእስር እንዲፈቱ ከማድረግ ባሻገር፤ < <ከሀገር የሚበልጥ የለም ! > > የሚል የራሱን ቀይ መስመር  አበጅቶ፤ የመከላከያና የደህንነት ሹሞቹን የሚመለከት ቁርጠኛ ውሳኔ አሳለፈ ...

ከዚህ በኋላ ይህንን ሁኔታ ይዘን መቀጠል አንችልም። የራሳቸው ወታደር፤ የራሳቸው ሚዲያ፤ የራሳቸው የሚያንቀሳቅሱት ሀብት ያላቸው የደህንነት አመራሮችና ኃይሎች እያሉ አብሮ መቀጠል ስለማይቻል ማንሳት ያስፈልጋል የሚል ውሳኔ ወስነን ማጥናት ጀመርን። ዕርምጃውን መከላከያ ላይ ብቻ እናድርገው ወይስ ደህንነት ላይ ብቻ እናድርገው የሚል ነገር አነሳን። ሁለቱ ላይ ካደረግንስ ምን አደጋ አለው? የሚለውን ማየት ጀመርን።

ይህንን ስናጠና በአንድ ጊዜ የደህንነት ሹምና የመከላከያ ኤታማዦር ሹም አንስተው ለብዙ እልቂት የተዳረጉ የአፍሪካ ሀገራት መኖራቸውን ተረዳን። ታሪክ የሚያሳየው ጉዳይ ስለነበር ያንን ለማስቀረት የሚቻለውን ጥናት ካዘጋጀንና ከተወያየን በኋላ የመጨረሻውን የግድ ማድረግ ያለብን በመንግሥት ውስጥ ያሉ መንግሥታትን ማንሳትና ተቋሞቹ ተቋም ብቻ መሆን አለባቸው የሚል ውሳኔ ነበር።

እዚህ ላይ በግልጽ ሳልጠቅስ የማላልፈው የወቅቱ ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የነበሩት ጄኔራል ሳሞራ የኑስ በንጽጽር መፈንቅለ መንግሥት እንዳይካሄድ ተቃውመው የቆሙ ነበሩ። ለውጡ ከመጣ በኋላም ሰፋፊ ድጋፍና የትብብር መንፈስ ያሳዩ ነበር። ይህ ግልጽ ነው። የሚካድ አውነት አልነበረም።

ነገር ግን ተባባሪም ቢሆኑ ተቋሞቹን ለመቀየር ያለን ፍላጎት ችግር ስላለበት እርሳቸውን አክብረን፣ ሸልመን አመስግነን፣ በጡረታ እንዲገለሉ ማድረግ፤ ሌሎቹ ላይም እንዲሁ ዕርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል በሚል በአንድ ጊዜ የመከላከያ ኤታማዦር ሹሙንና የደህንነት ሹሙን አነሳናቸው። ሁለቱም እኩል ግብረመልስ አልነበራቸውም። በንፅፅር ጄኔራል ሳሞራ በብዙ እጥፍ ይሻላሉ፤ በሥራቸውም፤ ለመተባበር ባላቸው ፍላጎትም። ነገር ግን ተቋማቱ ተቋም እንዲሆኑ የግድ ዕርምጃው ያስፈልግ ነበር።

“በአንድ ጊዜ የመከላከያ ኤታማዦር ሹሙንና የደህንነት ሹሙን አነሳናቸው። ሁለቱም እኩል ግብረመልስ አልነበራቸውም። በንፅፅር ጄኔራል ሳሞራ በብዙ እጥፍ ይሻላሉ፤ በሥራቸውም፤ ለመተባበር ባላቸው ፍላጎትም...”



ጀነራል ሳሞራ የኑስ ከቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ የክብር ሽልማት ሲበረከትላቸው፤

## የቤተሰብ ማህበሩ ገመና

**የለውጥ ሃይሉ የወሰደው እርምጃ በተቃራኒው ጎራ በተሰለፉ ሃይሎች ዙሪያ መፍረክረክ የፈጠረ ነበር። የደህነት ሹሙ በማግስቱ የተቋሙን ንብረት ሰርቀው ሸሹ፤ ይመሩት የነበረው መሥሪያ ቤት ሲፈተሽ ከተቋምነት ይልቅ የቤተሰብ ማህበር ይመስል እንደነበረና ብዙ ያልተነገሩ ገመናዎች እንደተሸከመም የለውጡ ሃይሉ አረጋግጧል ...**

ይህንን ዕርምጃ ከወሰድን በኋላ የነበረው የመካረር ፀባይ ግልጽ መልክ እየያዘ ስለመጣ የደህንነት ሹሙ በተነሱ ማግስት በርካታ ዘመናዊ መሣርያዎች፣ ትጥቆች እና ቁሳቁስ ሰርቀው ወደ መቀሌ ሄዱ።

የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘበው የምፈልገው ነገር ምን ሰርቀው እንደሄዱ እንኳን አናውቅም። ስንት ሰርቀው እንደሄዱም አናውቅም። ምክንያቱም ደህንነት የሚባለው መሥርያ ቤት የቤተሰብ ማህበር እንጂ ተቋም አልነበረም። ምን እንደገባ ምን እንደወጣ፣ ማን እንደገዛ፣ ማን እንደለመነ አይታወቅም።

ሁሉም ዝም፤ ሁሉም ጭጭ ነው፤ መረጃ የለም። እኔ አልሸባብ ይገድለሃል ከተባልኩ ጀምሮ የደህንነት ሹሙ እስከተነሱበት ቀን ድረስ በፖስታ ታሽጎ የሚላክልኝን መረጃ አንድም ቀን አንብቤው አላውቅም። ወረቀት በሚፈጭበት ማሽን ነው የማስገባው። የሚላካልኝ መረጃ ምን እንደሆነ ስለማውቀው ማለት ነው።

ተቋሙ የደህንነት ሹሙ ይህንን ይዞ ሄዷል ብሎ ሪፖርት ለማድረግ እንኳን የማይችል ተቋም ነበር፤ አያውቅም። በመጨረሻ በተቀናጀ መንገድ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ሁላችሁም እንደምታስታውሱት የግድያ ሙከራ ተደረገ። የግድያ ሙከራው ሲደረግ ፖሊሱም፣ መከላከያውም ደህንነቱም ባለበት ነው። በዚያ ደረጃ በቅርበት የተደረገው ሙከራ ሃሳቦቻቸውን ለማሳካት ሊሆን ስለሚችል ተቋማቱን እንፈትሽ ብለን ስንፈትሽ ነው ከደህንነት መሥሪያ ቤቱ ውስጥ የሄደ መሣርያ፣ የሄደ ቦምብ እንዳለ ያወቅነው። እስከዚያ ጊዜ ድረስ መረጃ አልነበረንም።

በዚያን ጊዜ ቢሆንም ጥርት ብሎ እንደዚህ አይነት መሣርያ ይህንን ያህል ቁጥር ያለው የሚል አይታወቅም። ከእስራኤል የተገዛ በቀንም በማታም የሚሠሩ በሌዘር የሚደገፉ፣ ድምፅ የሌላቸው ለግድያ የሚውሉ ትጥቆች መኖራቸውን እናውቃለን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጋር ይህ ግለሰብ የሀገርና የመንግሥት ሀብት ሰርቆ ሄዷል፣ ቢያንስ ሀብቱን አስመልሱ የሚል ሁለት ሦስት ወር የፈጀ ጭቅጭቅ ነበር።




“ይህንን ዕርምጃ ከወሰድን በኋላ የነበረው የመካረር ፀባይ ግልጽ መልክ እየያዘ ስለመጣ የደህንነት ሹሙ በተነሱ ማግስት በርካታ ዘመናዊ መሣርያዎች፣ ትጥቆች እና ቁሳቁስ ሰርቀው ወደ መቀሌ ሄዱ...

የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘበው የምፈልገው ነገር ምን ሰርቀው እንደሄዱ እንኳን አናውቅም። ስንት ሰርቀው እንደሄዱም አናውቅም። ምክንያቱም ደህንነት የሚባለው መሥርያ ቤት የቤተሰብ ማህበር እንጂ ተቋም አልነበረም...

እስከዛሬ ያላነሳኋቸውን ጉዳዮች አሁን የማነሳው  አመራሮች ትምህርት እንዲወስዱ፤ ከዚህ አንጻር መታነጽ ስላለባቸው የታለፈበትንም መንገድ የኢትዮጵያ ህዝብ የማወቅ መብት ስላለው ነው...”

ይህ መሥርያ ቤት እንዳልኳችሁ ወታደር አለው፤ ሚዲያ አለው። አባይ ሚዲያ የሚባል የደህንነት ሹሙ ያቋቋመው የግል ሚዲያው ነው - በመንግሥት ሀብት። ቤተመንግሥት አስፈላጊ ቦታ የራሱ ወታደሮች አሉት። ውጭ ሀገር ሄጄ እመጣለሁ እንዳይባል አየሩ አይታመንም፤ ኤርፖርቱ አይታመንም። በእነዚህ ኃይሎች ነው የሚጠበቀው።

ሰው የራሱ ነፃነት ሳይኖረው ማሰብም አይችልም፤ መከላከልም አይችልም። ይህንን የተከበረው ምክር ቤት መገንዘብ አለበት። ቀለል አድርጎ ማየት የለበትም። እስከዛሬ ያላነሳኋቸውን ጉዳዮች አሁን የማነሳው  አመራሮች ትምህርት እንዲወስዱ፤ ከዚህ አንጻር መታነጽ ስላለባቸው የታለፈበትንም መንገድ የኢትዮጵያ ህዝብ የማወቅ መብት ስላለው ነው።

## በኢትዮጵያ ልክ ያልተገነባው ተቋም

የደህንነት ተቋማት ሙያዊ ተልዕኮ የሚወጡ
ሳይሆኑ የቤተሰብ ማህበር መሆናቸውን ያረጋገጠው
የለውጥ ሃይሉ፤ የመከላከያ ሠራዊቱን አደረጃጀት
ሲፈትሽ ደግሞ ከአንድ ብሄር የተወጣጡ አመራሮች
የሚበዙበት  የብሄር ብሄረሰቦች የተመጣጠነ
ውክልና የራቀው በኢትዮጵያ ልክ ያልተገነባ መሆኑን
በጥናት ደርሶበታል ...

በኢትዮጵያ የደህንነትና የመከላከያ መዋቅር የነበረውን ችግር ለመፍታት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፣ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ፌዴራል ፖሊስ፣ መከላከያ ሚኒስቴርና የፋይናንስ ደህንነት ማዕከልን ያካተተ ሴክዩሪቲ ሴክተር ሪፎርም (SSR /security sector reform) ለመስራት ሙከራ ተጀመረ።

ሙከራ ስናደርግ የደህንነት ተቋማት የሚባሉት የሉም ማለት ይቻላል። የግለሰብ፣ የቤተሰብ ማህበሮች ናቸው። እውቀት የሌላቸው፤ ብቃት የሌላቸው፤ በትውውቅ፤ በዝምድና የተሰገሰጉ ሰዎች ያሉበት ተቋም ነው። ስለዚህ ፈርሶ መሠራት የሚጠይቅ ተቋም ነው።

መከላከያን ግን እንደዚያ ማድረግ የራሱ ችግር ስለነበረው መከላከያችን ምን እንደሚመስል በዳታ፣ በእውቀት እንመልከት ብለን ስንፈትሽ የመጣው ማስረጃ መከላከያን ትናንት ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ ብቻ ሳይሆን በሚቀጥሉት አምስትና አስር ዓመታት መቀየር የሚያስቸግር እንደሆነ ተረዳን። ለምሳሌ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ አራት ኮከብ ያላቸው ጄኔራሎች ( ሙሉ ጄኔራሎች) ከትግራይ ክልል 60 ከመቶ ሲሆኑ፣ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች በሙሉ 40 በመቶ ነበር።

አንድ ደረጃ ዝቅ ብለን ሌተናል ጄኔራል የሚባለውን ስንመለከት፤ ከትግራይ አካባቢ ያሉት 50 ከመቶ ናቸው። አንድ ደረጃ ዝቅ ብለን ሜጀር ጄኔራል የሚባለውን ስንመለከት ደግሞ 45 ከመቶ ከአንድ አካባቢ ናቸው። ብርጋዲየር ጄኔራል 40 ከመቶ ከአንድ አካባቢ ናቸው።

ኮሎኔል 58 ከመቶ፤ ሌተናል ኮሎኔል 66 ከመቶ እንዲሁም ሻለቃ 53 በመቶ ከአንድ አካባቢ ነው። ይህ ማለት ጄኔራልን ብንቀይር እንኳ፤ ቢያንስ አንድ ሻለቃ ኮሎኔል ለመሆን አስር ዓመት ስለሚወስድበት በሚቀጥሉት አስር ዓመታት መከላከያው ውስጥ ሚዛኑን የጠበቀ ወታደር መፍጠር አይቻልም።

ከላይ ጀምሮ እስከ ሻለቃ ድረስ በአማካይ ሲታይ 55 ከመቶ የሚሆነው ከትግራይ አካባቢ ነው። ጄኔራል አካባቢ በቆይታ ነው ይባል ይሆናል። ግን አንድ ሰው ሻለቃ እና ኮሎኔል ለመሆን ያለፉት 20 ዓመታት በወታደራዊ ሙያ በቂ ናቸው። የተሠራው ሥራ አሁንም በሚቀጥለው ማሰብ እንዳይቻልና አቅም ያለው አመራር ከአንድ አካባቢ እንዲወጣ ታስቦ የተደረገ ነው። ይህ ለትግራይም ሆነ ለኢትዮጵያም

> በኢትዮጵያ የደህንነትና የመከላከያ መዋቅር የነበረውን ችግር ለመፍታት ሙከራ ስናደርግ የደህንነት ተቋማት የሚባሉት የሉም ማለት ይቻላል። የግለሰብ፣ የቤተሰብ ማህበሮች ናቸው። እውቀት የሌላቸው፤ ብቃት የሌላቸው፤ በትውውቅ፤ በዝምድና የተሰገሰጉ ሰዎች ያሉበት ተቋም ነው። ስለዚህ ፈርሶ መሠራት የሚጠይቅ ተቋም ነው ...
> መከላከያን ግን እንደዚያ ማድረግ የራሱ ችግር ስለነበረው መከላከያችን ምን እንደሚመስል በዳታ፣ በእውቀት እንመልከት ብለን ስንፈትሽ የመጣው ማስረጃ መከላከያን ትናንት ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ ብቻ ሳይሆን በሚቀጥሉት አምስትና አስር ዓመታት መቀየር የሚያስቸግር እንደሆነ ተረዳን..."

አይጠቅምም። ትግራይ በሚገባውና ባለው ህዝብ ልክ መሳተፍና ሀገር መጠበቅ አለበት። አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያም ሆኑ ቤንሻንጉል ከሚገባቸው በላይ መያዝ የለባቸውም። እንዲህ ከሆነ ዞሮ ዞሮ ይህ አሁን የመጣውን ችግር ያስከትላል።

አሁን ያነሳሁት ማዕረግን በተመለከተ ነው፤ ስልጣንን አይመለከትም። ስልጣን ስንመለከት በመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት በዋና መምሪያ እና መምሪያ ደረጃ ያሉት 80 ከመቶ ከትግራይ ክልል ነው። ቅድም ያየነው 55 ከመቶ ነው፤ እሱ ጥሩ ነው። ማዕረግ የለበሰ ኦሮሞ እና አማራ ወይም ሌሎች ቢኖሩም በትክክለኛ ስንመለከተው አመራር የሚሰጠው 80 ከመቶ ከትግራይ ክልል ነው። ይህ ምን ማለት ነው የሚገዛውን ትጥቅ፣ ስልጠናውንና ግንኙነቱን ሁሉን ያውቃል። በአንድ አካባቢ ተይዟል ማለት ነው...

አንድ ደረጃ ዝቅ ብለን ስንመለከት እዞች አሉ። ኢትዮጵያ የነበራት እዝ አዛዥ እና ምክትል አዛዥ መቶ በመቶ ከትግራይ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ምሥራቅና ምዕራብ እዝ አማራ፣ ኦሮሞ ተብሎ ሎጂስቲክስ ወይንም የሰው ኃይል ይመደብ ይሆናል። ሰሜን ዕዝ ግን አዛዥ፣ ምክትል አዛዥ፣ ሎጂስቲክና አስተዳደር በሙሉ አራቱም ኮሚቴ ከትግራይ ክልል ናቸው። በሰሜን እዝ ይህ ለምን ሆነ ? የሚለውን በኋላ እመጣበታለሁ...

አንድ ደረጃ ከዕዝ  ዝቅ ብለን ክፍለ ጦር ስናይ፤ ክፍለ ጦሮች ሁለት መልክ አላቸው - ሜካናይዝድ እና እግረኛ። የኢትዮጵያ የሜካናይዝድ ክፍለ ጦሮች አዛዥ መቶ በመቶ ከትግራይ ናቸው። በእግረኛ ክፍለጦር 80 ከመቶ ከትግራይ ናቸው። ቅድም ያየነው ማዕረግ የሚያሳይ አሃዝ አለ። ሰዎች ማዕረግ አላቸው እንጂ ዕዝ አይመሩም፤ ክፍለጦር አይመሩም ማለት ነው። ዝም ብሎ ስንት ጀነራል አል ሲባል ለስም ብቻ ነው።

ከዚህም ደግሞ አንድ ደረጃ ዝቅ ብለን ስንመለከት በሜካናይዝድ ብርጌዶች 85 ከመቶ ከትግራይ ነው። እግረኛ ብርጌድ 80 ከመቶ ከትግራይ ክልል ነው። ከብርጌድ እስከ መከላከያ ሚኒስቴር ያልተመጣጠነ ውክልና ነበር ማለት ነው።

ምናልባት በስልጠና የሚቀየር ከሆነ ብለን ስንመለከት የመከላከያ ስልጠና ተቋማት 85 ከመቶ በትግራይ ልጆች ይመራል። ስለዚህ አዲስ ሰው ተመልምሎ ቢገባም ችግር ነው። ይህን የተዛባ ነገር የትግራይ ህዝብም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ አለበት።  መደገም የለበትም። ሁሉም በሚገባው ልክ ነው ድርሻውን መውሰድ ያለበት። ሁሉንም የሚመስልና የሚወክል የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን መገንባት ይገባል። በእርግጥ ሙያዊ መሆኑ መጠበቅ አለበት። እንደ ተወካዮች ምክር ቤት ከሁሉም ብሄር ማሟላት ሳይሆን ከሁሉም ብሄር አሰልጥኖ አብቅቶ ማምጣት ይገባል። ይህ ወደን ሳይሆን  በህገመንግስት የተቀመጠ ስለሆነ ኢትዮጵያን የሚመስል መከላከያ መገንባት ግድ  ይላል።

እስኪ ስልጣን ላይ ያለውን እንተወውና አጠቃላይ መከላከያ እንዴት ተገነባ ብለን የስልጠና ዶክመንት የምናውቀውንና የማናውቀውን አስመጥተን ስንመከለት፤ መከላከያ የተገነባበት ቀዩ መፅሐፍ መቶ በመቶ ከህገሪቱ ህገ መንግሥት በድፍረት በተቃራኒ የቆመ ነው። መፅሐፉ  አንተ

> የተሠራው ሥራ አሁንም በሚቀጥለው ማሰብ እንዳይቻልና አቅም ያለው አመራር ከአንድ አካባቢ እንዲወጣ ታስቦ የተደረገ ነው። ይህ ለትግራይም ሆነ ለኢትዮጵያም አይጠቅምም። ትግራይ  በሚገባውና ባለው ህዝብ ልክ መሳተፍና ሀገር መጠበቅ አለበት…”

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዘብ ነህ፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከተነካ ተዋጋ፤አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከሌለ ያንተ የምትላት ኢትዮጵያ የለችም ይላል። ስለዚህ በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኘው ሌላውም ብሄር  ቁጥር አነሰም በዛ ትርጉም የለውም፤ የተገነባው በዚያ እሳቤ ነው። ሰነዱ መከላከያውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጠባቂ አድርጎት ያስቀምጣል። ይህ ተቋም ለፓርቲ ያለው ውግንና የኢትዮጵያን መፃኢ ዕድል ከመወሰን አኳያ አደገኛ ነው የሚል ግልጽ ሃሳብ ነበር።

ለምሳሌ ሲዳማ ክልል ወላይታዎች ሲጨፈጨፉ በወቅቱ እዚያ አካባቢ የነበረው አዛዥ አሁን የመገናኛን መስመር ቆራርጦ ወታደር ያስጨረሰው ግለሰብ ነው።[9] መረጃ አለን ግን ማስረጃ የለንም። ወላይታ ሲዳማ ገደለኝ ይላል። ወላይታና ሲዳማ አይገዳደሉም፤ አብረው የኖሩ ናቸው። እዚያ አካባቢ ያለው አመራር ትስስር አለው፣ ገንዘብ አለው፤ ሚሽን ይሰጠዋል ያጋድላል ደግሞም ሠላም ያስከብራል።

9 የመገናኛን መስመር ቆራርጦ ወታደር ያስጨረሰው የተባለው ግለሰብ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባል የሆነው ሜጀር ጀነራል ገብረመድህን ፈቃዱ  (ወዲ ነጮ)  ነው። ግለሰቡ ከጁንታው ህወሃት ጋር በመመሳጠር ጥቅምት  24 ቀን 2013 ምሽት ላይ በትግራይ ክልል የሚገኘው የሰሜን ዕዝ ከማዕከል ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ እንዲቋረጥና  የዕዙ የመገናኛ ሥርዓት ለጁንታው የህዋሃት ወንበዴ ቡድን እንዲመቻች በማድረግ በሀገር ክህደት  ወንጀል ተጠርጥሮ ተይዟል።  ከለውጡ በፊት የማዘዣ ጣቢያውን በሃዋሳ ያደረገው የአጋዚ ኮማንዶና ልዩ ኃይሎች አዛዥ የነበረ ሲሆን፤  ከህወሓት ጋር ባለው ትስስር የሲዳማና የወላይታ ግጭት እንዲባባስ ሲሰራ እንደነበር መረጃ ተገኝቷል።

“ይህን የተዛባ ነገር የትግራይ ህዝብም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ አለበት። መደገም የለበትም። ሁሉም በሚገባው ልክ ነው ድርሻውን መውሰድ ያለበት። ሁሉንም የሚመስልና የሚወክል የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን መገንባት ይገባል። በእርግጥ ሙያዊ መሆኑ መጠበቅ አለበት...”





## የመከላከያ አዛዦች ስብጥር ከለውጡ በፊት

* ሙሉ ጀነራሎች (ባለ አራት ኮኮብ ጀነራሎች) ከትግራይ ክልል 60 በመቶ ከሌሎች ክልሎች 40 በመቶ፤
* ሌተናል ጀኔራል ከትግራይ ክልል 50 በመቶ ከሌሎች ክልሎች 50 በመቶ፤
* ሜጀር ጀነራል ከትግራይ ክልል 45 በመቶ ከሌሎች ክልሎች 55 በመቶ፤
* ብርጋዲየር ጀነራል ከትግራይ ክልል 40 በመቶ ከሌሎች ክልሎች 60 በመቶ
* ሙሉ ኮሎኔል ከትግራይ ክልል 58 በመቶ ከሌሎች ክልሎች 42 በመቶ፤
* ሌተናል ኮሎኔል ከትግራይ ክልል 66 ከመቶ ከሌሎች ክልሎች 34 በመቶ፤
* ሻለቃ ከትግራይ ክልል 53 በመቶ ከሌሎች ክልሎች 47 በመቶ፤
* በአጠቃላይ በኢፌዴሪ መከላከያ ከሙሉ ጀነራልነት እስከ ሻለቃ ማዕረግ 55 በመቶ ከትግራይ ክልል ፤
* በመከላከያ ዋና መሥሪያ ቤት በዋና መምሪያ እና መምሪያ ሃላፊነት ደረጃ ከተቀመጡት አመራሮች መካከል 80 ከመቶ የሚሆኑት ከትግራይ ክልል፤
* የመከላከያ ስልጠና ተቋማት አመራሮች 85 ከመቶ ከትግራይ ክልል፤
* በኢፌደሪ መከላከያ ሥር ያሉ እዞች አዛዥ እና ምክትል አዛዥ 100 በመቶ ከትግራይ ክልል፤
* ከእዝ አንድ ደረጃ ዝቅ ሲባል የእግረኛ ክፍለ ጦሮች አመራሮች ጦር 80 በመቶ እንዲሁም የሜካናይዝድ ክፍለጦር አዛዦች 100 በመቶ ከትግራይ ክልል፤
* ከእዝ አንድ ደረጃ ዝቅ ሲባል በሜካናይዝድ ብርጌዶች 85 ከመቶ እንዲሁም በእግረኛ ብርጌድ 80 ከመቶ አዛዦች ከትግራይ ክልል ነበሩ።

## የመከላከያ አዛዦች ስብጥር ከለውጡ በኋላ

* ከጀነራል እስከ ሻለቃ 55 ከመቶ ከትግራይ ክልል የነበረው የአመራሮች ስብርጥ ወደ 26 ከመቶ ዝቅ ተደርጓል፤
* የእዝ አዛዦች 100 በመቶ ከትግራይ ክልል የነበረው የአመራሮች ስብርጥ ወደ 25 ከመቶ ዝቅ ተደርጓል፤
* ከእዝ አንድ ደረጃ ዝቅ ሲባል የእግረኛ ክፍለ ጦር አዛዦች 80 በመቶ ከትግራይ ክልል የነበረው ስብርጥ ወደ 40 በመቶ እንዲሁም የሜካናይዝድ ክፍለ ጦር አዛዦች 100 በመቶ ከትግራይ ክልል የነበረው ስብርጥ ወደ 50 በመቶ ዝቅ ተደርጓል ፤
* ከክፍለ ጦር አንድ ደረጃ ዝቅ ሲባል የእግረኛ ብርጌድ አዛዦች 80 በመቶ ከትግራይ ክልል የነበረው ስብጥር ወደ 40 በመቶ እንዲሁም የሜካናይዝድ ብርጌድ አዛዦች 85 በመቶ ከትግራይ የነበረው ስብጥር ወደ 44 በመቶ ዝቅ ተደርጓል ፤
* የመከላከያ ስልጠና ተቋማት አመራሮች 85 ከመቶ ከትግራይ ክልል የነበረው ስብጥር ወደ ወደ 25 በመቶ ዝቅ ተደርጓል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የመከላከያ እና ደህንነት አካሄድና ስሪት ምንድን ነው ያስከተለው ? ብለን ስናይ፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል ዋና ዋና የሚባሉ ሕይወት የቀጠፉ፣ ንብረት ያወደሙና የመንግሥትን ትኩረት የሳቡ 113 ግጭቶች ነበሩ፤ የአሁኑን ሳይጨምር (በሰሜን እዝ ላይ የተፈጸመው ጥቃት)። ይህ ማለት በየሳምንቱ የጦርነት ድግስ ነበር። የመንግሥት ሥራ እዚህም እዚያም ማልቀስና መቅበር፤ ከአንደኛው ለቅሶ ሳይነሳ ወደ ሌላኛው ለቅሶ መሄድ ነበር። ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስራ እንዳይሰራ በተቀናጀ መንገድ ውስጥ ያለውን ኃይል በመጠቀም በየቦታው ሽብር ይፈጠር ነበር።

## ከ113 ግጭቶች በስተጀርባ ...

**የመከላከያና የደህንነት መሥሪያ ቤቱ አወቃቀር ምን አስከተለ? የሚለው ቁልፍ ጥያቄ ይሆናል። የህወሓት ጁንታ መዋቅሮቹን የሀገርና የህዝብ ሰላምና ደህንነት እንዲያረጋግጡ ከማድረግ ይልቅ ሥልጣኑን ለማራዘም እንዲሁም ለሚያቀነባብራቸው የጥፋት ሴራዎች ማስፈጸሚያ መሣሪያ አድርጓቸው ነበር ...**

113 ግጭት ሲፈጠር በሁሉም ክልሎች ግጭትና መጋደል አለ። ትግራይ ክልል ግን የለም። እነርሱም ትንሽ አያፍሩም እኛ ብቻ ነን ሰላም ይላሉ። አንዳንድ የውጭ ሰዎችም ሳይቀሩ ሰላም እኮ ያለው ትግራይ ክልል ብቻ ነው ይላሉ። አዎ! እዛ ሰላም አለ፤ ሰላም የሚያደፈርስ ከዚህ ቀን ከሌሊት የሚሠራ የለም። እዚህ ያለውን የሚያደፈርሱት እነርሱ ስለሆኑ።

ሁሌም ቁስል እየቆሰቆሱ ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ አባሉት። አሠራሩ ግን ተራ አልነበረም። ፋይናንስ፣ ሥልጠና፣ ስምሪት እና ሚዲያ አለ። ሚዲያዎች ቀድመው ይዘጋጁና አንድ ነገር ሲፈጠር ኦሮሞ አማራን ጨረሰ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ አማራን እንዲህ አደረገ ... ብለው ቀድመው የሚናገሩት እነርሱ ናቸው - በሶሻል በሚዲያ እና በመደበኛ ሚዲያውም። ሌላው ሞኛ ሞኝ ይከተላቸዋል። ያንን ተከትሎ እርስ በእርስ ይባላል። ግጭቱ ቶሎ እንዳይረጋጋ የብሄርና የሃይማኖት ግጭት እንዲፈጠር በከፍተኛ ደረጃ ሠርተዋል።

ተሳክቶላቸዋል ወይ? ከተባለ ሰዎች ተገድለዋል፣ ንብረት ወድሟል፣ ንጹሐን ዜጎች ምንም የማያውቁ ለፍተው ደክመው የሚያድሩ ሞተዋል ስኬት ከሆነ። ግን አልተሳካላቸውም። ይህ ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው ኬንያ ሲሰደድ በራሱ መመዘኛ ኬንያ ያለው ምግብ ይስማማኛል፤ ሰው ይቀበለኛል ብሎ በማመን ነው። ግን አንድ የጎጃም ሰው አምቦ ከተማ ሄጄ እኖራለሁ ሲል፤ የአምቦ ሰው ወንድሜ ነው ይቀበለኛል ቢርበኝ ያበላኛል፤ ብታመም ያስታምመኛል የሚል እምነት ይዞ ነው የሄደው፤ ካላመነማ ሰው ወዴትም አይሄድም። ወገኔ ካላለ ሰው አይሄድም። ወገኔ ብሎ የሄደውን ሰው፣ የተዋለደውንና ስንት መከራ አብሮ ያሳለፈውን ህዝብ እርስ በእርስ እንዲጠራጠር፣ እንዳይተማመንና በዓይነ ቁራኛ እንዲተያይ በከፍተኛ ደረጃ ተሠርቷል።



ይህን በዳታ ለማስደገፍ ባለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል በኦሮሚያ ውስጥ 37 ግጭቶች ነበሩ። በጉሊሶ፣ ሐረርጌ፣ ጉጂ፣ ወለጋ፣ ጭናቅሰን፣ ባሌ፣ ሻሸመኔና ሌሎችም ቦታዎች። በዚህ 37 ግጭት ውስጥ ሌላው የተጎዳ ብሄር እንዳለ ሆኖ በከፍተኛ ደረጃ ኦሮሞም ተጎድቷል። አባት፣ እናት ወንድምና እህት ሞቷል፣ ቤት ፈርሷል።

ይህ ኃይል ኦሮሚያ ክልልን የብጥብጥ ማዕከል እያደረገ ኦሮሞን ከሌሎች ወንድሞች ጋር እያቃረነ፤ እስላም ከክርስቲያን ጋር እያቃረነ፤ ለኦሮሞ እቆረቆራለሁ ይላል። በ37 ግጭት ውስጥ ብዙ የኦሮሞ እናት ያለ ባል እና ልጅ ቀርታለች። ኦሮሞ ካለማንነቱና ባህሉ አምነው፣ ወደውና አብረውት ከሚኖሩት ጎረቤቶቹ ጋር እንዲባላ ተደርጓል። ይህ ለማንኛውም ብሄር ሆነ ለኢትዮጵያም ኪሳራ ነው። የሚጠቀም ኃይል ካለ ይህ ኃይል ብቻ ነው።

“ሁሌም ቁስል እየቆሰቆሱ ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ አባሉት። አሠራሩ ግን ተራ አልነበረም። ፋይናንስ፣ ሥልጠና፣ ስምሪት እና ሚዲያ አለ ...

በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች አርባ ምናምን ዓመት እንዋጋ እያሉ የትግራይን ወጣት እያስጨረሱ አንዳቸውም ሳይሞቱ ሀገረሰላም ገቡ - ሌሎችን አስጨርሰው። እነርሱ አይሞቱም። እንዋጋ ማለት ‹‹እኔን ጠብቀኝ፤ እኔ አልሞትም፣ አንተ ሙትልኝ›› ማለታቸው ነው። እና የማን ሞኝ ነው ከዓመት ዓመት ለእነርሱ ነፍስ እየገበረ እነርሱን የሚያኖረው...”

በአማራ ክልል ባለፉት ሁለት ዓመታት ተከል 23 ግጭቶች ተከስተዋል። በቅማንት፤ በአጣዬ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልል በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር፣ ሞጣ ደግሞ በሃይማኖት። እያንዳንዱ ክልል በውስጡ ካሉ ብሄሮች፣ አጎራባች ክልሎችና አልፎ አልፎ አጎራባች ሀገራት ጋር እንዲባላ ተደርጓል።

በአማራ ክልል ብዙ ሰዎች ሞተዋል። ለምሳሌ ቅማንትን የወሰድን እንደሆነ ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት በአማራ ክልል ውስጥ የጎንደር አካባቢ ከሁሉም ብሄሮች የመዋለድና ከሁሉም ብሄሮች የመኖር ከፍተኛ ልምምድ ያለው ነው። በርካታ ኤርትራውያን፣ ኦሮሞዎች፣ ትግሬዎች፣ ቅማንቶች ብዙ ህዝቦች የተጋቡበትና የተዋለዱበት ሀገርም፣ ከተማም ነው።

ቅማንትና አማራ ተብሎ መለየት በማያስችል ደረጃ እያንዳንዱ ቤተሰብ የተጋባ ነው። በአማራ ክልል ያሉ አመራሮች ቁጥራቸው የማይናቅ ሚስቶቻቸው ቅማንት ናቸው። ልጆቻቸው ከአማራ አባትና ቅማንት እናት የተወለዱ ናቸው። አንድ ቋንቋ፣ ባህልና ወግ ያላቸው አንድ ቤተሰብና አንድ ህዝብ ናቸው። ይህን ግጭት አያውቁትም። ግን ይህ ግጭት ስፖንሰር ተደርጎ በአማራ ክልል ሰላም እንዳይኖር ሰዎች በብሄር እንዲጋደሉ ተሠርቷል፤ በዚህም ብዙ ሰው ተጎድቷል።

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል 15 ግጭቶች ነበሩ። መተከል፣ አሶሳ አካባቢ ከኦሮሚያም አማራም መፈናቀል ጋር የተያያዘ እና የዳንጉር አካባቢም ግጭት ነበር። ላለፉት ሁለት ዓመታት አርሶ አደር ወደ ማሳው ወጥቶ ተገደለ የሚለውን ዜና መስማት የተለመደ ሆኗል።

አዲስ አበባ ላይ 14 ግጭቶች ነበሩ። ከግጭቶቹ ሁሉ የሚገርመኝ ግን የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን የሚመለከት ነው። ከሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ጎን ለጎን በ10 ምድብ (category) ተከፍሎ እንዲገደሉ የታሰቡ ሰዎች ነበሩ። ብልጽግና ውስጥ ያሉ ኃላፊዎች፤ ከብልጽግና ውጪ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲ ኃላፊዎች፤ እንዲሁም ስማቸው የሚታወቅ ሰዎች በመግደል ሽብር ለማፋፋም ታቅዶ ነበር።

ለዚህም መጀመሪያ ከኦሮሚያ አካባቢ የተወሰኑ ሰዎችን መግደል፤ ከዛ ከአማራ አካባቢ ኃላፊዎችን መግደል፤ ግጭቱን የኦሮሞ እና የአማራ የማስመሰል ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። ሆኖም ሃጫሉን አጥተናል፤ ሌሎቹ እንዳይሳኩ በጣም ብዙ ሥራ ተሠርቷል። የሃጫሉ በተለየ የሚገርመኝ፣ ከጥቂት ዓመት በፊት ሃጫሉ ሁንዴሳ እንዴት በኦሮሚያ ቲቪ ታየ ብለው ቁም ስቅላችንን ያሳዩን ሰዎች፤ በግምገማ መከራ ያሳዩን ሰዎች፤ <<የኦሮሞ ታጋይ ሃጫሉ ተገደለ>> ብለው በቴሌቪዥናቸው ማስተላለፋቸው ነው።[10]

በጋምቤላ ሰባት ግጭት ነበር። በጋምቤላ ክልል ብቻ ሳይሆን በስደተኞች ካምፕ ጭምር ግጭት ነበር። በደቡብ የጌዲኦ፤ ጉራ ፈርዳ፣ ኮንሶ፣ ሚዛን ቴፒ በሌሎቹም አካባቢዎች ግጭቶች ነበሩ። በተለይ የጌዲኦ በጣም የሚገርመው በጌዲኦ እና በጉጂ መካከል በሁሉም መመዘኛ አንድ ቤተሰብ የሚባል ህዝብ ነው። አባልተውታል፤ ከዚህም አፈናቅለዋል ከዛም አፈናቅለዋል። ደቡብ ላይ በጣም ብዙ ሰዎች ተጎድተዋል። ህዝቤ ወገኔ ብለው የሄዱም ሌሎች ብሄሮች እንዲሁ ተጎድተዋል።

ጅግጅጋ እንዲሁም አፋር ላይ ከኢሳ ጋር በተያያዘና በሌላም የተነሳ ሦስት ግጭት ነበር፤ ድሬዳዋ ላይ ሦስት ግጭት ነበር፤ ሐረሪ ሁለት ግጭት ነበር፤ ሲዳማ ላይ ሁለት ግጭት ነበር። ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን በዚህ መልክ ትግራይ ላይ አንድም ግጭት አልነበረም። ሽራሮ የሚገኙ ኩናማዎች እና ትግራዮች አይጋጩም፤ በሃዋሳ ግን ወላይታ እና ሲዳማ ይጋጫል። ኢሮብ አካባቢ ያሉ የኢሮብ ህዝቦች ከትግራይ ጋር አይጋጩም፤ መጋጨትም የለባቸውም። ሌላ ቦታ ግን በእያንዳንዱ ክልል ብቻ ሳይሆን፤ ክልል ከክልል ግጭት እንዲፈጠር ሠርተዋል። ለምሳሌ፣ እንደ ክልል አማራ ቤኒሻንጉል ጉምዝ ያዋስነዋል፣ ተጋጭቷል፤ ኦሮሚያ ያዋስነዋል፣ ተጋጭቷል፤ አፋር ያዋስነዋል፣ ተጋጭቷል፤ ትግራይ ያዋስነዋል፣ አልተጋጨም። አፋር ኦሮሚያ ያዋስነዋል፣ ተጋጭቷል፤ ሶማሌ ያዋስነዋል፣ ተጋጭቷል፤ አማራ ያዋስነዋል፣ ተጋጭቷል፤ ትግራይ ያዋስነዋል፣ አልተጋጨም።

10 ዘርዓይ አስገዶም የህወሓት አባልና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ዳይሬክተር ነበሩ። የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ‹‹ሃጫሉ የኦሮሞ ወጣት ተነስ አራት ኪሎ ግባ የሚል ዘፈን ሲዘፍን እንዴት በኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (OBN) በቀጥታ ይተላለፋል›› በማለት የድርጅታቸውን አቋም አንጸባርቀው ነበር። አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ምሽት ከተገደለ በኋላ ግን በጁንታው ይተዳደሩ የነበሩት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሙሉ የይስሙላ ተቆርቋሪነት ከማንጸባረቅ አልፈው የብሄር ግጭት የሚቀሰቅስ ዘገባ ሲያተላልፉ ነበር።

"ባለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል ዋና ዋና የሚባሉ ሕይወት የቀጠፉ፣ ንብረት ያወደሙና የመንግሥትን ትኩረት የሳቡ 113 ግጭቶች ነበሩ፤ ይህ ማለት በየሳምንቱ የጦርነት ድግስ ነበር። የመንግሥት ሥራ እዚህም እዚያም ማልቀስና መቅበር፤ ከአንደኛው ለቅሶ ሳይነሳ ወደ ሌላኛው ለቅሶ መሄድ ነበር..."

"አፋር እና ሶማሌ መካከል ግጭት ይፈጠራል፤ ይህ ሲፈጠር የሁለቱን ክልል አመራሮች ጠርተን ግምገማ ተቀመጥን። ግምገማ ስንቀመጥ፣ የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ አወል አርባ፣ አንድ የሚገርም ሃሳብ አነሱ። አፋርና ሶማሌ ድሮም ይጣላል፤ አዲስ አይደለም። ግን የአሁኑ የአፋር እና የሶማሌ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ ወይ? ፈትሹ እስኪ አለኝ... እንዴት? አልኩኝ፤ አንደኛ፣ በዚህ ግጭት ሴት ይሞታል፤ ሆኖም ሶማሌ ሴት አይገድልም፤ አፋር ሴት አይገድልም። ምክንያቱም እንጋጨለን እንጂ ሴት አንገድልም፣ እናም ይሄ አዲስ ባህሪ ነው። ሁለተኛ፣ አፋር እና ሶማሌ ቀን ቀን ይጋጫል እንጂ ማታ ማታ አይዋጋም፤ የማታ ውጊያ አያውቅም፤ የአሁኑ ግን የማታ ውጊያ አለው። ሦስተኛ፣ አፋር እና ሶማሌ በግልጽ እየተናገረ እየሄደ ይዋጋል እንጂ በመሸፈኛ አፉን ሸፍኖ እና ራሱን ደብቆ አይዋጋም፣ የአሁኖቹኮ ፊታቸው የተደበቀ ነው አሉ..."

አፋር ላይ የገጠመን ትንሽ ለመረጃ ስለሚጠቅም እሱን ላንሳላችሁ። አፋር እና ሶማሌ መካከል ግጭት ይፈጠራል፤ ይህ ሲፈጠር የሁለቱን ክልል አመራሮች ጠርተን ግምገማ ተቀመጥን። ግምገማ ስንቀመጥ፣ የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ አወል አርባ፣ አንድ የሚገርም ሃሳብ አነሱ። አፋርና ሶማሌ ድሮም ይጣላል፤ አዲስ አይደለም። ግን የአሁኑ የአፋር እና የሶማሌ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ ወይ? ፈትሹ እስኪ አለኝ።

እንዴት? አልኩኝ፤ አንደኛ፣ በዚህ ግጭት ሴት ይሞታል፤ ሆኖም ሶማሌ ሴት አይገድልም፤ አፋር ሴት አይገድልም። ምክንያቱም እንጋጫለን እንጂ ሴት አንገድልም፣ እናም ይሄ አዲስ ባህሪ ነው። ሁለተኛ፣ አፋር እና ሶማሌ ቀን ቀን ይጋጫል እንጂ ማታ ማታ አይዋጋም፤ የማታ ውጊያ አያውቅም፤ የአሁኑ ግን የማታ ውጊያ አለው። ሦስተኛ፣ አፋር እና ሶማሌ በግልጽ እየተናገረ እየሄደ ይዋጋል እንጂ በመሸፈኛ አፉን ሸፍኖ እና ራሱን ደብቆ አይዋጋም፣ የአሁኖቹኮ ፊታቸው የተደበቀ ነው አሉ።

ይሄን ካሉ በኋላ፤ መከላከያን ኃይልህን አውጣ፣ የሶማሌን ክልል ኃይልህን አውጣ፣ የአፋርን ክልል ኃይልህን አውጣ፣ ፌዴራል ፖሊስም አውጣ አልን እና፤ ስፔሻል ፎርስ ነው ከዚህ የሚሄደው (ሪፐብሊካን)፣ መከላከያንም ካየህ ምታ፣ ፖሊስም ካየህ ምታ፣ የአፋርም የሶማሌ ክልልንም ካየህ ምታ፣ አንድ ሰው እንዳይጠጋ ሁላችሁም ውጡ ብለን ስፔሻል ፎርስ ላክን። እንኳን ግጭት፤ እንኳን ግድያ፤ ድምፅ የለም።

መከላከያን ከሁሉም ጋ አውጥተን አንችለውም። መከላከያ ባለበት አካባቢ የሚፈጠረው ግጭት ጠባሳው ከፍተኛ ነው። በዚህ ውስጥ በጣም የሚያሳዝነው ሱዳን ጋ የገጠመን ሁኔታ ነው። የሱዳን ህዝብ በተደጋጋሚ እንዳልኩት ለዚህ ሀገር ትልቅ ውለታ የዋለ ህዝብ ነው። አሁንም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከፍተኛ ድጋፍ ያደረገ ህዝብ ነው። ነገር ግን ለሱዳንም የተወሰኑ ሰዎች ሄደው መከላከያ ማለት እኮ እኛ ነን። እኛ አንወጋህም። መሬት የምትወስድበት ጊዜ አሁን ነው፤ መግባት ትችላለህ፤ ብለው የቆሰቆሱት ከእኛ ነው።

> ይህ ኃይል ኦሮሚያ ክልልን የብጥብጥ ማዕከል እያደረገ ኦሮሞን ከሌሎች ወንድሞች ጋር እያቃረነ፤ እስላም ከክርስቲያን ጋር እያቃረነ፤ ለኦሮሞ እቆረቆራለሁ ይላል። በ37 ግጭት ውስጥ ብዙ የኦሮሞ እናት ያለ ባል እና ልጅ ቀርታለች። ኦሮሞ ካለማንነቱና ባህሉ አምነው፣ ወደውና አብረውት ከሚኖሩት ጎረቤቶቹ ጋር እንዲባላ ተደርጓል። ይህ ለማንኛውም ብሄር ሆነ ለኢትዮጵያም ኪሳራ ነው። የሚጠቀም ኃይል ካለ ይህ ኃይል ብቻ ነው...
> የትግራይ ህዝብ ደግሞ ከሌሎች ጋር እንዳይስማማ፣ እንዳይገናኝ የመከበብ ስሜት እንዲሰማው አደረጉ፣ አማራ ሊወጋህ ነው፤ ኤርትራ ሊወጋህ ነው፤ ፌዴራል መንግሥት ሊወጋህ ነው፤ ብለው የከበባና የጦርነት ስጋት ውስጥ አስገቡት። ልወረር ነው ብሎ እንዲያስብ አድርገው በከፍተኛ ሁኔታ ሠሩበት። ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ በኢተገማች ስሜት ውስጥ እንዲገባ አደረጉ...”

የሱዳን መንግሥት ግን እኔ በኃይል ሳይሆን በህጋዊ መንገድ ነው ይገባኛል የምለውን ነገር የምመልሰው ብሎ መረጃውን ለኛ ሰጥቶናል። እዚህ የሚያጋጩን አልበቃ ሲል እዚያም ተወጣ። ሶማሊያ ብትሄዱ በተመሳሳይ ይኸኛው መንግሥት ሞቃዲሾን ይደግፋል፤ እንትናን ይደግፋል፤ እያሉ ሶማሊያዎችን ከኛ ጋር ለማባላት ፤ደቡብ ሱዳንም ብትሄዱ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ያበቃ አይደለም። የኮማንዶ ወታደሮች ቤተመንግሥት ታጥቀው የመጡበትን ታስታውሳላችሁ። 200 የሚሆን የታጠቀ ኃይል ነው የመጣው። ከመጣበት ቤተመንግሥት እስከወረረበት ጊዜ ድረስ ምንም ዓይነት መረጃ አልነበረም። ህዝብ ማጋጨት፣ በተደበቀ መንገድ የግድያ ሙከራ ማድረግ፣ ክልልና ክልል ማጋጨት በቂ ስላልነበረ እዚሁ ግቢ ድረስ መጡ፤ እሱም ከሸፈ። ህገወጥ የመሣርያ ዝውውር፤ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር በስፋት ተካሄደ።

ይህ ማስፈራራት፣ ይህ ማጋደል ከህዝብ፣ ከብሄር፣ ከእምነት ወጣና ብልጽግና ውስጥ ገባ። በየጊዜው ግድያ፣ በየጊዜው ግጭት በሚሆንበት ሰዓት ለውጡን በህይወታቸው ተወራርደው ያመጡ ግለሰቦች ጭምር አይ በቃ እነዚህን ሰዎች አንችላቸውም ተስማምተን ካልቀጠልን አሉ። የሚሉንን ካልሰማን ይህ ጉዳይ አይሳካም አሉ። ሰው እንዴት ከሰይጣን ጋር ሊስማማ ይችላል? ምክንያቱም ልስማማ ብትልም አትስማማም። ለይተህ ቆርጠህ ካልሠራህ በስተቀር።

ውስጣችን ያለ ኃይልም በከፍተኛ ደረጃ ተፍረከረከ። ተቃዋሚውም ብዙ ሃሳብ ውስጥ ገባ፤ ህዝብም ተስፋ ቆረጠ። ይህ መንግሥት እንደው በቃ... በቃ... ተባለ፤ እንደምታውቁት ነው። አሁን ምን አሉ፤ የድሮው ይሻልሃል። ወደ ድሮው ብትመለስ ይሻልሃል፤ ጠንካራ መንግሥት ያስፈልግሃል። በትክክለኛ ቋንቋ አፋኝ መንግሥት ያስፈልግሃል ብለው በግልጽ ቅስቀሳ ጀመሩ።

የትግራይ ህዝብ ደግሞ ከሌሎች ጋር እንዳይስማማ፣ እንዳይገናኝ የመከበብ ስሜት እንዲሰማው አደረጉ፣ አማራ ሊወጋህ ነው፤ ኤርትራ ሊወጋህ ነው፤ ፌዴራል መንግሥት ሊወጋህ ነው፤ ብለው የከበባና የጦርነት ስጋት ውስጥ አስገቡት። ልወረር ነው ብሎ እንዲያስብ አድርገው በከፍተኛ ሁኔታ ሠሩበት። ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ በኢተገማች ስሜት ውስጥ እንዲገባ አደረጉ።

ወጥቶ መግባት የማያስተማምን፤ ቤተሰብ በሰላም ወጥቶ መግባት የማይተማመንበት፤ በስጋት የተሞላ ሀገር እንዲሆን አደረጉት። መንግሥት በለውጥ ቅልበሳ በየሳምንት በሚፈጠር አጀንዳ እንዲወጠር ሞከሩ። ለውጡ ወደፊት መጓዝ እንዳይችል ሰፊ ሥራ ሠሩ።

# ከጺስ ቀን ...

## የዛሬን ድል ትናንት የሠራው የመከላከያ ሪፎርም

በደህንነትና በመከላከያ ተቋማት የነበረው ስር የሰደደ ችግር መፍትሄ ካልተበጀለት ሀገር በተቀደደላት የጥፋት ቦይ እየፈሰሰች ወደማትወጣው አዘቅት እንደምትወርድ ግልጽ ነበር። አዲስ የተስፋ ቀን እንዲወለድ በትዕቢት የደነደነው አጥፊው ቡድን የሚያውቃቸው፤ ቢያውቃቸውም የናቃቸው እንዲሁም የማያውቃቸውም  ሪፎርሞች መተግበር ጀመሩ...



የሴኪዩሪቲ ሴክተር ሪፎርም (የደህንነት ተቋማት ሪፎርም) በተለይም በመከላከያ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ፤ ማስተካከያ ካልተደረገ በየቦታው ያለው ግጭት እንደሚቀጥል ታምኖበት ስራው ቀጠለ። ሪፎርም ያስፈልጋል ብለን በሦስት ከፈልነው። የላይኛው አመራር፣ መካከለኛው አመራር፣ የታችኛው አመራር።



የላይኛው አመራር ቅድም ያነሳሁላችሁ ከጀነራል እስከ ሻለቃ የነበረውን 55 ከመቶ ወደ 26 ከመቶ ዝቅ አደረግነው። የህግ ማስከበር ዘመቻው ከመጀመሩ በፊት 26 ከመቶ ከፍተኛ አመራሮች ከትግራይ ናቸው። ቁጥሩ ከፍ ያለ ቢሆንም የትግራይ ክልል ተወላጆች በመከላከያ ውስጥ በቂ ድርሻ ማግኘት እንዳለባቸው ፅኑ እምነት አለን። በሱ ላይ ጥያቄ የለንም። ይስተካከል ነው እንጂ ትግራይ የሚባል መከላከያ ውስጥ አይኑር የሚል አቋም አልነበረንም።

እዞች ላይ መቶ  የነበረውን 25 አደረግን። በተለይ የደቡብ ህዝቦች እንዲገነዘቡት የሚያስፈልገው ለውጡ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ለደቡብ ጄኔራሎች የመጨረሻው ጣራ ሜጀር ጄኔራል ነበር። ሌተናል ጄኔራል የሚል ማዕረግ ደቡብ ክልል ያገኘው ከለውጡ በኋላ ነው። ከደቡብ 25፣ ከኦሮሞ 25፣ ከአማራ 25፣ ከትግራይ 25 አድርገን የሚያጋጥመን ነገር ካለ ሰው በብቃት እንዲወዳደር ያንን አካባቢ እኩል አደረግነው።



ይህ የሆነው መሆን ስለሚችል፤ ብቃት ያላቸው ሰዎች ስላሉ ነው። የብቃት ችግር አይደለም ጉዳዩ። ብቃት እንዳላቸው አሁን አሳይተዋል። ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር ሙያ የሚጠይቅ ስለሆነ መቶ በመቶ የነበረውን፤ አሁን 50 በመቶ ትግራይ እንዲሆን ተደርጓል። ከ50 በላይ መሄድ አልቻልንም። በቀላሉ መቀያየር የሚቻል ስላልነበረ። እግረኛ ክፍል ጦር 80 በመቶ የነበረው 40፣ ሜካናይዝድ ብርጌድ 85 የነበረው 44፣ እግረኛ ብርጌድ 80 የነበረው 40፤ 50 በመቶ ገደማ ስታፍ ወደ 25 ዝቅ አድርገን የሥልጠና ተቋማት ላይ ወደ 25 ዝቅ አድርገን ላይኛውን ሠራነው።

እዝ አዛዥ አንዱ ደቡብ፣ አንዱ ኦሮሞ፣ አንዱ አማራ፣ አንዱ ትግራይ ለማድረግ ተሞከረ። በከፍተኛ አመራር ደረጃ ያሉ የቀነስናቸው ሰዎች አንድም ሰው የጡረታው ጊዜ ሳይደርስ ያወጣነው የለም። ድሮ እነ አበባው ታደሰ፣ እነ ባጫ ደበሌ ገና በሚሠሩበት አፍላ እድሜያቸው ሌተናል ጀነራል ደረጃ ስለደረሱ ውጡ ተባሉ። እኛ ግን ያንን ስህተት






አልደገምንም። ጡረታ የደረሰበት ሰው ብቻ ህግ ተከትሎ ይፈጸም የትናንትናውን መድገም የለብንም የሚል አቋም ስለነበረ በጡረታ የሚወጣውን እየቀነስን አብዛኛው ተራዝሞለት ስለነበር ለማስተካከል ሞከርን።

ሁለተኛው ማስተካከያ ግን መካከለኛ አመራሩን የሚመለከት ነው። ከመካከለኛ አመራሩ ጋር በተያያዘ  ሻለቃና ሌተናል ኮሎኔል ላይ የደረሱ አባላትን በቀላሉ ማመጣጠን ባለመቻሉ ችግር ፈጥሮ ነበር።  ጄኔራል የፖለቲካ ሹመት ነው። አንድ ኮሎኔል በስድስት ወሩ ወይም በአመት ጄኔራል ተብሎ ሊሾም ይችላል። አንድ ሻለቃ ግን የተለየ ጀብድ ካልሠራ በዓመት ሌተናል ኮሎኔል መሆን አይችልም። ጊዜ አለው፤ ዝም ብሎ ማራገፍ አይቻልም። ዝም ብሎ መሾምም አይቻልም። ዝም ብለን ካራገፍን ኢትዮጵያ ትናንትናም የተጎዳችው መከላከያ ፈርሶ ነው፤ አሁንም ማፍረስ ይሆናል። እንገንባ ብለን እናፈርሳለን የሚለው ስጋት ፈጥሮ ነበር።

ከመካከለኛው አመራር ጋር በተያያዘ የገጠመን ሌላው ችግር ለውጥ ስናደርግ ከዚህ የወጣው ኃይል ጡረታ ወጥቶ ፎቁን እዚህ አስቀምጦ እዚያ (ወደ ትግራይ ክልል በመሄድ) ሌላ መከላከያ መገንባት ጀመረ። እና መካከለኛውን በስፋት ብናወጣው እዚያ ሄዶ መገንባቱ አይቀርም። እዚህ ባዶ ስለሚቀር መካከለኛውን ትንሽ እንያዘው አልን። አናራግፈው፤ ብናራግፈውም ይሄኛው ይዳከማል። ሌላ ይጠናከራል በሚል፤ ሲወጣ ሌላ ቦታ ስለሚያጠናክር። ይሄን ደግሞ ማዘጋጀት ጊዜ ያስፈልጋል።

ሦስተኛው ታችኛውን አመራር የሚመለከት ስራ ነበር። ታችኛው አመራር ላይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል በመንግሥት የተሠጡ ሥልጠናዎች እና ውይይቶች ባለፉት አስር፤ አስራ አምስት ዓመታት ከመከላከያ ጋር ተደርጎ አያውቅም። መከላከያ ይሄን በደንብ ያውቀዋል። ስትራቴጂውን መቀየር ኢትዮጵያዊ ወታደር እንዲሆን በህገ መንግሥትና በኢትየጵያ ህዝብ ብቻ የሚመካ እንዲሆን የብልጽግና ወታደር እንዳይሆን፤ የብልጽግና ወታደር ከሆነ አደገኛ ስለሆነ። በግልጽ ሥልጠና ሰጥተን፤ ወታደሩ የደመወዝ ጥያቄ ነበረው፤ የዩኒፎርም ጥያቄ ነበረው። የተቀደደ ዩኒፎርም ይለብሳል። ያን ለማሟላትና ታች ያለውን ኃይል ለማዘጋጀት ሙከራ አደረግን። ይሄ ሙከራ በሁለት ዓመት የሚጠናቀቅ አልነበረም። ጊዜ ይፈልግ ነበር። ጊዜ ስለሚፈልግ በፈለግነው ልክ መሄድ አልቻልንም።

# ምስጢራዊ ሪፎርም

በመከላከያ ተቋሙ ላይ ከሚደረገው ሪፎርም ጋር በተያያዘ በየትኛውም መድረክ የሚደረጉ ውይይቶችና የሚተላለፉ ውሳኔዎች በአንድ ሰዓት ውስጥ ከህወሓት ጁንታ ስብስብ ጆሮ መድረሱ፤ የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ውስጥ የሚያስገባ ሁኔታ በመፍጠሩ፤ የኢትዮጵያን ህልውናና አንድነት ለመጠበቅ መከላከያን በሚመለከት በሦስት ተከፍሎ ከተተገበረው ሪፎርም ውጪ ምስጢራዊ ሪፎርም ተዘጋጀ።

አንደኛው ሪፐብሊካን ጋርድ መመስረት ነው። ስፔሻል ፎርስ ማዘጋጀት አለብን፤ ኦፕሬሽ የሚሠራ ፣ ችግር ካጋጠመን ቢያንስ የሚገታ በሚል፤ከፍተኛ ብቃት ያላቸው፣ በርካታ ሀገራት የሰለጠኑ ስፔሻል ፎርሶች ለማዘጋጀት ሞከርን።

ሁለተኛው አየር ሃይል ነው። አየርሃይል ሞቶ ነበር - እሱን ማቅናት። በብዙ ምክንያት ቴክኖሎጂ ስለሚያስፈልግ መዘጋጀት አለብን በሚል በተለይ የድሮን ወይም <<አንማን ኤር ቪዬክል (ዩኤቪ)>> የሚባሉትን ለመታጠቅ ሰፊ ሥራ ሠራን። ግን እነሱ በሚያውቋቸው ቦታዎች በማስቀመጥ ቁጥራቸውን፣ ዓይነታቸውን እንዲያዩ አልፈቀድንላቸውም። ይህ ሪፎርም ምስጢራዊ ነበር። ስፔሻል ፎርስ ሰልፍ ሲያሳይ ማየት ጀምረዋል። ነገር ግን ያለንን ብቃትና ቁጥሩን አያውቁትም።

የአየር ሃይልን ሪፎርም በግርድፉ ያውቃሉ፤ሙሉውን አያውቁም። ታስታውሱ ከሆነ ከውጊያው ጥቂት ቀናት በፊት አየርሃይልን ስናስጎበኝ ነበር። አንዳዶቻችሁ እንኳን በልባችሁ ወይም በፌስቡክ አየርሃይል ለምንድነው የሚታየው ብላችኋል። ያ ሆን ብለን ነው። አየርሃይሉ ያው የምታውቁት ነው፣ አዲስ ነገር የለም ብለን ነው ያሳየናቸው። የተዘጋጀነውን ነገር ጠላት እንዲያውቅ ስለማንፈልግ።

እና ያን አየ ርሃይል ሲያዩ ደስ አላቸው፤ ዝግጅት የለም ብለው ተደፋፈሩ ማለት ነው። የተዘጋጀውን ድሮን በሚመለከት ብዙ ወሬዎች ይወራሉ። ያው በግልጽ ሄዳችሁ ማየት ትችላላችሁ። ለዓመታት ሲታሰብበትና ሲገነባ የቆየ አቅም ነው። ነገር ግን የድሮኑን በሚመለከት የጁንታውን ኃይል እኔ አልደበኳቸውም። በግልፅ ከጥቂት ወራት በፊት የሚሊሺያ ውግያ አንዋጋም። ዘመናዊ ውግያ እንዋጋለን። እንደዚህ ዓይነት ቴክሎጂ አለን፤ እባካችሁ ውግያ አታስቡ ብያቸዋለሁ። ግን አላመኑም፤ ምክንያቱም በነሱ ኔትወርክ ውስጥ አይታይም። ስለዚህ አልተቀበሉትም።





> የኢትዮጵያን ህልውናና አንድነት ለመጠበቅ መከላከያን በሚመለከት በሦስት ተከፍሎ ከተተገበረው ሪፎርም ውጪ ምስጢራዊ ሪፎርም ተዘጋጀ...

## የሚስጢራዊ ሪፎርም በረከት

ይህ ኃይል ከመቀሌ ሸሽቶ ሃገረ ሰላም አካባቢ እየተሰባሰበ ነው ያለው። እንዲሰሙኝ የምፈልገው ከምሽቱ አራት ሰዓት እና አምስት ሰዓት አካባቢ በሲቹዌሽን ሩም[11] ውስጥ አቢ አዲና ሃገረ ሰላም መካከል የነበረውን መተረማመስ ስናይ ነበር ያደርነው።

የጠላትን እንቅስቃሴ በቀጥታ ነው የምናየው። ማታ አላጠቃናቸውም። ምክንያቱም በሸሸት ውስጥ ሚስቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውን ይዘው ሄደዋል። ከሰሜን እዝ ያፈኗቸውንም ወታደሮች ይዘው ሄደዋል። ህዝብ ውስጥም አቢ አዲና ሃገረሰላም አካባቢ በጣም መተረማመስ ነበር። አናጠቃም ብለን ዓይተን ነው የተውነው። ይሰማሉ፤ እነሱ ስለሚያውቁት ነው። ግን አይቀጥልም ይሄ።

> 99 ከመቶ ኢላማ መትተናል፤ 99 ከመቶ ‹‹ኮላተራል ዳሜጅ›› አልነበረውም። የሚያጠራጥር ሲሆን አንተኩስም፤ ለምሳሌ ማታ አንተኩስም፤ ሕፃናት ቢሞቱስ ብለን፤ የኛ ስለሆኑ። በስፔሻል ፎርሱና በኤርፎርሱ ላይ የተፈጠረው ብቃት ጠላት የሚገምተው አልነበረም...”



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ እና ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች የህግ ማስከበር ዘመቻውን ሂደት በተመለከተ ከሲቺዌሽን ሩም ክትትል ሲያደርጉ፤

11 ሲቺዌሽን ሩም (situation room) ኦፕሬሽኖችን ለመምራት የተዘጋጀ በቴክኖሎጂ የተደራጀ ክፍል ነው። የጁንታው አባላት ከመቀሌ ሸሽተው አቢ አዲና ሃገረ ሰላም አካባቢ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከሲቺዌሽን ሩም ክትትል ይደረግበት ነበር።





> አንድ ሮኬት ወደ ትግራይ ክልል አልተኮስንም። ማን ላይ ነው ሮኬት የምንተኩሰው፤ ሮኬት ማለት በኪሎሜትሮች ሳታየው ሄዶ የሚወድቅ ነገር ነው። ማን ላይ ምን እንደሚያመጣ አይታወቅም። የእኛ ፓይለቶች ሄደው ሲቪሎች አሉ ካሉ ከእነ ቦምባቸው ነው የሚመለሱት፤ መወሰን ስለሚችሉ። በድሮን እያየን ስለምንወስን አናደርገውም። በሮኬት ግን አደገኛ ነው። የተሻለ ቁጥር ቢኖረንም ሀገራችን ስለሆነ አላደረግነውም። እኛ ጁንታ አይደለንም። በኃላፊነት ነው የምንሠራው... በየትም ዓለም ውጊያ የማንም ሀገር ወታደር ቢሆን ከዚህ የበለጠ ብቃት ማሳየት አይችልም። በጣም ዲሲፕሊንድ ጀግና ወታደር ነው ያለን...”



ከሲቪል ሰዎች ጋር በተያያዘ የተነሳው ጥያቄ እጅግ ከሚገርመኝ የኢትዮጵያ አየር ኃይልና የመከላከያው ብቃት አጠቃላይ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ብቃት በተለይ ድሮንን በሚመለከት የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ የምፈልገው ነገር አለ። አንድ ሚግ ወደጠላት ቀጠና ሲሄድ ታርጌት ተሰጥቶት፣ ሰዓት ተሰጥቶት፣ ከሄደ በኋላ ሙሉ ኃላፊነቱ የካፒቴኑ ነው። ራሱ ወስዶ ያጠቃና ይመለሳል። ድሮን እንደዚያ አይደለም። ድሮን እያንዳንዱ ኢላማ ከታየ በኋላ ፓይለቱ ለዘመቻ መኮንን ጥያቄ አቅርቦለት በእያንዳንዱ ኢላማ ተፈርሞ ነው። ከፈለገ የተከበረው ምክር ቤት ማየት ይችላል፤ በተኮስነው ሚሳይል ወይም ጥይት ልክ ፊርማ አለ፤ ለእያንዳንዱ ኢላማ ኃላፊነት ይወሰዳል።

99 ከመቶ ኢላማ መትተናል፤ 99 ከመቶ <<ኮላተራል ዳሜጅ>> አልነበረውም። የሚያጠራጥር ሲሆን አንተኩስም፤ ለምሳሌ ማታ አንተኩስም፤ ሕፃናት ቢሞቱስ ብለን፤ የኛ ስለሆኑ። በስፔሻል ፎርሱና በኤርፎርሱ ላይ የተፈጠረው ብቃት ጠላት የሚገምተው አልነበረም። ድሮንን የሚያስቡት ለተኩስ ብቻ ነው። እኛ ግን ድሮንን የምንጠቀመው 90 በመቶ ለማየት ነው። እንቅስቃሴውን ለማየት። ቀንም ማታም እናያቸዋለን።

ከሲቪል ሰዎች አደጋ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል። በሦስት ሳምንት ውስጥ ሁመራ፣ አዲ ጎሹ ፣ ዳንሻ፣ ሽራሮ፣ አዲ ሃገራይ፤ አዲ ኋላ፣ አዲ ነብሪ፣ አዲ ዳሮ፣ ሽሬ፣ ሰለክላካ፣ አክሱም፣ አድዋ፣አዲግራት፣ህዳጋ ህሙስ፣ ዛላምበሳ፣ መቀሌ - አንዲት ከተማ አንድ ሰው አልገደለም መከላከያ። በየትም ዓለም ውጊያ የማንም ሀገር ወታደር ቢሆን ከዚህ የበለጠ ብቃት ማሳየት አይችልም። በጣም ዲሲፕሊንድ ጀግና ወታደር ነው ያለን። መቀሌ ልታፈርሱ ነው ያልተባለ ዘመቻ የለም፤ መቀሌ እኮ የኛ ነው፡፡ በኛ ሀብት የተገነባውን እንዴት እናፈርሰዋለን? በመቀሌ ኦፕሬሽን አንድ ሰው አደጋ አልደረሰበትም። <<ስፔሻል ሰርጀሪ>> ነው የሰራው።



ነገር ግን ጥያቄዎች ይነሳሉ። ለምን ልዩ ሃይል ብቻ፣ ለምን አየር ኃይል ብቻ፣ ለምን ሜካናይዝድ አልሠራችሁም የሚል ጥያቄ ይነሳል። ምክንያቱም ሰው መጠየቅ አይቸገርም፤ መሥራት ነው የሚቸገረው። ሜካናይዝድ መሥራት ያልተቻልበት ምክንያት ብር ይፈልጋል። አንድ ታንክ ስንት እንደሆነ ታውቁታላችሁ። ያን አሁን ባለንበት ሁኔታ መፈፀም ያስቸግራል። ነገር ግን ይኼ ጁንታው ከመከላከያ ሰርቆ የሚጠቀምበት ሮኬት እጥፍ ቁጥር የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር አለው።

እኛ እጥፍ አቅም እንዳለን እነሱ አያውቁም። ነገር ግን አንድ ሮኬት ወደ ትግራይ ክልል አልተኮስንም። ማን ላይ ነው ሮኬት የምንተኩሰው፤ ሮኬት ማለት በኪሎሜትሮች ሳታየው ሄዶ የሚወድቅ ነገር ነው። ማን ላይ ምን እንደሚያመጣ አይታወቅም። የእኛ ፓይለቶች ሄደው ሲቪሎች አሉ ካሉ ከእነ ቦምባቸው ነው የሚመለሱት፤ መወሰን ስለሚችሉ። በድሮን እያየን ስለምንወስን አናደርገውም። በሮኬት ግን አደገኛ ነው። የተሻለ ቁጥር ቢኖረንም ሀገራችን ስለሆነ አላደረግነውም። እኛ ጁንታ አይደለንም። በኃላፊነት ነው የምንሠራው።

## የጎደለን ...



መላው የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ የምፈልገው ሌላው ጉዳይ ብዙዎቻችን በፌስቡክ ነው የምንዋጋው። ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል መከላከያን ትንሽ ከፍ እናድርገው ብለን ሰፋፊ ምልመላዎች ለማከናወን ሞክረን ነበር። ሌሎቹን ክልሎች ሳይጨምር ከትላልቆቹ ኦሮሚያና አማራ አንድ ሺ ሰው ማግኘት ምጥ ነበር። ሰው ወታደር መሆን አይፈልግም፤ ግን ሀገርህን አትከላከልም፣ ቅድሚያ ዕርምጃ አትወስድም ይላል፣ ይህ ለፌስቡክ እንጂ ለተግባር አይሆንም።

ለመመልመል ፍላጎት አልነበረም። አንድ ሰው፣ አንድ ሙሉ የሆነ ወጣት ወታደር መሆን ሙሉ ሰው ያደርጋል። በብዙ ሀገራት 18 ዓመት የሞላቸው ሰዎች ስድስት ወር፣ አንድ ዓመት ግዳጅ ፈጽመው ነው ወደሥራ የሚገቡት፤ በኛ ሀገር ይህ የለም። እንዴት መቶ ሚልየን ሰው ባለበት ሀገር ውትድርና ስትመለምል አምስት ሺ አስር ሺ ሰው ማግኘት ፈተና ይሆናል?

ይህንን የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያስብበት ይገባል፤አደገኛ ነው። ወታደር ማለት እኮ አምስት ቀን ምግብና መጠጥ ሲከለክሉት እሞታለሁ እንጂ ሀገሬን አልክድም የሚል ወኔ ያለው ማለት እኮ ነው። ይህንን ሰው እንዴት ይጠላል። ወታደር ማለት ሳይከፈለው ቤት ተከራይቶ ሚስት ማግባት የሚያስችል ህይወት ሳይኖረው ከአንድ የቀን ሠራተኛ ደመወዝ ያነሰ እየተከፈለው ህይወቱን በነፃ የሚገብር እኮ ነው። ለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ዝግጅቱ እናሳ ነበር። አሁን ማወቅ አለበት። ማረም አለበት። እንዲሁ የሚገነባ ነገር የለም። ወደፊት ጠላት ይመጣል፤ ትከላከላላችሁ፣ ፍቃደኛ ከሆናችሁና ከተሳተፋችሁ። በዚያ መንገድ ብቻ ነው ሀገር መከላከል የሚቻለው።

ሌላው ዳያስፖራ ነው። ዳያስፖራ እንደሚታወቀው ሀገሩን ይወዳል፤ የሆነ ነገር ሲፈጠር ይጮሃል፣ ይበሳጫል፤ ሰልፍ ይወጣል፤ ይታወቃል። ነገር ግን ዳያስፖራ ይህንን የጁንታ ኃይል በከፍተኛ ደረጃ በፋይናንስ ሲያስታጥቀው ነበር። በተደጋጋሚ እባካችሁ አንድ ብር ለማትረፍ፤ ሁለት ብር ለማትረፍ ህገወጥ በሆነ መንገድ አትመንዝሩ፣ ስንል የነበረው ከመንግሥት በላይ ይህ ኃይል የውጭ ምንዛሪ ያገኝ ነበር። ዳያስፖራው አንድ ብር ለማትረፍ ብሎ ወንድሙ የሚገደልበትን ጥይት እና የጥፋት መሣሪያ ያስታጥቃል። ዳያስፖራውም መንቃት አለበት።

አውቃለሁ በህገወጥ መንገድ ገንዘብ ሲመጣ ትርፍ ይኖረዋል። ነገር ግን ያ ትርፍ የራስን ወንድም ደም የሚደፋ፣ የሚመጥ ሊሆን ይችላል። በህገወጥ መንገድ መመንዘር ወንጀለኞችን እያሳበጠ ንፁሐን ዜጎችን የሚጎዳ ስለሆነ ዳያስፖራው ከዚህ አንጻር እርምት ማድረግ አለበት።



በብዙ ሀገራት 18 ዓመት የሞላቸው ሰዎች ስድስት ወር፣ አንድ ዓመት ግዳጅ ፈጽመው ነው ወደሥራ የሚገቡት፤ በኛ ሀገር ይህ የለም። እንዴት መቶ ሚልየን ሰው ባለበት ሀገር ውትድርና ስትመለምል አምስት ሺ አስር ሺ ሰው ማግኘት ፈተና ይሆናል?
ይህንን የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያስብበት ይገባል፤አደገኛ ነው። ወታደር ማለት እኮ አምስት ቀን ምግብና መጠጥ ሲከለክሉት እሞታለሁ እንጂ ሀገሬን አልክድም የሚል ወኔ ያለው ማለት እኮ ነው። ይህንን ሰው እንዴት ይጠላል...”

## ፖለቲካዊ ሪፎርም ለፖለቲካዊ ሽፍጥ

**በመከላከያና በደህንነት ዘርፉ የነበረው በዘመን ሂደት የደነደነ ችግር፤ ችግሩን ለመፍታት የተሄደበት መንገድ በስፋት ተነስቷል። የለውጥ ሃይሉ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በሌሎችም መስኮች የነበሩትን ጉድለቶች ለመፍታት ያካሄዳቸውም የሪፎርም ስራዎችም በጠቅላይ ሚኒስትሩ አንደበት ተብራርተዋል...**

ብልጽግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

በጸጥታ ተቋማት ሪፎርሙ (ኤስ ኤስ አር) ምንም ያህል የተሠራ ቢሆንም ምንም ያህል ያደገ ቢሆንም በሌሎች ዘርፎች ሪፎርም ካልሠራን በስተቀረ ኢትዮጵያ ውስጥ የተሟላና የምናስበውን ሰላምና ብልጽግና ልናመጣ አንችልም።

አንደኛው ፖለቲካል ሪፎርም ነው። ወታደሩን ተዉትና ፖለቲካ ውስጥ ኢ.ህአዴግ ከፈረሰ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች የሚባል መርዘኛ አስተሳሰብ አለ። ኢ.ህአዴግ የሚባል ትናንትና የተፈጠረ ፓርቲ ለስንት ሺ ዓመት የነበረችን ሀገር እሱ ህልውና ላይ እንድትመሰረት አድርጎ ማሰብና መሥራት በጣም አደገኛ ነገር ነው። ፓርቲው እሳቤው እንደዚያ ነበር። እኛ ከሌለን ሀገር የለችም የሚል ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ወደ ፓርቲው ሪፎርም ስንገባ ብልጽግና ሲፈጠር ህወሓት ለቀቀ የሚሉ ሰዎች አሉ። ስህተት ነው። ብልጽግና ሳይፈጠር ወደ ሃዋሳ ጉባኤ ልንሄድ ስንል የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አጀንዳ ይዞ ተወያይቷል። ሃዋሳ አንሄድም፣ ጉባኤ አንካፈልም ብሎ። በውስጥ ከለቀቁ (resign) ካደረጉ ቆይተዋል። እኛ መረጃው አለን። የመጡት ግዴለም አሁን ከምንወጣ ውስጥ ሆነን እናምሳቸው ብለው ነው። መረጃ እናገኛለን፤ ሃሳባቸውንም እናውቃለን። ውስጥ ሆነን እያመስን የሚፈልጉትን እንዳያሳኩ ማድረግ ይሻላል ከምንወጣ ብለው በድምፅ ወስነው ወደ ሃዋሳ መጡ።

ሃዋሳ ከመጡ በኋላ የነበረው የኢ.ህአዴግ መድረክ የጭቅጭቅ፤ የንዝንዝ መድረክ ነው ያደረጉት። ለምሳሌ የአልጀርስ ስምምነት እንቀበል፤ ኤርትራ የተወሰነላትን መሬት ትውሰድ፣ በሰላም እንጨርስ የሚለውን የኢ.ህአዴግ ሥራ አስፈጻሚና እነዚህ ነባር አመራች ጭምር ባሉበት

“ኢህአዴግ ከፈረሰ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች የሚባል መርዘኛ አስተሳሰብ አለ። ኢህአዴግ የሚባል ትናንትና የተፈጠረ ፓርቲ ለስንት ሺ ዓመት የነበረችን ሀገር እሱ ህልውና ላይ እንድትመሰረት አድርጎ ማሰብና መሥራት በጣም አደገኛ ነገር ነው። ፓርቲው እሳቤው እንደዚያ ነበር። እኛ ከሌለን ሀገር የለችም የሚል ነው...”

በሙሉ ድምፅ ነው የተወሰነው። እንዲወሰን አንዱ አስረጂ የነበረው የደህንነት ሹሙ ነበር። ፓርላማም ቀርቧል፤ ታውቃላችሁ። ይህ ኃይል ግን የተወሰነው ውሳኔ እንዳይፈፀም ሁለት ዓመት ገደማ አንቆ ይዞታል።

በሃዋሳው ጉባኤ የነበረው የቡድኑ አሰላለፉ ሦስት ነበር። ስብሰባውን የጭቅጭቅ መድረክ ለማድረግ የተመደቡ ቡድኖች ናቸው። አንደኛው አሰላለፍ ገና ስብሰባው ሲጀመር ዝም ብሎ የሚሳደብና የሚያራክስ ነበር። ሁለተኛው ቡድን እነሱን የሚቃወምና ደጋፊ የሚመስል ነው። ሦስተኛው ደግሞ አስታራቂ ሽማግሌ የሚመስል ኃይል አለ። አንተም ተው፣ አንተም ተው፣ እንደዚያ እኮ አይደለም፤ ህጉ እኮ እንደዚህ አይደለም ወዘተ... እያለ የሚያምታታ። ይህ በስርዓት ታቅዶ፣ ተወያይተውበት ሰው ተመድቦ ነው የሚሠራው።

ይህ ውስጥ ገብቶ እጅ እያወጣ እየደገፈን የሚውለው ኃይል ልክ ስብሰባውን ጨርሶ ሲወጣ ማታ በመግለጫ ይቃወመናል። ውስጥ ሲደግፈን ቆይቶ በመግለጫ ይቃወመናል። ውስጥ የሚሳደበው ደግሞ በሚዲያ አይታይም። ይህ <<በአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን>> ዓይነት የነበረ ስልት ነው። በዚያ ጊዜ እንዲህ ነው፤ ይከፋፈሉና ጨዋታ ይጫወታሉ። እናውቀው ስለነበር ግን እኛን ብዙም አልጎዳንም። መድረኮቹ ግን የጭቅጭቅ፣ የንዝንዝ ተደርጓዋል። የሥራ እንዳይሆኑ ጥረት ተደርጓል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ፓርቲው የተወያየበት ምስጢር እንዲወጣ ከፓርቲው ውሳኔ ውጪ በተቃርኖ ለህዝብ መናገር፣ ውስጥ እጅ እያወጡ ውጪ መቃወም፣ ወንጀለኛ መሸሸግ፣ ኢትዮጵያ በሁሉም፤ ከሁሉም ለሁሉም የሆነ ተቋም ይኑራት ሲባል አሁን አፋር አሁን ሱማሌ የሚባለው እንዴት ከኛ እኩል ድምፅ ያወጣል በሚል አካታች የሆነ ፖለቲካ የሚቃረን ሃሳብ በስፋት ተሠርቷል። የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከገዢ ፓርቲ አንጻር የፈወሰው ትልቁ ውልደት የብልጽግና መፈጠር ነው። ብልጽግና ሲፈጠር ከፖለቲካ መድረክ ያላቸው ቁማር እንዲቆረጥ አድርጓል። ትልቅ ድል የብልጽግና መፈጠር ነው።

በእርግጥ ብልጽግና አሀዳዊ ነው ለማለት ሞክረዋል። ብልጽግና አሀዳዊ አይደለም። ብልጽግና እውነተኛ የፌዴራል ስርዓት የሚፈጥር ፓርቲ ነው። ብልጽግና ሁሉም ብሄሮች በቋንቋቸው፣ በባህላቸው ተከብረውባት ሁሉም ብሄሮች እምዬ የሚሏት ኢትዮጵያ እንድትኖር የሚፈልግ ሃይል ነው። አንዱ ከፍ አንዱ ዝቅ እንዲል አይፈልግም፤ አንዱ ቋንቋ እንዲያድግ፤ አንዱ እንዲጠፋ አይፈልግም። ለዚህ አልታገለም። ለዚህም ነው ሁሉም ህዝቦች በእኩልነት የሚሳተፉበት ተቋም ለመገንባት ጥረት የሚያደርገው።

> “የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከገዢ ፓርቲ አንጻር የፈወሰው ትልቁ ውልደት የብልጽግና መፈጠር ነው። ብልጽግና ሲፈጠር ከፖለቲካ መድረክ ያላቸው ቁማር እንዲቆረጥ አድርጓል። ትልቅ ድል የብልጽግና መፈጠር ነው...”

እነዚህ ኃይሎች እንዴት አሸባሪና አሸባሪ ሚዲያዎች ሀገር ውስጥ ይገባሉ ብለው መከራ ሲያሳዩን ቆይተው አሸባሪ ካሉት ኃይል ጋር ፌዴራሊስት ኃይል ብለው መሰረቱ።[12]

ምንም ይሉኝታ ምናምንም የለም ማለት ነው። ወደ ሀገር ውስጥ እናስገባ ስንል እንዴት ይገባሉ ጭቅጭቁ ከፍተኛ ነበር። በኋላ ወዳጅ ሆነው ፌዴራሊስት ብለው ሞከሩ።

የፓርቲ ለውጥን ተከትሎ የህወሓት ጁንታ የተከተለው አካሄድ ከኮሚንታንግ ትምህርት የተወሰደበት ነው። ኮሚንታንግ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ቻይናን ነፃ እያወጣ ሲሄድ ሁለት ሚልዮን የሚጠጉ ሲቪል ሰርቫንትና የመንግሥት ተቋማትን ይዞ ታይዋን የምትባል ሀገር ፈጥሯል። ኢኮኖሚም የተማረም ሰው ነበረኝ ብሎ ነው ይህን ያደረገው። ኮሚንታንግ ግን አንድ ዕድል ነበረው። ታይዋን ወደብ አላት።

ልክ እንደ ኮሚንታንግ እዚህ ያለው ሰብስበው የፓርላማ አባላት ሳይቀሩ ሄዱ። እባካችሁ መገንጠል የሚባለው ሃሳብ ለእናንተ አይጠቅምም፤ ጥቅማችሁ የሚረጋገጠው ከኢትዮጵያ ጋር ነው። አታስቡት፤ የእንትና የእንትና ልምድ ኪሳራ አምጥቷል። ስንል <<ኧረ እኛም አላሰብንም>> በሚል የኮሚንታግን ያረጀ ያፈጀ ፍላጎት ለመከወን ነው ከፖለቲካ ፍላጎት አንፃር ሲሠሩ የነበሩት።

---

12 ህወሓት ከብልጽግና ፓርቲ ጋር እንደማይቀላቀል አቋሙን ይፋ ካደረገ በኋላ ‹‹የኢትዮጵያ ፌዴራሊስት ኃይሎች ጥምረት ለሀገራዊ መድህን›› የሚል የተለያዩ ፓርቲዎች ስብስብ አደራጅቶ በመቀሌ ስብሰባ ሲያካሂድ ነበር። በመድረኩ ከሚሳተፉ ፓርቲዎች መካከል አንዳንዶች ከለውጡ በፊት በሽብርተኝነት የተፈረጁ ነበሩ።

# የኢኮኖሚ ሪፎርሙ እና እንገት የያዘው የብር ኖት ለውጥ

ከኢኮኖሚ አንፃር ያየን እንደሆነ ኢኮኖሚ ተቀዛቅዟል፣ማክሮ ኢኮኖሚክ ያለመመጣጠን (imbalance) አለ፣ ሥራ እጥነት አለ፣ ፕሮጀክቶቻችን ትልቁም ትንሹም በምዝበራ ቆመዋል፣ የተመዘበረ ፕሮጀክት ነው ያለው። ደመወዝ መክፍል ችግር ነው፣ እዳ መክፈል ችግር ነው። የውጭ ምንዛሪ ችግር ነው።

> በኢኮኖሚ ብዙ ሪፎርሞች ተሠርተው ልክ እንደ ብልጽግና የመጨረሻ እንገት የሚይዘው የብር ኖት ለውጡ ነበር...”

ይሄን ሪፎርም ካልሠራን መከላከያ ምንም ቢያብጥም ደመወዝ ካላገኘ ይበተናል። ልክ እንደ ፖለቲካው ኢኮኖሚውም ሪፎርም ይፈልግ ነበር። በኢኮኖሚ ብዙ ሪፎርሞች ተሠርተው ልክ እንደ ብልጽግና የመጨረሻ እንገት የሚይዘው የብር ኖት ለውጡ ነበር። በብር ለውጡ ምክንያት የመጣው የኢኮኖሚ ለውጥ እየተሳካ ዓለምም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ለውጥ ተስፋ የሚጣልበት መሆኑን እያወቀ ሄደ። ፕሮጀክቶች ድንጋይ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን መጨረስ እንደሚቻል በትንሹም በትልቁም እያሳየን ሄድን።

በነገራችን ላይ ለጊዜ ብዬ አልገባም እንጂ ልክ እንደ መከላከያ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ባንኮች እና ትልልቅ የልማት ተቋማት ልክ እንደመከላከያ የታጠሩ ነበሩ። የታጠሩት ለሥራ አይደለም ሀብት <<ኤክስትራክት>> ለማድረግ ነው። በመከላከያና በደህንነት ተቋማት ያለው ሁሉ በኢኮኖሚ ሴክተር አለ። በቴሌኮም አለ፣ በኤልፓ አለ፣ በስኳር በሁሉም አለ። እዚህ ውስጥ አልገባም። ኢኮኖሚክ ሪፎርሙ ግን በጣም ወሳኝ ነበር።







# አፈናን ታሪክ ያደረገ የፍትህ ዘርፍ ሪፎርም ...

ኢትዮጵያ ውስጥ አፋኝና የፖለቲካ ምህዳር የሚያጠቡ ብዙዎች የሚቃወሟቸው ሕጎች ነበሩ። የለውጥ ሃይሉ የመጀመሪያ ስራ አፋኝ የነበሩና የፖለቲካ ምህዳር የሚያጠቡ ሕጎችን ማሻሻል ነበር። ለምሳሌ የበጎ አድራጎትና ማህበራትን አዋጅ ብትወስዱ መደራጀት ስቃይ የሆነበት ሀገር ስለሆነ ትንሽ ፈታ ይበል ብለን ሠራን። በእርግጥ እዚህ አካባቢ በጣም የተበራከቱ ኤጀንሲዎች ሥራቸውን ብቻ ሳይሆን ሌላ ተጨማሪ ሥራ እየሠሩ የማስቸገር ዝንባሌ አላቸው። እሱን እየፈተሸን እርማት የምናደርግ ይሆናል። ግን አንዱ አፋኝ አዋጅ እሱ ነበር። ጥፋተኛውንም አልሚውንም አፍኖ የያዘ።

ሁለተኛው የምርጫ ቦርድ ማሻሻያ አዋጅ ነበር። የምርጫ ቦርድ ተቋም ሆኖ ቆሞ <<ኢንዲፔንደንት ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩሽን>> ሆኖ ታምኖ ተደራጅቶ የሚፈልገውን ሥራ በሕገ መንግሥት አግባብ መከወን እንዳይችል በአዋጅ የታነቀ ስለነበረ ጠንካራ ተቋም እንዲሆን ለማድረግ የሚታወቀው ሥራ ተሠርቷል።

ሦስተኛው የምርጫ ሕግ ነው። የስነምግባር ሕግ የፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ሕግ በውስጡ የያዘ እንዴት ተመዝግበን በምን ዲሲፒሊን ሥራ እንሠራለን የሚለውንም የሚያሳይ ነው። ቀድሞ በፓርቲዎች መካከል የነበረውን ጫና የሚፈታ ሕጋዊ አግባብ የሚያሳይ ማለት ነው። ሌላው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ነው። ሰብዓዊ መብት እንደምታውቁት የኛ ካድሬዎች የሚመሩት ተቋም ነበር። ከለውጥ በኋላ ተቋሙን አጠናክረን ካቆምን በኋላ መንግሥትን ሳይፈራና ሳይቸገር ለፓርላማ ሪፖርት የሚያቀርብ ብዙ መጠንከር ያለበት ጉዳይ ቢኖርም ግን በንፅፅር <<ሊበራል>> የሆነ ነፃ የሆነ ጫና የሌለበት ተቋም ለመፍጠር ተሞክሯል።



“ኢትዮጵያ ውስጥ አፋኝና የፖለቲካ ምህዳር የሚያጠቡ ብዙዎች የሚቃወሟቸው ሕጎች ነበሩ። የለውጥ ሃይሉ የመጀመሪያ ስራ አፋኝ የነበሩና የፖለቲካ ምህዳር የሚያጠቡ ሕጎችን ማሻሻል ነበር...”

በሕግ አግባብ በልምምድ እያረመ መሄድ ያስፈልጋል። ግን እንደዚህ ዓይነት አፋኝ ሕጎች ለማሻሻል ከፍተኛ ሥራ ተሠርቷል። ይሄ ሥራ የተሠራው ካቢኔው ከለውጥ በኋላ ከሰኞ እስከ ዓርብ ሥራውን ሠርቶ ቅዳሜ ቅዳሜ የካቢኔ ስብሰባ እያደረገ ነው። አብዛኛው ሕጎች የተሻሻሉት ቅዳሜ የሚባል የካቢኔ ስብሰባ ከለውጥ በኋላ ከመጣ ነው፤በፊት አልነበረም። በተጨማሪ ጊዜ ወስደን እንሥራ በጣም ብዙ ውዝፍ ሥራ አለ ከሚል የመጣ ነው።

ከእነዚህ አፋኝ ሕጎች ውጪ በኢኮኖሚው ደግሞ የኢንቨስትመንት አዋጅ፣ የንግድ ሕግ ፤የካፒታል ገበያ አዋጅ፣ በተለይ በተለይ ደግሞ የግልግል ዳኝነት አዋጅ የሚመጣው ኢንቬስተር በሙሉ ግልግል ሲባል ሌላ ሀገር ስለሚመርጥ እኛ በተባበሩት መንግሥታት ያለውን ሕግ የተስማማን ሀገር ሆነን ስናበቃ የግልግል ዳኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ማድረግ የሚያስችል ቁመና መፍጠር እንችላለን በሚል ሕግ ተሻሽሏል። እነዚህ ሁሉ ኢኮኖሚውን የሚያሳልጡ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለንግድ ምቹ በሆኑ ሀገራት ተርታ ውስጥ ኢትዮጵያ የነበራትን ደረጃ የሚያሻሽሉ ብዙ ባለህብቶች መጥተው እንዲሠሩ የሚያደርጉ ናቸው። ከ60 ዓመት በላይ የቆዩ ሕጎች ተሻሽለዋል። የወንጀለኛ መቅጫ ስነሥርዓትን ብንወስድ 60 ዓመት የቆየ ትልቅ መድብል ነው። ከንጉሡ ጊዜ በኋላ አልተሠራም። ከሪፎርም በኋላ አሁን ያለውን ዘመን እንዲዋጅ ተደርጎ ተሠርቷል። የንግድ ሕግ የወንጀል ሕግና ስነሥርዓት የማስረጃ ሕግ ትላልቅ መድብሎች ለረጅም ዓመታት ያልተሠሩ በሕግ ሪፎርም ተሠርተዋል።

ሌላው አፋኙ ሕግ የፀረ ሽብር ሕግ ነበር። ከሽብር ወንጀል ጋር በተያያዘ በርካታ ሰዎችና ቡድኖች ይሰቃዩ ነበር፤ ሕጉ ተሻሽሏል። ከዚህ ሁሉ በላይ አስከፊው የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር አዋጅ ነበር። ሰው ከታሠረና ሕግ ፊት ከቀረበ በኋላ ጥፍር መንቀል፣ ጭለማ ቤት ማስቀመጥ፣ መግረፍ፣ ባልታወቀ እስር ቤት ማስቀመጥ የመሳሰሉት ሰብዓዊ መብትን የሚጥሱ እና የሚቃረኑ አካሄዶች እንዲስተካከሉ በቀለብ እንዳይቀጣ፣ በቲቪ ማየት እንዳይቀጣ፣ በመፃፍ ማንበብ እንዳይቀጣ ታራሚ እንዲሆን በአዋጅም በበጀትም ተደግፏል።

ሌላው የሚዲያ አዋጅ ነው ከለውጡ በፊት ከ270 በላይ ዌብ ሳይትና ብሎገርስ ዝግ ነበሩ። <<ኮንቬንሽናል ሚዲያ>> ጃም ይደረጋል። ጃም ማድረግ ካልተቻለ ደግሞ በየቤት ዲሽ እንዳይታሠር ይደረጋል። እሱ ቀርቶ ሚዲያው ለቀቅ ይደረግ ሲባል በዚያው ልክ <<አቢዩዝ>> የሚያደርጉ አሉ። እሱን



## ክፉ ቀንን የዋጀ የዲፕሎማሲ ሪፎርም

ወሳኝ ሪፎርም የተሰራበት ሌላው ጉዳይ ዲፕሎማሲ ነው። ዲፕሎማሲ ላይ ሁለት ችግሮች አሉ፤ አንደኛው ኢትዮጵያ ወደብ የላትም። ሁለተኛው ጂኦ ፖለቲክሱ ኢትዮጵያን ማዳከም የሚፈልጉ ኃይሎች ብዙ ጊዜ በዘመናት የሚታዩ አሁንም አክቲቭ ሆነው ያሉበት ሁኔታ አለ።


ጎረቤቶቻችንን ካልያዝን ፈተና ይገጥመናል የሚል ሃሳብ ነበረን። ደግሞም በተግባር እንዳየነው ዘንድሮ ከኤርትራ ጋር ታርቀን ባይሆን ኖሮ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ለመገመት ያስቸግራል። መታረቃችን የግለሰቦች አለመሆኑን መታረቃችን የህዝቦች መሆኑን ከኤርትራ መንግሥት በላይ የኤርትራ ሕዝብ በተግባር አሳይቶናል። ሶማሊያ ስንሄድ እኛኮ እናንተን አናምናችሁም፤ በክልል ከፋፍላችሁን የምታባሉን እናንተ ናችሁ፤ የእናንተ መንግሥት ነው ይሄን የሚያደርገን፤ በጣም እንጠላችኋለን፤ የሚል ሳይደብቁ ነገሩን።

ደቡብ ሱዳን ስንሄድ አሁን እኮ የምንባላበት ነገር በሙሉ የናንተ ውጤት ነው። በኢጋድ ውስጥ ስዩም መስፍን የሚባል ሰው መድባችሁ አባልቶን አከፋፍሎን ወጣ።[13] ልንታረቅ አልቻልንም ይላሉ። ጎረቤት በሙሉ እናንተኮ ብሎ የሚጠላት ሀገር ነበረች ኢትዮጵያ።

ይሄ እዚህ ያየነው መከፋፈልና መጣላት ውጪም ነበረ። በጎሳም በምንም በምንም መከፋፈል ስለነበረ ከፍተኛ ጥላቻ ነበራቸው እኛ ላይ። ይሄንን ለመጠገን የጎረቤት ሀገራት አጋርነት ማጠናከር አለብን፤

"በዚህ ኦፕሬሽን ለኤርትራ ህዝብና መንግሥት ለሱዳን ህዝብና መንግሥት ለጅቡቲ ህዝብና መንግሥት፣ ለሶማሊያ ህዝብና መንግሥት፣ ለኬንያ ህዝብና መንግሥት፣ ለደቡብ ሱዳን ህዝብና መንግሥት ከፍተኛ ምስጋናና ክብር በተከበረው ምክር ቤት ፊት ማቅረብ እፈልጋለሁ። ያልረዳን የለም ሱዳን እንደተለመደው ከጎናችን ቆማ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጋልናለች። ኤርትራ፣ ኬንያ ፣ጅቡቲ፣ ሱዳን ሁሉም ጎረቤቶቻችን ያስፈልጉን ነበር። ወደፊትም በተከባበረ መንፈስ በወዳጅነት አብረን እንሠራለን፤ ያስፈልጉናል..."

13 ስዩም መስፍን እአአ በ2015 የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ባለስልጣን (IGAD) በመወከል የደቡብ ሱዳን የእርስበርስ ግጭት እንዲያበቃ ዋና አደራዳሪ በመሆን ተሹመው ነበር።













ሚዛን መጠበቅ አለብን፤ ቅድሚያ ለዜጎች ክብር መስጠት አለብን ብለን ሥራ ጀመርን። አንዱ የኤርትራው ጉዳይ ነው፤ በጋራ ነው የተወሰነው። ብልጽግና አልወሰነም። ኢህአዴግ ነው የወሰነው። ጁንታው ነው የወሰነው። የአልጀርስን ስምምነት እንቀበል ብሎ። ቃለ ጉባኤው አለ ታቃላችሁ። ከዚያ በኋላ ፓርላማ መጥቼ አቅርቤዋለሁ ሃሳቡን። ግን እርቁ እንዳይፈፀም ያልተቆፈረ ጉድጓድ የለም።

አሁን ግን ጁንታው የተከበረውን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አዋርዶ ራቁቱን ወደ ኤርትራ ሲልከው የኤርትራ ህዝብ አለበሰው። የኤርትራ ህዝብ ውሃ አጠጣው፣ አበላው፣አስታጠቀው። ይሄን የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅም፣ ማክበርም አለበት። የኤርትራ ህዝብ ወንድም ህዝብ ብቻ ሳይሆን የቁርጥ ቀን ዘመድ መሆኑን በተግባር አሳይቷል። በነገራችን ላይ ኦፕሬሽን ተካሂዶ በየቦታውና እስር ቤት ያገኘናቸው ሰዎች እኮ በአስር ቀን ውስጥ ጠውልገዋል። ወደ ኤርትራ የወጡት ግን በሁለት ሦስት ቀን ተዋግተው አሸንፈዋል። ያስራበን የእኛ ነው፣ ያስጠማን የእኛ ነው። ራቁታቸውን የሄዱ ሰዎች የኤርትራን ህዝብ ልብስ ለብሰው መጥተዋል። ለዚህ ነው የኤርትራ ህዝብ ወጋን የሚሉት። እንግዲህ ራቁታችንን አንዋጋም መቼም።

በዚህ ኦፕሬሽን ለኤርትራ ህዝብና መንግሥት ለሱዳን ህዝብና መንግሥት ለጅቡቲ ህዝብና መንግሥት፣ ለሶማሊያ ህዝብና መንግሥት፣ ለኬንያ ህዝብና መንግሥት፣ ለደቡብ ሱዳን ህዝብና መንግሥት ከፍተኛ ምስጋናና ክብር በተከበረው ምክር ቤት ፊት ማቅረብ እፈልጋለሁ። ያልረዳን የለም ሱዳን እንደተለመደው ከጎናችን ቆማ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጋልናለች። ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን ሁሉም ጎረቤቶቻችን ያስፈልጉን ነበር። ወደፊትም በተከባበረ መንፈስ በወዳጅነት አብረን እንሠራለን፤ ያስፈልጉናል።

# ነገረ ሰሜን እዝ

## የመጨረሻው መጀመሪያ

የህወሓት ጁንታ እስከ ጎረቤት ሀገራት የዘለቀ የጥፋት እጁን ዘረጋ፤ ሀገር በማተራመስና በማፍረስ በሚፈጠረው ክፍተትም የሰራው ወንጀል ተድበስብሶ እንዲቀር ሲጥር ከረመ፤ ሁሉም አልተሳካለትም። የኋላ ኋላ በሰሜን እዝ የፈጸመው በግፍ የተሞላ ጥቃት የመጨረሻው መጀመሪያ ሆነ ...



የሰሜን ዕዝ ጥቃት ድንገት አልተፈፀመም። ተሳደቡ መልስ የለም፤ በኢኮኖሚው በመሣሪያውም በሌላውም ሻጥር ሠሩ መልስ የለም። በየቦታው አጋደሉ፣ አፋኑ፣ መልስ የለም። የጨረቃ ምርጫ[14] ሲያካሄዱ ጠብቀዋል አልወጋናቸውም ዝም አልን፤ መልስ የለም። ብዙ ፖለቲካ ተጫወቱ፤ መልስ የለም። ይሄ ሁሉ ሲመራቸው ነው ወደ ውጊያ የገቡት።

ከዚያ በፊት ግን ሰሜን እዝ እና ሌሎች እዞችን ስናነጻጽር በአጭር ቋንቋ ሌላው እዝ ተደምሮ ሰሜን እዝን አያክልም። በትጥቅም በሁሉም ነገር የኢትዮጵያ የመከላከያ ዲፖ የሚባለው እያንዳንዱ ተተኳሽ ያለው ትግራይ ክልል ነው። አንድም ተተኳሽ እዚህ የለም። ኢትዮጵያ ያላት ሮኬትና ሚሳኤል በሙሉ ያለው ትግራይ ክልል ነው። ሚሳኤል ላይ የሚጫወቱት ሰዎች በሙሉ የአንድ አካባቢ ሰዎች ናቸው።

ያንን ሮኬት ለማምጣት ብዙ ሙከራ ተደርጓል። ጠርተን ይሄ ሮኬት ሌላ ቦታ አደጋ እያጋጠመን ስለሆነ፤ አሁን የኤርትራ ጉዳይ ስለማያስፈራን እናንሳው ስንል፤ ከእኛ ጋር የተወያየው ማታ ሪፖርት ያደርጋል ጠዋት ሕፃናት ያስተኛሉ፤ ሴቶች ያስተኛሉ፤ አይሄድም ከዚህ ይላሉ። ለምን ሲባል፤ ኤርትራ ይወጋናል ይላሉ። ዋናው ጉዳይ ኤርትራ አይደለም እንደማይወጉ ያውቃሉ፤ ትጥቁ አይወጣም ነው። እየተዘጋጁ ስለነበረ። እኛ ደግሞ ጨፍልቀን ገድለን ከወጣን እንኳን ሌላው ህዝብ እናንተም አትቀበሉም። እንዴት መከላከያ ሕፃናት ገድሎ ይወጣል።

እያስታመምን እያባበልን ሚሳኤል ማውጣት እንደማንችል ስናውቅ ሚሳኤሉ በስታርተር (starter) ስለሚነሳ ቁልፉን አምጡ አልን። ቁልፉን አምጥተው አሳይተው መከላከያ ነው ያለው ብለው ያስቀመጡ ሰዎች ናቸው ውጊያው ሲጀመር አሁን በየቦታው የሚተኮሰው ማለት ነው።[15]

በነገራችን ላይ መከላከያ ትጥቁም ስንቁም ሜካናይዝዱም ለዓመታት እዚያ እንዲከማች የተደረገበት ምክንያት ይህ ለውጥ ባይመጣም የህገሪቱ አቅም በሆነ መንገድ እዚያ ብቻ እንዲሆን ታስቦ የተሠራ መሆኑ ግሃድ ነው። የኢትዮጵያ ታንክ፣ መድፍ፣ ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ ትልቁ የነዳጅ ዲፖ እንኳን እዚያ ነው።

ስለዚህ ወታደሩ <<ሞቢሊቲ>> የሚባል ነገር እንዳይኖረው የታሰበ ነበር። ያንን ሁሉ ገዝቶ ለመተካት ገንዘብ የለም፤ በስፔሻል ኃይል፣ በአየር ኃይል እና በሮኬቶች ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። ነገር ግን እናንተ ዘገያችሁ ያላችሁት ገና ከዚህ በላይ ጊዜ ያስፈልገን ነበር። መከላከያን በሹመት አይቻልም፣ አንድን ሻለቃ እንደሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ መሾም አይቻልም።

መሣሪያዎች እንዳይወጡ ካደረጉ በኋላ ግን ተስፋ ቆርጠን እንድንዘጋጅ ያደረገን የበቀደሙ ሳይሆን ሌላ ቦታ ግጭት ገጥሞን በዚያ ደረጃ ሀገራቸውን ይከዳሉ የሚል ግምት ስላልነበረን ግጭቱን ሪፖርት አቅርበን ወታደሩና ትጥቁ በተወሰነ ደረጃ ኢትዮጵያን ይከላከል አደጋ እያጋጠመን ነው ስንል <<በፍጹም አይሆንም፤ ወታደሩም ሆነ ትጥቁ አይሄድም!>> አሉ። በዚያ በኩል ውጓቸው እያሉ በዚህ በኩል ትጥቁ አይሄድም አሉ።

ይህንን ሥራ እየሠሩ ቆይተው ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ከምሽቱ አምስት ሰዓት ተኩል ገደማ እዚህ ያለው ግልገል ጁንታ መገናኛ በጣጥሶ እዚያ ያለው መብራት እና ስልክ አጥፍቶ በየቦታው ወታደሩ አርባም፣ ሃምሳም፣ ስድሳም ሆኖ ተበታትኖ እርስ በእርሱ እንዳይገናኝ እንዳይተጋገዝ ኮሙኒኬሽን አጥፍተውበት በሚሊሻ ከበው እምቢ ያላቸውን ደግሞ ቁስ እና ሽማግሌ እየላኩ እጅ ስጥ እያሉ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ግፍ ፈጸሙ። ብዙዎቹን አፈኑ፣ ብዙዎቹን ገደሉ። የተገደሉት የእኛ ወታደር ሄዶ እስኪቀብራቸው እጅና እግራቸው ታስሮ ራቁታቸውን ነበሩ።

በነገራችን ላይ አስከሬን ዘር የለውም። ሰው በህይወት ካለ ብቻ ነው ዘር ያለው፤ ዘር ማለት ቋንቋ፣ ባህል ነው፤ አስከሬን ቋንቋ፣ ባህል የለውም። ሲሞት ሰብዕናውን ትቶ ሬሳ ነው የሚሆነው። ሬሳንም ኦሮሞ ነህ፣ አማራ ወይ ጉራጌ ነህ ብሎ ማሰብ ሰብዓዊነት አይደለም። መግደል ሳያንስ አለመቀብር በጣም ጸያፍ ነው። ያውም ብዙ ውለታ የዋለልህን ወታደር። እብሪትና ትዕቢት መጥፎ ነው፤ በእብሪትና በትዕቢት ተወጥረው መሣሪያ ካለን ብለው ነው ያደረጉት። ይሄን ከማድረጋቸው በፊት በይፋ በመድረካቸው ላይ እኛ የምንለውን የኢትዮጵያ መንግሥት ካልፈጸመ እንኳን

14 ህወሓት ህገ መንግሥቱን በመጣስ በትግራይ ክልል ምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም ጳጉሜ 4 ቀን 2012 ዓ.ም ህገ ወጥ ምርጫ አካሂዷል። ከአጠቃላይ ከ190 የምክርቤቱ መቀመጫዎችም ህወሓት 189 መቀመጫ አግኝቻለሁ ማለቱ ይታወሳል።

15 የህወሓት ጁንታ ከሰሜን እዝ በህገወጥ መንገድ የወሰዳቸውን ሮኬቶች ወደ ባህርዳርና ጎንደር መተኮሱ ይታወሳል። ወደ ጎረቤት ሀገር ኤርትራ ሮኬቶቹን በመተኮስ ግጭቱ አካባቢያዊ ይዘት እንዲኖረው ቢሞክርም ምንም አይነት የአጸፋ እርምጃ አልተሰጠውም። ሮኬቶቹ ኢላማቸውን ያልጠበቁ እንደነበሩ ይፋዊና ይፋዊ ያልሆኑ የሀገራቱ ምንጮች አረጋግጠዋል።



ሴኮቱሬ ጌታቸው

> መብረቃዊ ጥቃት ፈጽሜ ሰሜን እዝን በእጄ አድርጌአለው ነው ያሉት፤ የክልሉ መሪዎች እየወጡ የሰሜን እዝ ከእኛ ጋር ነው የሚዋጋው ይላሉ...”

ኢትዮጵያን ምሥራቅ አፍሪካን እንበጠብጣለን በማለት በአደባባይ ለዲፕሎማቶች ሲናገሩ ነበር። ዲፕሎማቶቹም ይፈራሉ፤ እነዚህን ከነካችሁ አካባቢው ይታመሳል ይላሉ።


በጣም የሚያሳዝነው ግን ያረጀ ዝንጀሮ በወጣትነት የለመደውን ዝላይ ለመዝለል ሲሞክር የሚገጥመው ችግር ነው። እነዚህ ሰዎች ምንም ዓይነት የወታደራዊ ሳይንስ እውቀት የላቸውም። በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በውትድርናውም ያረጀ ሃሳብ ነው ያላቸው።

ይህን በተመለከተ ሁለት ታሪካዊ ጭብጦችን በማሳያነት ላቅርብ። የመጀመሪያው የአሜሪካን የእርስ በርስ ጦርነት ነው (እአአ ከሚያዝያ 1861 እስከ ግንቦት 1865)። የእርስበርስ ጦርነቱን የፈጠረው ዋናው ጉዳይ በደቡብ አሜሪካ ግዛቶችና በሰሜን አሜሪካ ግዛቶች የነበረ ግጭት ነው። ግጭቱም የባሪያ ስርዓት ይቅር፣ አይቅር የሚል ነበር። አብርሃም ሊንከን የተሰኘው ፕሬዚዳንት ሲሾም የባሪያ ስርዓትን አስቆማለሁ አለ። ደቡብ አካባቢ ያሉ በጥጥና በሰሊጥ እርሻ የሚታወቁት ግዛቶች  ይሄ ስርዓት መቀጠል አለበት መቆም የለበትም የሚል አቋም ያዙ። ጀነራል ጀፈርሰን ዴቪስ የሚባል በአሜሪካን ጦር አካዳሚ የተማረ በደቡብ ግዛት አካባቢ እራሱን ቺፍ ኦፍ ስታፍ አድርጎ ደቡቦች ተገንጥለናል ብለው የአብርሃም ሊንከንን አስተዳደር አንቀበልም የሚል ዘመቻ አደረጉ።

አብርሃም ሊንከን ልክ እንደኛ ለዓመታት ለመነ ታገሰ። ይሁንና ሳውዝ ካሮላይና የሚባል ግዛት ውስጥ የነበረ ሜካናይዝድ ጦር ሳያስብና ሳይዘጋጅ በጀነራል ጀፈርሰን ዴቪስ በሚመራ ቡድን በሌሊት ተደበደበ፤ መሳሪያ ተቀማ፣ ተነጠቀ። ጀነራል ጀፈርሰን ወታደር ነኝ ውትድርናን ከኔ በላይ የሚያውቅ የለም በሚል እብሪት ተወጥሮ ነበር ይህን ድርጊት የፈጸመው።

አብርሃም ሊንከን ሚሊሻዎች ጠርቶ መጀመሪያ የሠራው እነዚህ የደቡብ ግዛቶች ወደውጭ የሚሄዱበትን ድንበር መዝጋት ነበር። እነሱ እንደ ጄፈርሰን ዴቪስ ሰሜን እዝን ሲያጠቁ እኛ ደግሞ ፈጠን ብለን ድንበር መዝጋት ላይ ነው የመጀመሪያውን ኦፕሬሽን ያካሄድነው።

አሜሪካኖችን በዚያ ዘመን ያጋጠማቸው ፈተና ዛሬ እኛም ደርሶብናል። ደቡብን ከሰሜን ጋር አንድ በማድረግ የተቋጨው ለሶስት አመት ተኩል የተካሄደውን የእርስበርስ



> አሁን የማይካድራው በምን አማርኛ ነው የሚገለጸው፤ ምንድን ነው የሚባለው፤እነዚህ ሰዎች የታጠቁ እንኳን ቢሆኑ ምንአልባት ስም ይሰጠዋል። ምንም የማያውቁ የቀን ሠራተኞችን ሰብስበው ፣በቀን ሸቅለው የሚኖሩ ሰዎችን ሰብስበው፣በላባቸው የሚሠሩትን ሰብስበው በጅምላ ማረድ ይህ የፖለቲካ ሽንፈት እና ውድቀት፤ የሞራል ድቀት ካለሆነ በስተቀረ ሰብዕና አይደለም መጥፎ ድርጊት ነው…”

ጦርነት የተቀሰቀሰው የእነ ጄፈርሰን ዴቪስ አካሄድ ህገመንግስታዊ አይደም በሚል ነው። ጊዜው ቢለያይም እኛም የገጠመን ነገር ተመሳሳይ ነው። ህገ መንግስት ተጥሶ ጥቃት ተፈጸመብን፤ በሦስት ዓመት ተኩል ሳይሆን በሦስት ሳምንት ጨረስነው። በአጋጣሚ ጉዳዩን በዚህ ብትረዱን ጥሩ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ።

ሁለተኛው አሜሪካ ጋር የሚያያዘው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፐርል ሃርበር በሚባል ቦታ ላይ ጃፓን በአሜሪካ ጦር ላይ ተመሳሳይ ያልታሰበ ድንገተኛ ጥቃት ፈጽማ የባህር ኃይሉ የአሜሪካን ጦር መታ። ያኔም የአሜሪካ ፓርላማ እራሱን ለመከላከል ወስኖ ጦር መዛሪያ ብቻ ሳይሆን የኑክሊየር ቦምብ ተጠቅሞ ጃፓን እንዳልነበረች ሆነች።

በነገራችን ላይ በአሜሪካ የእርስበርስ ጦርነት የጀነራል ጀፈርሰን ዴቪስ ትዕቢት ከቀሰቀሰው ጦርነት 20 ዓመት በኋላ የደቡብ አሜሪካ ግዛት እራሱን ወደነበረበት መልሶ መገንባት አልቻለም።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተፈጸመ በኋላም ወደ ጃፓን የዘመተውን የአሜሪካ ጦር የመራው ጀነራል ማክአርቱር የሚባለው ውጊያውን አሸንፎ ሲወጣ በቶኪዮ ውስጥ ሻል ያለው መንደር የአሜሪካ ጦር ሰፈር ብቻ ነበር። ቶኪዮ ከአሜሪካ ካምፕ ውጪ ምንም ዓይነት መሰረተ ልማት የማይታይባት የወደመች ከተማ ሆና ነበር። በዚያም ሳያበቃ እስከአሁንም ድረስ በዚያ ውጊያ ሰበብ በጉዳዩ ምንም ዓይነት እውቀት የሌላቸው ቀጣይ ትውልዶች በጃፓን ውስጥ ምን ዓይነት በሽታ ታቅፈው ሲወለዱ እንደነበር ይታወቃል።

ይህንን ያረጀ ያፈጀ እሳቤ ይዞ ነው ስግብግቡ ጁንታ የሰሜን እዝ ላይ ጦርነት ያወጀው፤ ማወጅ አይደለም አንድ የእኛ ሰው አለ እዚያ፤ በእኛ ሰው አማካይነት እንደነገሩን መብረቃዊ ጥቃት ፈጽሜ ሰሜን እዝን በእጄ አድርጌአለው ነው ያሉት፤[16] የክልሉ መሪዎች እየወጡ የሰሜን እዝ ከእኛ ጋር ነው የሚዋጋው ይላሉ።

ሰሜን እዝ ማለት ከኤርትራ ጋር የተዋጋ ብቻ ሳይሆን 20 ዓመት ተጨማሪ ጥቃት እንዳይፈጸም የተከላከለ ኃይል ነው። ሰሜን እዝ ከእነሱ ጋር ከሆነ ምንም ማሰብ አያስፈልግም። ድሮም እየተከላከለ ነው፤ ጨኸት አያስፈልግም። እሱን ይዞ መከላከል ነው፤ ትጥቁ ያለው እዚያ፤ሰው ያለው እዚያ፤ በአንድ ሚዲያ ከእኛ ጋር ነው። ጠዋት ደግሞ ተወጋን። የሚገለባበጡ ጉዳዮች አሉ።

ንጹሐንን ማስጨረስ፣ አሁን የማይካድራው በምን አማርኛ ነው የሚገለጸው፤ ምንድን ነው የሚባለው፤እነዚህ ሰዎች የታጠቁ እንኳን ቢሆኑ

16 ህዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት በጁንታው የሚተዳደረው ድምጺ ወያነ ቴሌቪዥን ‹‹እይታ›› በሚል በሚያስተላልፈው የውይይት ፕሮግራሙ የጁንታው አባል የሆኑት አቶ ሴኮቱሬ ጌታቸው ተጋብዘው የትግራይ ልዩ ሃይልና ሚሊሻ በሰሜን እዝ ላይ አስቀድሞ ጥቃት መፈጸሙን አስመልክቶ የሚከተለውን ብለዋል። ‹‹ የትግራይ ህዝብ ግልፅ የሆነ አደጋ ላይ መግባቱን በመገምገም ከውስጥም ከውጭም በሁሉም አቅጣጫ ትግራይን ለመጨፍለቅ የታሰበው ሴራ ጫፍ ላይ መድረሱን በመገንዘብ ፈጣን እርምጃ መውስድ ነበረበት። ለዚህም ነው የሰሜን ዕዝን ከተባበሩት እጃችንን አናነሳም ካሉት የዕዙ አባላት ጋር በመተባባር እና ሊተባባሩ ፍቃደኛ ያልሆኑትን ደግሞ በሀይል ተልዕኳቸውን እንዳይወጡ ‹‹ዲሞብላይዝ›› የማድረግ እንቅስቃሴ ነው። በጣም ፈጣን የሆነ እርምጃ ነው የተወሰደው። በ45 ደቂቃ ውስጥ ዕዙን በሙሉ ለመቆጣጠር የተቻለበት ነው፤ አንዳንድ ፖኬቶች ላይ ከቀሩት ውጪ። እንግዲህ ይሄ እርምጃ ‹‹አንቲሲፓቶሪ ሰልፍ ዲፌንስ›› (anticipatory self defense) የሚባል አለም አቀፍ ሃሳብ አለ። ትንንሽ ሀገሮች ለጥቃት የተጋለጡ መሆናቸውን ሲያዩ እና ግልፅ የሆነ የመጥፋት ስሜት በሚሰማቸው ጊዜ፤ እንጨፈለቃለን ብለው ባሰቡ ጊዜ ፈጣን የሆነ መብረቃዊ የሚባል ጥቃት በማድረስ ወራሪውን ሀይል በማዛባት በማተራመስ እራሳቸውን ከጥቃት የሚያድኑበት ዘዴ ‹‹አንቲሲፓቶሪ ሰልፍ ዲፌንስ›› ይባላል። ቀደም ብለህ ነገሮች ከመድረሳቸው በፊት የምታደርገው የመከላከያ እርምጃ ነው። … ስለዚህ መብረቃዊ የሆነ እርምጃ መወሰድ ነበረበት ፤ ያ መብረቃዊ እርምጃ ባይወሰድ ኑሮ ይህን ጊዜ ትግራይ አሁን ቁጭ ብልን የምናወራበት አይነት ክልል አይሆንም ነበር። … የሰሜን ዕዝን በመበታተን በሰላም የሚገቡት በሰላም እንዲገቡ በማድረግ ያለውን የጦር መሳሪያ በሀሪገቱ ሰባ ሰማኒያ ፐርሰንት ሊሆን የሚችለውን ከባድ መሣሪያን ጨምሮ የተኩስ አቅም ጨምሮ የትግራይ ህዝብ አቅም እንዲሆን በማድረግ ስለተጠናቀቀ የመጀመሪያው እንቅስቃሴ ነው።››



በማይካድራ የጅምላ ግድያ የተፈጸመባቸውን ዜጎች ወደ ቀብር ስፍራ ለመውሰድ ያገለገለ ቃሬዛ፤

ምንአልባት ስም ይሰጠዋል።[17] ምንም የማያውቁ የቀን ሠራተኞችን ሰብስበው ፣በቀን ሸቅለው የሚኖሩ ሰዎችን ሰብስበው፣በላባቸው የሚሠሩትን ሰብስበው በጅምላ ማረድ ይህ የፖለቲካ ሸንፈት እና ውድቀት፤ የሞራል ድቀት ካለሆነ በስተቀረ ሰብዕና አይደለም መጥፎ ድርጊት ነው።

በነገራችን ላይ በወታደርና በዜጎቻችን ብቻ አይደለም፤ ሽሬ አካባቢ የስደተኞች ካምፕ አለን፤ በዚሁ ካምፕ የነበሩ የሌላ ብሔር ተወላጆችን እንዲሁ አፍነው አስረዋቸዋል። በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ላይ ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል። በሁሉም ነው የተሠራው። ይህ ሥራ ዓላማው የነበረው መጀመሪያ ሰሜን እዝን መምታት፣ በማግስቱ ጠዋት ደግሞ ጎንደር እና ወልዲያን መያዝ፣ ከዚያም አዲስ አበባ ባሉ ወኪሎች ቦንብ ማፈንዳት፣ ከዚያም አዳማ እንዲሁም ሃዋሳ ቦንብ ይፈነዳል፣ ሀገር ይበጠበጣል፣ ከዚያ ወዲያ የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን ብለው ነበር። እዚህ ያሉ ኃይሎችም መንግሥት ሲቀየር የሆነ የሆነ ቦታ ለመያዝ እየተዘጋጁ ነበር።

17 የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) እንዲሁም በትግራይ ክልል የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተከትሎ የተቋቋመው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ የመስክ ምልከታ አድርገው ባወጡት የመጀመሪያ ሪፖርት ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በማይካድራ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የጅምላ ግድያ ተፈጽሟል። በተለይ በከተማው የአማራ ብሔር ተወላጆች በብዛት በሚኖሩበት ልዩ ስሙ ‹‹ግንብ ሠፈር›› በሚባለው መንደር እስከ ወልቃይቴ ቦሌ ሠፈር ድረስ የሚገኙ ዜጎች፣ ግፍና ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ተጨፍጭፈዋል። ድርጊቱ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትና በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸመ የጦር ወንጀል ነው። ወንጀሉ ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ልዩ ሃይልና ሚሊሻ በሰሜን እዝ ላይ ጥቃት መፈጸማቸውን ተከትሎ የተደረገ ነው። ጥቃቱ ከመከሰቱ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ወደ ማይካድራ ለመግባት ሲቃረብ፣ ሁሉም ከማይካድራ የሚያስወጡ ኬላዎች በአካባቢው አስተዳደር፣ በሚሊሻና በፖሊስ ኃይሎች ተዘግተው ነበር፡ ፡ በከተማው አራት ዋና ዋና መውጫዎች በተቋቋሙ ኬላዎች ላይ በተሰማሩ ሚሊሻና ‹‹ሳምሪ›› የሚባል የትግራይ ተወላጆች መደበኛ ያልሆነ የወጣቶች ቡድን ከአካባቢው ለመሸሽ የሞከሩትን ተመልሰው ወደ ቤታቸው እንዲገቡ በማስገደድ፣ የትግራይ ተወላጅ የሆኑና ያልሆኑ ሰዎችን ለመለየት መታወቂያ ካርድ እየተመለከቱ ማጣራት አድርገው ጥቃት መፈጸማቸው በሪፖርቶቹ ተጠቅሷል። የሟቾች ትክክለኛ ቁጥር በመጣራት ላይ ሲሆን፤ እስካሁን እስከ 600 ሰዎች መሞታቸው ተረጋግጧል።

## ክብር ለቁርጥ ቀን ልጆች

የስግብግቡ ጁንታ ቡድኑ በሰሜን ዕዝ ላይ አስነዋሪ ተግባር ቢፈጽምም በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ሴራው ከሸፏል። ህገወጥ ቡድኑ ገና በማለዳው ሽንፈት እንዲከናነብ የተሰጠው የተቀናጀ ምላሽና የተገኘው ድል ምን ይመስል ነበር?



የመጀመሪያ ሥራችን ጎንደር እና ወልዲያን እንዳይያዝ ማድረግ ነው፤ ለዚህም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማግስቱ ወጥቶ ሁሉም የታጠቀ ኃይል በአንድ ኮማንድ ስር እንዲካተት ተደርጓል። በኦሮሚያ አካባቢ ያለው መከላከያ ሠራዊት በርካታ ኃይል ወደ ግዳጅ ቀጣናው ስለሚወጣ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ያንን ሽፍዋ የሚመጣውን ጠላት እንዲመክት ተልዕኮ ተሰጠው። የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ከፍተኛ ውጊያ ሲያካሄድ ነበር፤ የሚቃጣውንም ሙከራ ባያከሽፍ ኖሮ መሃል አገር ይታመስ ነበር።

የአፋር እና የአማራ ክልል ሚሊሻ እና ልዩ ኃይሎች በተለይ በድንበር አካባቢ ላይ በነበሩ ጥቃት በሚያጋጥማቸው ቦታዎች ላይ መከላከያን እስከምናስጠጋ በከፍተኛ ተጋድሎ ተከላክለው የጠላትን የመስፋፋት ፍላጎት አስቁመዋል። የቤንሻንጉል ጉምዝ ልዩ ኃይል እና የፌዴራል መንግስት በመተባበር በቤንሻንጉል አካባቢ ያለውን ሥራ እንዲሠሩ፤ የፌዴራል ፖሊስ እዚህ ከተማ ውስጥ ሆነው በፈንጂ እና በቦንብ ሊያሰቃዩ የሚያስቡ ሰዎችን ቀን ከሌት ፈትሸው እንዲያስታግሱ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። ለእነዚህ ሁሉ ከፍተኛ ክብር መስጠት ያስፈልጋል።

በተለይ የመከላከያ ኃይልን በሚመለከት የተከበረው ምክር ቤት ብዙ ሀገራት የመከላከያ ሠራዊት ዩኒፎርም ለብሰው ታክሲ ሲጠብቁ፣ አውሮፕላን ጣቢያ ሲሄዱ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ዩኒፎርም የሚከበርበት ምክንያት የጭንቅ ቀን ህይወት ስለሚያስከፍል ነው። እንደምታውቁት እኛ በቂ ደመወዝ አንከፍላቸውም። ቢያንስ እንደ ሀገር እና ህዝብ መለዮ የምናከብር በሰልፎች ቅድሚያ የምንሰጥ፤ ውትድርና ለሀገር ዋጋ የሚከፈልበት ሙያ መሆኑን የምናምን ዜጎች መሆን አለብን።

የኢትዮጵያ ጠላት እንደ መሽሩም የሚፈላ ነው። ይሄ ሀገር እንዲቀጥል ከፈለግን ለመከላከያ ክብር መስጠት ያስፈልጋል። ይህን ሁሉም ዜጎች ማድረግ አለባቸው። ማገልገልም አለብን፤ ማክበርም አለብን። ይሄን በማድረግ ነው በቀጣይ የሚገጥመንን ፈተና የምንወጣው።

ጦርነቱን በሚመለከት እንደከዚህ ቀደሙ በግርድፍ ሳይሆን ትንሽ ገባ ገባ እያልኩ ለተከበረው ምክር ቤትና ለኢትዮጵያ ህዝብ መግለጽ እፈልጋለሁ።

“በተለይ የመከላከያ ኃይልን በሚመለከት የተከበረው ምክር ቤት ብዙ ሀገራት የመከላከያ ሠራዊት ዩኒፎርም ለብሰው ታክሲ ሲጠብቁ፣ አውሮፕላን ጣቢያ ሲሄዱ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ዩኒፎርም የሚከበርበት ምክንያት የጭንቅ ቀን ህይወት ስለሚያስከፍል ነው...”

የመጀመርያው ሥራ ወደ ጎንደርና ጎጃም እንዳይስፋፉ ማድረግ፣ ጥቃትን መከላከል ነበር። ወደ ኤርትራ እንዲያፈገፍግ ያዘዝነው ኃይል አለ፤ ግን መገናኛ የለም፤ ስልክ የለም። የጥቂት ወታደሮችን ስልክ ብቻ በተለየ መንገድ ለመክፈት ሞክረን እንዲሸሹና በኤርትራ በኩል ደግሞ ሰው በእግሩ ሄዶ ውጡ እንዲላቸው መልዕክት አድርሰናል።

የሰሜን እዝ አዛዥ በሚመለከት የተከበረው ምክር ቤት እንዲያውቅ የምፈልገው ጀኔራል ድሪባ መኮንን የሰሜን እዝ አዛዥ ሆኖ እያገለገለ ውጊያው ከመጀመሩ ከ 15 ቀን በፊት ስብሰባ ከእነርሱ (ከጁንታው የህወሓት ሰዎች ጋር) ጋር ውሎ ምሳ ከበላ በኋላ ይታመማል። ራሱን ይስታል፤ ጦር ኃይሎች ይገባል። አብረው የነበሩ ሰዎች አቅምሰውት ነው የሚል መረጃ አመጡ፤ እንደዚህ ዓይነት ነገር እንዳታወሩ። በሜዲካል ይጣራ ብለን አፈነው።

ጀኔራል ድሪባ እስከዛሬ ድረስ ተነስቶ ሥራ የሚሠራበት ደረጃ አልደረሰም። እርሱ ሲታመምብን ነው ወደ አዲስ ምደባ የሄድነው እንጂ ፈልገን አይደለም። ለካስ እሱን በማኮላሸት የሚመጣውን ትዕዛዝ እምቢ የማለት ፍላጎቶች ነበሩ። ከዚያ እስኪድን ድረስ ሰው መደብን፤ የተመደበውን አንቀበልም አሉ።

በምክትልነት የሚሠራውን ጀኔራል አዳምነህ መንግስቴን አፈኑ፤ ጦሩ እንዳይገናኝ አደረጉ። ጥቃቱ ማክሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሲከፈት ሌሊቱን ሙሉ መረጃም የማግኘት ችግር ነበር። ረቡዕ  ወደ አማራ ክልል ጥቃት ስለጀመሩ፤የመጀመርያው ሥራ እንዳይስፋፉ ማቆም ነው፤ መከላከል ጀመርን። ኃይላችንን እያመጣን ካንድ ከሁለት ቀን በኋላ ተደራጅተን ድንበር ለመዝጋት ሞከርን።



ሌ/ጀነራል ድሪባ መኮንን



ብ/ጀነራል አዳምነህ መንግስቴ

ድንበር ለመዝጋት ከሞከርን በኋላ የስበት ማዕከሉ ተረጋግቶ ማሰብ እንዳይችል እያጠቃን ከትግራይ ወደ ኤርትራ የሄደውን ጦር ለማወቅ ጄነራል አበባው ታደሰ ፣ጄነራል ጌታቸው ጉዲናና ጄኔራል ባጫ ደበሌን ይዤ ወደዚያ ሄድኩኝ። ሦስቱን ጄኔራሎች ይዘን የሄድንበት ዋናው ምክንያት ጦሩን አይተን ያለበትን ሁኔታ ገምግመን ለማቀድ ነው።

ጦሩ ጋር ስንሄድ ከፍተኛ አሳዛኝ ሁኔታ ነው የነበረው። ጄነራል አበባው ታደሰ ለዓመታት የመራውና ያደራጀው የሰሜን እዝ ኃይል ነበር። ጦሩ እሱን እያየ ሲያለቅስ የፈለግከውን ዕርምጃ ትወስድብኛለህ አልመለስም በእግሬ ነው የምገባው ከጦሩ ጋር አለ። ጄነራል ጌታቸው ጉዲና የእዙ አዛዥ ነበር። ልጆቹ ናቸው የተመቱበት። ከጦሩ ጋር አለቀሰ፤ አልመለስም አለ።

ጦሩ በጣም የሚያስደንቅ ጀግንነት ነበረው። በተለይ አንዳንዶቹን በኋላም አነሳቸዋለሁ ወደ ኤርትራ ትጥቃቸውን ይዘው ማርከው ሁሉ የገቡ አሉ። ራቁታቸውን የገቡ አሉ። የጠወላለጉ አሉ። ልመናቸው በፍጥነት ይሄንን ጁንታ ወደ ህግ እናቅርብ እዚህ እንዳታቆዩን የሚል ነበር። በዚህ ምክንያት የሚያስፈልጋቸውን ካየን ከለየን በኋላ ምደባ አድርገን አስተካከልን። በዚያ በኩል ጠላት ጥርጣሬም አልነበረውም አፍርሻለሁ ብሎ ስለሚያስብ። አመራሮች መድበን በዚህ የማጥቃትና ስበት ማዕከል እያዳከምን እዚያ ስንደራጅ ቆየን።

ሮኬቱን በሚመለከት ከሮኬት ጋር ቀድሜ እንዳነሳሁላችሁ ኢትዮጵያ ያሏት ሮኬቶች በሙሉ እዚያ ነው ያሉት። ሰዎቹም የአንድ አካባቢ ሰዎች ናቸው። ለማውጣት ብዙ ተሞክሯል። አሁን ግን ልክ ችግሩ ሲፈጠር ይሄ ሮኬት አደጋ ያስከትልብናል ያሰጋል መጀመሪያ ሮኬቱን እንዳይጠቀሙበት ብለን ስናጣራ ሁለት መረጃ ነው ያገኘነው።

አንደኛው መረጃ መቀሌ ያለው ሮኬት ሦስት መቶ ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል፤ ሮኬቱን የሚያስተኩሰው መሣሪያ ደግሞ ከከተማው ወጣ ብሎ እንደሚገኝ ያመለክታል። ከዚያ ዝቅ ያለ አቅም ያለው አድዋ ሜቴክ ካምፕ ውስጥ ይገኛል። ሁሉም ወታደራዊ ሰዎች እኔም ባለሁበት ተወያይተናል፤ ተጨቃጭቀንበታል። እንምታው፣ አንምታው በሚልም ተጨቃጭቀናል።


የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ የምንፈልገው መቀሌ ላይ የተከማቸውን ሚሳኤል መምታት ምን አልባት ከተማውን ሊያጠፋው ይችላል። ምን እንደሚያስከትል እርግጠኞች ስላልሆንን ማብለያው ከከተማ ውጪ ስለሆነ ዜጎችን አይጎዳም በሚል እንዲመታ፤ ከተማ ውስጥ ያለው ግን እንዳይመታ ተወሰነ። ተመትቶ ሰዎቻችን ቢያልቁ አደገኛ ስለሆነ። አድዋ ላይ ያለው ግን ከተማ ውስጥ ሜቴክ ካምፕ ስለሆነ እርሱ ላይ ከተኮስን በከፍተኛ ደረጃ አድዋን ያጠፋታል የሚል ስጋት ስለነበር እንዲህ አይነት አደጋ የሚያስከትል ሃላፊነት መውሰድ አይገባም በሚል ትተነዋል፡ ፡ ጠላት ግን ቀድሞ ተዘጋጅቶ ስለነበር በፍጥነት ከቦታ ቦታ እየቀያየረ የእውር ድንብር ሙከራዎች አድርጓል።

ሮኬቱን በተመለከተ ይህንን ካደረግን በኋላ፤ የተከተልነው አካሄድ ሳያውቁ የተቀላቀሉ ኃይሎች እጃቸውን መስጠት

የሚያስችላቸው እድል እንዲያገኙ ማድረግ ነው። ዜጎቻችንን እንዳይጎዱ የከተማ ውጊያ እንዲቀርም ስኬታማ ሥራ ሠርተናል። ውጊያው በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅና የጠላት የማድረግ አቅም በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ሰርተናል። በነገራችን ላይ የጁንታው ኃይል ሁመራን ሳይጨምር ከሽራሮ መቀሌ ለመግባት 15 ዓመት ነው የፈጀበት (ህወሓት የሚመራው የትጥቅ ትግል በተደረገበት የደርግ ዘመን)። እኛ ግን በ15 ቀን ነው የገባነው። እኛም ሆነ እርሱ በእግር ነው የገባነው።

ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት ከጎንደር ጫፍ ጀምሮ እስከ ሁመራም እስከ ሽሬ አድዋም በእግሩ ነው የገባው። አንዳንዶቻችሁ ዘገየም ስለምትሉ ብዬ ነው። መንገዱ በኮብራ ይሰለቻል እንኳን በእግር። ወታደር ሆኖ ነው እንጂ ያደረገው እናንተ በኮብራም ይሰለቻችኋል። እኔም ይሰለቸኛል። በእግሩ እየጠማው አደረገው። ይህንን ለማድረግ የተከተልነው አሰላለፍ ፣ አደረጃጀት በግልጽ አነሳላችኋለሁ፤ እንትና ወጋ እንትና አልወጋም የሚል ውዥንብር ውስጥ እንዳትገቡ።





“የአፋር እና የአማራ ክልል ሚሊሻ እና ልዩ ኃይሎች በተለይ በድንበር አካባቢ ላይ በነበሩ ጥቃት በሚያጋጥማቸው ቦታዎች ላይ መከላከያን እስከምናስጠጋ በከፍተኛ ተጋድሎ ተከላክለው የጠላትን የመስፋፋት ፍላጎት አስቁመዋል...”

## እነ ድል ቁርሱ...

አንዳንዴ ቃላት ስሜትን አይገልጹም። ጀግንነትም ከቃላት ፊት ሲቆም የሚገለጽበት ቋንቋ የሚያጥርበት አጋጣሚ ይፈጠራል። የኢፌዴሪ ጦርሃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የህግ ማስከበር ዘመቻውን የመሩትን ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች በሚገልጹ ቃላት ጀግንነታቸውን አወድሰዋል፤ ለሀገር የከፈሉትን ውለታ ጠቅሰዋል...




## ድል ቁርሱ

ጀነራል ብርሃኑ ጁላ

ሳተናው ጀነራል በላይ፣ ልበ ቆራጡ ጀነራል መሰለ  ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ሆነው የመጀመሪያ የመከላከል ሥራ በጎንደር ሁመራ በኩል በመምራት ሁመራን ይዘዋል።  ሳተናው በላይም ሆነ ልበቆራጡ መሰለም የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው። አማካሪም አልነበራቸውም፣ የተለየ ሀይልም አልነበራቸውም። እስከ ሁመራ በእግራቸው ሄደዋል። ትንታጉ ጀነራል አበባው በምዕራብ ግንባር ወደ ተኮምብያ የወጣውን የኢትዮጵያ ወታደር አደራጅቶ አስታጥቆ እነ ገመህሎ፣ ባድመ፣ ቢያራን የመሳሰሉትን ይዞ ሽራሮን እንዲቆጣጠር ተልዕኮ ተሰጠው። ጀነራል በላይና ጀነራል መሰለ ሁመራን ከያዙ በኋላ አዲጎሹን ይዘው ተከዜን ተሻግረው ሽራሮ ላይ ከጀነራል አበባው ኃይል ጋር እንዲቀላቀሉ ተደረገ። ሽራሮን የያዘው ጀነራል አበባው ነው፤ ሁመራን የያዙት ጀነራል በላይና ጀነራል መሰለ ናቸው። ይህ ኃይል ተደምሮ ነው ሽሬንና አክሱምን የያዘው።

ራማና እዚያ አካባቢ የነበረውን ውጊያ ጀነራል ባጫ ነው ያደራጀው። የጀነራል ባጫ ተልዕኮ ወደ እንቲጬና አድዋ የሚሄደውን ቦታ እንዲይዝና ሽሬ ሲጠጋ ያኛው ኃይል አድዋን መቁረጥ ነው። በዛላንበሳ ያለውን ከመያዙ በፊት ነበልባሉ ጀነራል ባጫ የተሰጠው ተልዕኮ በጾረና በራማ በኩል ያለውን ኃይል ማደራጀትና ጀምር ሲባል መሄድ ነው። ለእርሱ ግን የሚጠበቁ ሀይሎች አሉ።



**ትንታጉ**

ሌ/ጀነራል አበባው ታደሰ




**ነበልባሉ**

ሌ/ጀነራል ባጫ ደበሌ



**ሀገር ወዳዱ**

ሌ/ጀነራል ዮሐንስ ገብረመስቀል



**የወገን አቅም ገንቢው**

ሌ/ጀነራል ሀሰን ኢብራሂም

> ነገር ግን ልዩ ሀይሉ አንድ ሰው ሳይሞት መቀሌን ለመቆጣጠር ያደረገው ጀግንነት በቃላት የሚገለጽ አይደለም። በሁመራ ላይ የነበረውን ምሽግ ይህ ልዩ ሀይል አንድ ሰው ሰውቶ ብርጌድ አፍርሷል። በፊልም ካልሆነ በስተቀር የእነዚህን ሰዎች ጀግንነት መናገር ያስቸግራል..."

በዛላንበሳ በኩል ግስላው ጀነራል ጌታቸው የወጣውን ሀይል አደራጅቶ በከፍተኛ ጀግንነትና ቆራጥነት ዛላንበሳንና አዲግራትን እንዲይዝ ተልዕኮ ተሰጥቶታል። ልክ የእነጀነራል በላይና የእነ ጀነራል አበባው ሃይል ሽሬ ሲደርስ የአድዋው የአዲግራቱ የፈጠነበት ምክንያት በየቦታው የተደራጀ፣ ቀድሞ ምሽጉን የያዘ ሀይል ስለነበረ ነው።

በምስራቅ በኩል በተለይ ከባድ መሣሪያን በማስተባበር ሥራ የጀመረው ወታደራዊ ሊቁ ጀነራል አለምሸት ነበር። ከእርሱ ጋር ነጎድጓዱ ጀነራል ሰለሞን፣ አይበገሬው ጀነራል ዘውዱ ነበሩ። ይህ አሰላለፍ ቋሚ አይደለም። የጀመርነው በዚህ መልኩ ቢሆንም በኋላ የተገላበጡ ጉዳዮች አሉ። የጁንታው ሃይሎች ቶሎ ሲጨፈለቁ አንዳንዶቹ ወደሌላ ግንባር የሄዱበት ሁኔታ አለ። ምርጫው መሰረት ያደረገው እያንዳንዱን ተራራ፤ የእያንዳንዱን ተራራ ከፍታ ነጥብና መሹለኪያ ቦታዎችን ከማወቅ አንጻር ነው።

ሳተናው ጀነራል አበባው ከኤርትራ ጋር በነበረው ውጊያ ያንን ቀጣና በስም በዝርዝር የሚያውቀው ነው። እንዲሁም ግስላው ጀነራል ጌታቸው ዛላንበሳ አካባቢን በተመለከተ ጠላት ከሚያውቀው ያልተናነሰ ወይም የተሻለ እውቀት አለው። የውጊያውን አንገት ቦታዎች፣ አስቸጋሪ ቦታዎች፣ ተራራ ቦታዎችን በመለየት ለማካሄድ ተጠቅመንበታል።



**ግስላው**

ሌ/ጀነራል ጌታቸው ጉዲና



**መረጃ አነፍናፊው**

ሌ/ጀነራል አስራት ዴኔሮ



**ወታደራዊ ሊቁ**

ሜ/ጀነራል አለምሸት ደግፌ



**ሰው ሀይል አመጋጋቢው**

ሜ/ጀነራል ሀጫሉ ሸለማ

እዚህ ድል ቁርሱ ጀነራል ብርሀኑ ጁላ ሁለት ማዘዣ ጣቢያዎችን ይዞ እጅግ የሚያስደምሙ 24 ሰዓት ከሲቹዌሽን ሩም የማይወጡ ጀግኖች ጀነራሎችን በመያዝ በኮማንድ ፖስት አጠቃላይ ሂደቱን ሲመራ ቆይቷል። ከእነዚህ መካከል አንዱ ሀገር ወዳዱ ጀነራል ዮሐንስ ይገኝበታል። በሀገሩ የማይደራደረው ጀነራል ዮሐንስ፤ መረጃ አነፍናፊውና የጠላትን ኮቴ የሚከተለው ጀነራል አስራት፤ ካርታን እንደ ምድር የሚያነበው የዘመቻ መኮንኑ ጀነራል ተስፋዬ ፤ ሎጀስቲክስን የሚያሳልጠው ጀነራል አብዱራህማን፤ የሰው ሀይልን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያመጋግበው ጀነራል ሀጫሉ፤ የወገንን አቅም የሚገነባው ጀነራል ሀሰንና ሌሎችም በአንድ ኮማንድ ፖስት ሥር ሆነው በሁለት ማዘዣ ጣቢያ ቀንና ማታ ውጊያ ይመሩ ነበር።

እዚህ ጋር ሳልገልጽ የማላልፋቸው ሁለት ሀይሎች አሉ። አንደኛው አርድ አንቀጥቅጡ ጀነራል ይልማ ነው። የአየር ሀይል አዛዥ በከፍተኛ ሁኔታ ጀግኖች ተዋጊዎችን ይዞ ባሰብነውና ባለምነው ልክ ጦርነቱ እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ ተጋድሎ ፈጽመዋል። ንስሩ ጀነራል ሹማና ጀነራል ብርሀኑ በቀለ ልዩ ሀይሎችን በማደራጀት የሰሩ ናቸው።

በነገራችን ላይ ስለ ልዩ ሀይሎች አላወራም። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ጸሐፍትና አርቲስቶች፣ፊልም ሰሪዎች በዓለም ላይ የማታገኙት ጀግንነት ተፈጽሟልና ስሩበት። እኔ ጀግንነት ልለው የምችለው ከሌላ ሀገር ጋር ተዋግተን ቢሆን ነበር። ከእኛ ለእኛ ስለሆነ የተቃጠለውም ታንክ የእኛ የሞተውም ሰው የእኛ ስለሆነ እርሱ ላይ ጊዜ አላባክንም።



**አይበገሬው**
ሜ/ጀነራል ዘውዱ በላይ



**ሳተናው**
ሜ/ጀነራል በላይ ሥዩም



**ልበ ቆራጡ**
ሜ/ጀነራል መሰለ መሰረት



**ሎጂስቲክስ አሳላጩ**
ሜ/ጀኔራል አብዱራህማን እስማኤል



**ካርታን እንደ ምድር አንባቢው**
ብ/ጀነራል ተስፋዬ አያሌው



**ጀግናው**
ብ/ጀነራል ሙሉዓለም አድማሱ

ነገር ግን ልዩ ሀይሉ አንድ ሰው ሳይሞት መቀሌን ለመቆጣጠር ያደረገው ጀግንነት በቃላት የሚገለጽ አይደለም። በሁመራ ላይ የነበረውን ምሽግ ይህ ልዩ ሀይል አንድ ሰው ሰውቶ ብርጌድ አፍርሷል። በፊልም ካልሆነ በስተቀር የእነዚህን ሰዎች ጀግንነት መናገር ያስቸግራል። በምስራቅ በኩል የሄደው ልዩ ሀይል ፊት ለፊት ያየውን ጠላት አልዋጋም ብሎ ሰርስሮ ገብቶ የመጀመሪያውን ጥይት የተኮሰው ውጊያውን ከሚመራው ጀነራል ጀርባ ሆኖ ነው። ጠላትን በትኖ ጥይት ጨርሶ በእጁ ከጠላት ተናንቆ መሣሪያ የቀማ ጀግና አለ። በዚያ መንገድ ነው በ15 አመት የሄዱበትን በ15 ቀን ድል ማግኘት የተቻለው።

እዚህ ውስጥ ብዙ መጠቀስ ያለባቸው ሰዎች ቢኖሩም ጀኔራል ግርማ ከበበው የ7ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ክፍለ ጦሩ እየተዋጋ እስከደረስንበት ቀን ድረስ እሞታለሁ እንጂ መሣርያዬን አልሰጥም ብሎ ኃይሉን ይዞ ኤርትራ የገባው



**ንስሩ**
ሜ/ጀነራል ሹማ አብደታ



**ንስሩ**
ሜ/ጀነራል ብርሃኑ በቀለ



**አርዕድ አንቀጥቅጡ**
ሜ/ ጀነራል ይልማ መርዳሳ



**ነጎድጓዱ**
ሜ/ጀነራል ሰለሞን ኢተፋ

አንዱ እሱ ነው - ሙሉ ትጥቁን ይዞ። መሸከም ያልቻለውን አቃጥሎ። እኛ ኤርትራ ስንሄድ ያ ሁሉ ታንክ ፤ ያሁሉ መድፍ አልጠበቅንም፤ የተደራጀ ትጥቅ ያለው ኃይል ነበር የወጣው። የ5ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ጀነራል ሙሉዓለም እንደምታውቂት በሁመራ አካባቢ እስከሚደረስለት ድረስ እየተዋጋ አንድም ትጥቅ ሳያስወስድ የቆየ ጀግና ነው።

**ጀግናው**
ብ/ጀነራል ግርማ ከበበው



በባድመ በኩል የ8ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ጀነራል ናስር አባዲጋ ሙሉ ክፍለ ጦሩ ሙሉ አቅሙን ይዞ ነው እየተዋጋ ነው የወጣው። በኋላም እየተዋጋ ሽራሮን የያዘው እሱ ነው። እንደነዚህ አይነት አስደማሚ ሰዎች፤ እንደነዚህ አይነት ለህይወታቸው ቅንጣት የማይሳሱ ጀግኖች ኢትዮጵያ ባትፈጥር ኖሮ ሁኔታው ካለምንም ጥርጥር አሁን ያለንበትን ነገር የሚቀይር ነው። እንደምናቃቸው ሀገራት ኢትዮጵያን የሚያደርግ ነው።

**ጀግናው**
ብ/ጀነራል ናስር አባዲጋ



# እናት ኢትዮጵያ ስትወጋ ከማየት ...



እዚህ ላይ የትግራይን ህዝብ ሚና፤ የትግራይን ህዝብ ጀግንነትና ሀገር ወዳድነት የተከበረው ምክር ቤት በትክክል እንዲገነዘበው እፈልጋለሁ። ግጭቱ ገና ሲጀመር መከላከያን አትንኩት በማለቱ ባንዳ ተብሎ የተመታ አለ፤ ህይወታቸውን ለማዳን ከፍተኛ ሙከራ ያደረጉ ሰዎች አሉ። ወደ ኤርትራ ከወጣው ጦር ጋር አብሬ እወጣለሁ፤ እናት ኢትዮጵያ ስትወጋ አብሬ አልቀመጥም ብሎ የወጣ የትግራይ ተወላጅ አለ።

ጥፋቱን ብቻ ሳይሆን ልማቱን ማየት ጥሩ ነው። በሁመራ በኩል እንዴት መከላከያን ትመታላችሁ ብሎ ከመከላከያ ጋር እየተዋጋ የቆሰለ፣ የተመታ ሰው አለ። ጉዳዩ የኢትዮጵያዊነትና የስግብግብ ጁንታነት እንጂ የኢትዮጵያና የትግራይ አልነበረም። በኋላ ሽሬ ስንደርስ 200 ብሬል ህዝቡ አምጥቶ አስረክቧል፤ ይህ የእናንተ ነው፤እናንተን ምቱ ብለው ሰጥተውናል፤እኛ አንመታችሁም ብለው አስረክበውናል። አክሱም ስንደርስ አርባ የሚጠጉ ቁስለኞችን ደብቆ አቆይቶ ይኸው ልጆቻችሁን እንካችሁ ተረከቡ ብሏል ህዝቡ።

መቀሌ ስብሰባ ነበረ፤ ዘገያችሁብን፤ እንኳን መጣችሁ። ከመጣችሁ አልቀረ ቶሎ መብራቱ፣ ስልኩም ተሰርቶ ወደ ነበረ ህይወታችን እንመለስ። በአንዳንድ ከተማ የሚታዩ ዱርዬዎችም የተበተነው ኃይልም ዘረፋና ጥፋት እንዳያካሂዱ ፤ውድመት እንዳይደርስ፤ የዚህ ሀገር ስሙ እንዳይጠለሽ በፍጥነት አስተዳደር ይመስረትልን ብሎ እጁን ዘርግቶ የተቀበለን መቀሌ ነው። ወታደሩም ሀገር ወዳድ በመሆኑ አንድም ጥፋት ሳያደርስ ማለት ነው።

ይህ ኃይል ግን በምድር ብቻ አልተዋጋንም። አንደኛ ቅድም እንዳነሳሁት በእኛ መከላከያ ውስጥ ሻምበሉ ሻለቃው ምናምኑ ወጥቶ ወደዚያ ሲሄድ አመራር የሌለው ጦር ሆኗል ማለት ነው። ዋናው ትጥቅ ተወስዷል፤ ለመከላከል የሚያመቸው የተሻለ ቦታ ተይዟል።በዲፕሎማሲ ቀደም ብለው ብር ይዘው ሰዎች ተሰማርተዋል፤ ብዙ የማሳመን ስራ ተሰርቷል። በየሀገራቱ እየሄዱ <<ሎቢ>> የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፤ በሚዲያ <<ሎቢ>> የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፤ በሚድያም በዲፕሎማሲም በሁሉም ነው ውጊያ የተከፈተብን። በሁሉም ተከፈተና ብዙዎቹ ወዳጆቻችን ወደ ንግግር ግቡ አሉ።

የተከበረው ምክር ቤት እንደሚያውቀው እኛ ንግግር በጣም ነው የምንፈልገው፤ ጦርነት በጣም ነው የምንጠላው። ስለምናውቀው ለምነናል። እስከጨፈጨፉን ጊዜ ድረስ ለምነናል። ከዚያ በኋላ ግን ጎንደርን ያዙ ፤ወልዲያን ያዙ ፤አዲስ አበባን እንደፈለጋችሁ አድርጉ ማለት ነው የቀረን እንጂ የተውነው ጉዳይ አልነበረም። እነሱም ነገር እየከረረ ሲሄድ ቶሎ ብለው ፖለቲካው መፍትሄ ምናምን ማለት ጀመሩ። ፖለቲካ ካልክ ሰሜን እዝን 20 ዓመት የጠበቀህን አትመታም። በነገራችን ላይ ማንም ሀገር አያደርገውም፤ እኛን ነው ተነጋገሩ ያሉን እንጂ ማንም ሀገር የመከላከያ ጦር ቢመታበት ይዋደቃል እንጂ አይነጋገርም። እኛ ግን ድሃዎች ስለሆንን ነው ይህን ያሉን።




በትግራይ ክልል ወፍላ ወረዳ ፋላ ቀበሌ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት የ78 አመት እናት ሀዳስ ዓለመ የጁንታውን ቡድን ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር በመሆን ድል ላደረገው የአማራ ክልል ልዩ ሃይል አባል ፍቅራቸውን ለመግለጽ እሸት ሲሰጡት፤

“እዚህ ላይ የትግራይን ህዝብ ሚና፤ የትግራይን ህዝብ ጀግንነትና ሀገር ወዳድነት የተከበረው ምክር ቤት በትክክል እንዲገነዘበው እፈልጋለሁ። ግጭቱ ገና ሲጀመር መከላከያን አትንኩት በማለቱ ባንዳ ተብሎ የተመታ አለ፤ ህይወታቸውን ለማዳን ከፍተኛ ሙከራ ያደረጉ ሰዎች አሉ። ወደ ኤርትራ ከወጣው ጦር ጋር አብሬ እወጣለሁ ፤እናት ኢትዮጵያ ስትወጋ አብሬ አልቀመጥም ብሎ የወጣ የትግራይ ተወላጅ አለ...”

# የኖቤል...

ፈታኝ ጊዜያትን በጀግኖች ልጆቿ
መስዋዕትነትና በመሪዎቿ ጥበብ
እያለፈች የምትገኘው ኢትዮጵያ
ለሁሉም ይድረስ የምትለው
መልዕክት አላት ...



## ለቅን ወዳጆቻችን...

ለወዳጆቻችን ያለኝ መልእክት ዲፕሎማሲን እናውቃለን፤ ኢትዮጵያ ማለት የተባበሩት መንግስታትን የመሰረተች ሀገር ናት፤ኢትዮጵያ ማለት የአፍሪካ ህብረትን የመሰረተች ሀገር ናት፤ ስለዚህም ስለዲፕሎማሲና ስለ መደራደር አይነገራትም። በሰላም፤ በድርድር የምንታወቅ ህዝቦችና ሀገር ነን። ሰላም አስከባሪ ሆነን ብዙ ያገለገልን ነን። በኮሪያ እና በበርካታ የአፍሪካ ሀገራት - ይህ ይቀጥላል።

ግን ለወዳጆቻችን መንገር የምፈልገው ነገር ወዳጅ መሆን ከፈለጋችሁ እኛንም ማወቅ አለባችሁ። እኛ ምንም ድሃ ብንሆን መንግስት በመሆን በጣም ብዙ ዓመታት አንዳንዶቻችሁም ሳትፈጠሩ መንግስት የነበርን ሀገር ነን። እንደ ሀገር ሳትቆሙ ሀገር የነበርን ሀገር ነን። ሀገርና መንግስት ግር የሚለን ህዝቦች አይደለንም። ይህንን እንድታውቁ እንፈልጋለን። እንኳን ዛሬ የዛሬ መቶ ዓመት የተሻለ ትጥቅ ያለው ኃይል ልግዛችሁ ብሎ አይ እኛ ሞታችንን እንመርጣለን እንጂ አንገዛም ያልን ብቸኛዋ ነጻ ሀገር ነች ኢትዮጵያ። ይህንን ከረሳችሁ ማስታወስ ያስፈልጋል።

የተከበሩ አፈ ጉባኤ ክብራቸውም ሽልማታቸውም ውዳሴያቸውም የኢትዮጵያ ህልውና ነው። በመደለያ በኢትዮጵያ ህልውና የሚደራደር ኢትዮጵያዊም አትጠብቁ። ስህተት ነው። ሰላም ወዳድ መሆናችን ለሰላም የምንተጋ መሆናችንን ተገንዝባችሁ የእኛን ነገር አውቃችሁ በትብብር መንፈስ እንስራ እንጂ ድህነት አይደለም፤ የድህነት ድህነት ቢመጣ ክብሩን አሳልፎ የሚሰጥ ኢትዮጵያዊ የለም። እንግዲህ ይህንን ነገር እንዳትፈርዱብን የእኛ ጥፋት አይደለም። አባቶቻችን ናቸው በደም ውስጥ ያስተላለፉብን፤ አንችልም። አንችልምና በሳንቲም ማስፈራራት አይሰራም።

ከኢትዮጵያ ጋር ተከባብሮ መስራት ብቻ ነው የሚያዋጣው። ለስጋችሁ ሰዎችም ኢትዮጵያን ኢትዮጵያዊ እያለ ማሸነፍ አይቻልም። ካለቅን በኋላ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይቻላል። ኢትዮጵያዊ እያለ ማንም ማሸነፍ አይችልም፤ ዛሬም ወደፊትም። በዚህ መንገድ ማሰብ ተገቢ አይደለም። ተጨንቀን ተመረን ህግ ለማስከበር ስንሞክር እኛን ማድመጥ አስፈላጊ ነው። ይሄ ለቅኖቹ ወዳጆቻችን ነው።

“እኛ ምንም ድሃ ብንሆን መንግስት በመሆን በጣም ብዙ ዓመታት አንዳንዶቻችሁም ሳትፈጠሩ መንግስት የነበርን ሀገር ነን። እንደ ሀገር ሳትቆሙ ሀገር የነበርን ሀገር ነን። ሀገርና መንግስት ግር የሚለን ህዝቦች አይደለንም። ይህንን እንድታውቁ እንፈልጋለን። እንኳን ዛሬ የዛሬ መቶ ዓመት የተሻለ ትጥቅ ያለው ኃይል ልግዛችሁ ብሎ አይ እኛ ሞታችንን እንመርጣለን እንጂ አንገዛም ያልን ብቸኛዋ ነጻ ሀገር ነች ኢትዮጵያ። ይህንን ከረሳችሁ ማስታወስ ያስፈልጋል...

የድህነት ድህነት ቢመጣ ክብሩን አሳልፎ የሚሰጥ ኢትዮጵያዊ የለም። እንግዲህ ይህንን ነገር እንዳትፈርዱብን የእኛ ጥፋት አይደለም። አባቶቻችን ናቸው በደም ውስጥ ያስተላለፉብን፤ አንችልም። አንችልምና በሳንቲም ማስፈራራት አይሰራም...”

## በተለይ ድብቅ አጀንዳ ካነገባችሁ ...

እዚህ ውስጥ ደግሞ የተደበቀ አጀንዳ አለ። የተደበቀውን አጀንዳ ስም መጥራት አልፈልግም፤ የእኛ ጎረቤቶች በሙሉ የደመቀ ኃይልና የዐቢይ ኃይል የሚባል ያላቸው ናቸው። ደመቀና ዐቢይ ተነጋገሩ እንጂ፤ ደመቀ የአንተን ወታደር ወደዛ አስጠጋ... ዐቢይ የአንተ ወታደሮች... የሚል ነው አካባቢው በሙሉ። ደመቀና ዐቢይ አልተስማሙም። ኪጋሊ ላይ ድርድር ያድርጉ ፤ጆሃንስበርግ ድርድር ያድርጉ... እየተባለ ሀገር ለሀገር የሚዞርበት ነው አካባቢያችን በሙሉ። ኢትዮጵያ አንድ መንግስት ነው ያላት። ያ መንግስቷ ህግ ያከብራል፤ በህግ ይሰራል፤ ለህግ ይገዛል፤ ካጠፋ በህግ ይጠየቃል። ለዜጎቹ ክብር ይሠጣል። በተቻለ መጠን ኢትዮጵያን የመሰለ ዴሞክራሲ ይገነባል። ሌላ ለመምሰል አንሰቃይም፤ እኛን የሚመስል፤ እንጂ እንደ እንትን ሀገር የእንትናና የእንትናን ሃይል እያልን እያጫወትን ትንሽ ክፋት የሚመስል ነገር ያለባችሁ ሰዎች እርሱት ይሄ ኢትዮጵያ ውስጥ አይሰራም። ይሄ ኃይል ምን እያደረገ እንደመጣ ፤ኢትዮጵያ ውስጥ ምን እየሰራ እንደመጣ የማይገነዘብ የዓለም መንግስት ያለ አይመስለኝም። ሁሉ ቢቀር ማይካድራን ያልሰማ ሰው የለም።

ማይካድራን ሰምተን፤ የሰሜን እዝ ምክትል አዛዥ ታፍኖ፤በሺ የሚቆጠር ሠራዊትና ዜጋ ታፍኖ፤ ሬሳ በማያውቀው ዘሩ እራቁቱን ተጥሎ፤ ሰዎች ራቁታቸውን ሄደው፤ ተነጋገሩ። ከማን ጋር ነው የምንነጋገረው?

የትኛውም ኃይል ከኢትዮጵያ ጋር በስምምነት ፤በድርድር መስራት ለሚፈልግ በራችን ክፍት ነው። ነገር ግን በግፍ፣ በጨዋታ፣በአሻጥር ኢትዮጵያን ለማሸነፍ የሚፈልጉ ሀገራት ካሉ ቁጭ ብለው ታሪክ እንዲማሩ ነው የምመክራቸው፤ አይቻልም። በሰላም፤ በምክክር፤ በዲፕሎማሲ ነው ከእኛ ጋር መስራት የሚቻለው።

በእርግጥ የተከበረው ምክር ቤት እንዲረዳው የምፈልገው የኢትዮጵያ መንግሥት የህግ ማስከበር ዘመቻውንም እያካሄደም ድርድር ሲያደርግ ነበር። ድርድር አያደርግም

> “ኢትዮጵያ አንድ መንግስት ነው ያላት ።
> ያ መንግስቷ ህግ ያከብራል፤ በህግ ይሰራል፤
> ለህግ ይገዛል፤ ካጠፋ በህግ ይጠየቃል።
> ለዜጎቹ ክብር ይሠጣል። በተቻለ መጠን
> ኢትዮጵያን የመሰለ ዴሞክራሲ ይገነባል።
> ሌላ ለመምሰል አንሰቃይም፤
> እኛም የምንፈልገው ሰላም ነው። ይህ
> ማለት የራስን ፍላጎት መግለጽ እንጂ
> በዚያ በኩል ያለው በጥፊ ሲመታህ ነገር
> እንደሚቀየር ግልጽ ነው...”

የሚለው ውሸት ነው፤ ድርድር ስናደርግ ነበር። ባለፉት ሁለት ሶስት ሳምንታት የህግ ማስከበር ዘመቻውንም እያካሄድንም ድርድር ነበር። የዓለም መንግስታትም እንዲያውቁት ድርድር የተካሄደው ከዶክተር ሙሉ ነጋ ጋር ነው።[18] ከህጋዊው የትግራይ አስተዳደር ጋር። ከእሱ ኮሚቴዎች ጋር ድርድር ነበረን፤ እንዴት ነው ትግራይን የምናደርገው? ዘመቻው የሚፈጸመው? በሚለው ዙሪያ ውይይት አድርገናል።

አንደኛ ህግ አስከብሩ ወንጀለኛ ያዙ፤ ሁለተኛ ከተማ ውስጥ እንዳትዋጉ ዜጎች እንዳይጎዱ፤ ሶስተኛ በያዛችሁት አካባቢ ክልሉን የመገንባት የማቋቋም ሥራ ስሩ ብሎ ዶክተር ሙሉ ነጋና የእርሱ ቡድን እቅድ ሰጥቶ በዚህ ዙሪያ ድርድር ስናደርግ ነበር። ከወንጀለኛ ጋር ካልተደራደርክ ድርድር የለም የሚለው ስህተት ነው። ከህጋዊው አስተዳደር ጋርማ ስንደራደርና ስንመካከር ነው የከረምነው፤ ወደፊትም ይቀጥላል።

ጦርነትን ለጎረቤትም አልመኘውም፤ ሱዳኖችም እንዳትሞክሩት አይጠቅምም፤ ሶማሊያም እንዳትዋጉ

18 በፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በትግራይ ብሔራዊ ክልል የሚቋቋመውን ጊዜያዊ አስተዳደር አስመልክቶ ደንብ አጽድቋል። በዚህ መነሻነት ዶክተር ሙሉ ነጋ በትግራይ ክልል የተቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነው መሰየማቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ህዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም አስታውቀዋል።



ዶክተር ሙሉ ነጋ
የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ

አይጠቅምም፤ እኛም የምንፈልገው ሰላም ነው። ይህ ማለት የራስን ፍላጎት መግለጽ እንጂ በዚያ በኩል ያለው በጥፊ ሲመታህ ነገር እንደሚቀየር ግልጽ ነው። በዚህ ደረጃ መገንዘብ ጥሩ ነው። ጫናው ብዙ ነው። የሆነ ሆኖ እባካችሁ ተረዱን፤ እኛ ውጊያ እንፈልግም። ሰላም እንፈልጋለን በክብራችን ከመጣ ግን ለማንም የማንደራደር መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል።

ወንጀለኞችን ለህግ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የሀገር ክህደት የፈጸሙ ፤የሽብር ሥራ የሰሩ ፤የጦር ወንጀለኞችን ያስተባበሩ ፤የመሩና የደፈሩ በርካታ ሰዎች አሉ። ይህን ከኦፕሬሽኑ ጋር በደንብ ተግባብቶ መረዳት አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያ ሥራ የታፈኑብንን ነጻ ማውጣት፤ የተገደሉብንን መቅበር፤የተቀማነውን ታንክ ማስመለስ ነበር። በሺ የሚቆጠር ቁስለኛውም ጤነኛውም ተመልሷል፤ የሚቀር አለ። የሞቱብንን ቀብረናል ፤ ካምፖቻችንን ይዘናል፤ የመንግሥት ሃብት አስመልሰናል።

“ባለፉት ሁለት ሶስት ሳምንታት የህግ ማስከበር ዘመቻውንም እያካሄድንም ድርድር ነበር። የዓለም መንግስታትም እንዲያውቁት ድርድር የተካሄደው ከዶክተር ሙሉ ነጋ ጋር ነው…
ከህጋዊው የትግራይ አስተዳደር ጋር፤
ከእሱ ኮሚቴዎች ጋር ድርድር ነበረን… ”

## ለኢትዮጵያውያን እናቶች እንባና ጸሎት

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በህግ ማስከበር ዘመቻው የትግራይ ህዝብና መሰረተ ልማቶች እንዳይጎዱ የተከፈለውን ዋጋ አንስተዋል። ያሸነፈው የኢትዮጵያውያን እናቶች እንባና ጸሎት ነው ብለዋል። በኢትዮጵያውያን እናቶች እንባና ጸሎት በተገኘው ድል ስምም ለሁሉም ዜጋ የሚበጅ መልዕክት አስተላልፈዋል...



መከላከያ ሠራዊቱ መቀሌን ከያዘ በኋላ ፍተሻ ልጀምር ወይ ብሎ ነበር፤ አይቻልም ነው ያልነው። መከላከያው ስልጠናውና ብቃቱ ለመዋጋት ነው። ከተማ ውስጥ ለመፈተሽ ልምድ የለውም፤ ሊያጠፋ ይችላል። ቦታህን ይዘህ ቆይ፤ የሰለጠነ ፌዴራል ፖሊስ ገብቶ ሥራውን ይሰራል ብለን መከላከያ አንድም ሰው ቤት አልገባም።

መቀሌ ስንቃረብ ኲያ ፣ ነጃሺና ውቅሮ አካባቢ ብታምኑም ባታምኑም አርሶ አደሩ ምንም እንዳልተፈጠረ ማሳ ይሰበስብ ነበር። የራሱ ወታደር እንደሆነ ያውቃል። ምንም የተፈጠረ ነገር የለም፤ ፕሮፖጋንዳውንም ያውቃል።

ሌላው ጉዳይ ሁለት ጊዜ 72 ሰዓታት ሰጥተናል። ለምን 72 ሰዓት ተሰጠ፤ ለምን ተራዘመ የሚሉ ሰዎች አሉ። የተራዘመበት አላማ ብዙ ነበር። ሁሉንም ግን አልገልጸውም። አንደኛው ግን ወደ መቀሌ እየተቃረብን ስንሄድ በዚያ ፍጥነትና ሞራል የመጣው ሃይል ጁንታው አለ ብሎ የሚያስበው መቀሌ ላይ ስለሆነ ትንሽ ረገብ አድርገን ስሜቱ ሰከን እንዲል ካልሰራን በኋላ የሚጸጽተን ነገር ሊፈጠር ይችላል፤ጁንታውን አገኘሁ ብሎ በትልቅ ሞራል ከሚገባ ሰከን ብሎ ስፔሻል ፕላን አውጥቶ በተለየ መንገድ ጉዳት እንዳይኖር አድርጎ በተለየ መንገድ እንዲሰራ ማድረግ ይገባል  በሚል ነው።

ሁለተኛ ጁንታው እንዳየነው በሄደበት ሁሉ እያጠፋ ስለሚሄድ መቀሌ አካባቢ ሊያጠፋ ይችላል። ሶስተኛ ውጊያ የማይፈልጉ በርካታ ሰዎች አሉ፤ እጃቸውን መስጠት የሚፈልጉ፤ ለእነሱም እድል መስጠት ያስፈልጋል በሚሉና በሌሎችም ምክንያቶች ነው።  እንደምንገባ እናውቃለን፤ እንደምንይዝ እናውቃለን፤ ግን እቅድ አውጥተን አስበን ፤ሰክነን፤ አሰማርተን ሃላፊነት ሰጥተን ማድረግ ስላለብን ነው ያዘገየነው። በአጭር ጊዜ ብለናል በአጭር ጊዜ ጨርሰናል። ከዚህ ቢፈጥንም ጥፋት ያመጣል፤ ከዚህ ቢዘገይም ጥፋት ያመጣል። በተቀመጠለት ጊዜ ነው የተከናወነው። በእርግጥ መከላከያ በሁለት ሳምንት እጨርሳለሁ የሚል እቅድ አቅርቧል። ነገር ግን በመንግሥት እንዲታይ ተደርጎ የተወሰኑ

“ወንጀለኞች ተሰባስበው ወደ ሆነ አካባቢ ሄደዋል። እንታገላለን፤ የሚል ነገርም ያነሳሉ። ከማን ጋር ነው የሚታገሉት ? መታገል ያለባቸው ከራሳቸው ጋር ነው፤ ከገዳይ ሃሳባቸው፤ ከዘራፊ ሃሳባቸው፤ ህዝብ ከሚያፍን ሃሳባቸው ጋር ነው መታገል ያለባቸው ። የትግራይ  ወጣት ምን በወጣውና ነው ከእነዚህ ጋር የሚታገለው። ተደራጅቶ በፖለቲካ ብልጽግናን ማሸነፍ ይችላል።...”

ቀናት ተጨምሯል። ምክንያቱም <<ኮላተራል ዳሜጅ>> እንዲፈጠር ስለማይፈለግ።

አሁን ቀጣይ ያለው ሥራ ወንጀለኞችን ከተደበቁበት እያወጡ መያዝ ይሆናል። ወንጀለኞች ተሰባስበው ወደ ሆነ አካባቢ ሄደዋል። እንታገላለን፤ የሚል ነገርም ያነሳሉ። ከማን ጋር ነው የሚታገሉት ? መታገል ያለባቸው ከራሳቸው ጋር ነው፤ ከገዳይ ሃሳባቸው፤ ከዘራፊ ሃሳባቸው ፤ህዝብ ከሚያፍን ሃሳባቸው ጋር ነው መታገል ያለባቸው ። የትግራይ ወጣት ምን በወጣውና ነው ከእነዚህ ጋር የሚታገለው። ተደራጅቶ በፖለቲካ ብልጽግናን ማሸነፍ ይችላል። በጥይት አይደል በፖለቲካ በሰላማዊ ምርጫ፤ በ <<ቡሌት>> ሳይሆን በ <<ባሎት>>፤ በጥይት ሳይሆን በምርጫ ኮሮጆ ይሁን መሸናነፍ ነው ያልነው።

በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች አርባ ምናምን ዓመት እንዋጋ እያሉ የትግራይን ወጣት እያስጨረሱ አንዳቸውም ሳይሞቱ ሀገረሰላም ገቡ - ሌሎችን አስጨርሰው። እነርሱ አይሞቱም። እንዋጋ ማለት <<እኔን ጠብቀኝ፤ እኔ አልሞትም፣ አንተ ሙትልኝ>> ማለታቸው ነው። እና የማን ሞኝ ነው ከዓመት ዓመት ለእነርሱ ነፍስ እየገበረ እነርሱን የሚያኖረው። ጀግኖች ቢሆኑ ኖሮ የመቀሌን ህዝብ ጥለው ከሚሄዱ እዛው እየተዋደቁ ይሞቱ ነበር። አንተ ተዋጋ እያሉ ይሸሻሉ፤አንተ ተዋጋ እያሉ ይሸሻሉ ... ይሄ በጣም አደገኛ ነገር ነው።



> ትግራይ የተከበረ ህዝብ ነው፤ ራሱን ማስተዳደር ይችላል። እንኳንም ከአፈና ነጻ ወጣ እንጂ። በራሱ ልጆች በአጭር ጊዜ ምርጫ አካሂደን ህዝቡ በፈለገው ሰው በራሱ ሰዎች ይተዳደራል..."

ሰዎቹ ትምህርት ወስደው ቶሎ ብለው እጃቸውን ለህግ ቢሰጡ መልካም ነው። በህግ ካልሆነ ያው በውጊያ ነው፤ ውጊያ ደግሞ ህይወት ይቀጥፋል። እኛ እየተከተልናቸው ነው፤ ብዙ እርቀት ሊሄዱ አይችሉም። እጅ መስጠት ጥሩ ነው። እነሱን በሚመለከት ሁሌ አይሞቱም። ከቤተመንግስት ሲወጡ ቤተመንግስት ምን ጉዳይ አለን፤ አዲስ አበባ ሆነን እናስተዳድረዋለን አሉ፤ ከአዲስ አበባ ሲወጡ ገደል ይግባ መቀሌ ሆነን እናስተዳድራለን አሉ፤ ከመቀሌ ሲወጡ ደግሞ ሀገረ ሰላም ነን ይላሉ። እንደዚህ አይሆንም። ህዝብ እያስጨረሱ ላለመሄድ ቆም ብሎ ማሰቡ ጠቃሚ ነው።

የእኛ ቀጣዩ ሥራ ትግራይን መገንባት ነው። የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ ችግር ያለበት ህዝብ ነው። የተከበረው ምክር ቤት ማወቅ ያለበት የትግራይ ህዝብ የሚኖረው በሬሽን ነው። ያም ሬሽን እየተቀነሰበት ነው ኑሮውን እየገፋ ያለው። አሁን ማድረግ ያለብን ህዝባችንን ከችግር ማውጣት ነው። ከችግሩ መውጣት እንዲችል መደገፍ አለብን፤ ማቋቋም አለብን፤ የተሰደደውን መመለስ አለብን።

ስደተኛን በሚመለከት 30ሺ ሰው ገደማ ተሰዷል የሚል መረጃ አለ። የተከበረው ምክር ቤት እንደሚያውቀው ይህ ለውጥ በሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ተፈናቅለው መመለስ ችሏል። 30 ሺ ለእኛ ቁርስ ናት። ልምድ አለን። በሶማሌ ልምድ አለን፤ በጌዲኦ ልምድ አለን። በሁሉም ቦታ ተፈናቅሎ አቋቁመናል፤ በሳምንት እናቋቁማለን። የተባበሩት መንግሥታትም፤ የሱዳን መንግሥትም ስደተኛ ነን የሚል ሃይልም በራችን ክፍት ነው። ዜጎቻችን ናቸው ወንጀል እስካልሰሩ ድረስ  ተባብረን እንመልሳቸዋለን።

ግን አንድ ችግር አለ፤ ሴቶችና ህጻናት በብዛት የሉም። ወጣት ብቻ ነው ስደተኛ የሆነው። ይህ ወጣት ማነው? የሚለው ጊዜ የሚመልሰው ይሆናል። ማይካድራ ላይ ሰው አርዶ ከሆነና ማስረጃና መረጃ ከተገኘበት በህግ ይጠየቃል። ንጹህ ዜጋ ከሆነ ግን ነገ ጠዋት እንመልሳለን። ያቋቋምነው ኮሚቴ አለ፤ ዝግጁ ነን፤ ዓለምም በዚህ ጉዳይ ማገዝ ከፈለገ በራችን ክፍት ነው። እኛ ዜጎቻችን ውጪ እንዲቀመጡ አንፈልግም።

የፖለቲካ ውይይት ከክልሉ ህጋዊ ፓርቲዎች ፤ከአረና፣ ከትግራይ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ፣ከብልጽግና እና ከሌሎች ህጋዊ ፓርቲዎች ጋር ይደረጋል። ከዚህ ውጪ አንድም ሰው ትግራይን እንዲያስተዳድር አንፈልግም፤ አናደርግም። ትግራይ የተከበረ ህዝብ ነው፤ ራሱን ማስተዳደር ይችላል። እንኳንም ከአፈና ነጻ ወጣ እንጂ። በራሱ ልጆች በአጭር ጊዜ ምርጫ አካሂደን ህዝቡ በፈለገው ሰው በራሱ ሰዎች ይተዳደራል።

ጁንታው ጋር ያለው ጉዳይ የሚቀጥለው ኦፕሬሽን ይቀጥላል። እንደመንግስት ሆኖ እንደሀገር ሆኖ ያለው ጨዋታ አበቃ እንጂ እንደግለሰብ ጥፋተኞች ካሉ ቀጣይ ይሆናል። ግን ለጁንታውም ቢሆን ምክር መስጠት ጥሩ ነው። መጀመሪያ አንድና ሁለት ወንጀለኛ ላለመስጠት ተብሎ ይሄ ሁሉ ነገር ተፈጠረ ። አሁን እኛ ወታደር ሆኖ የከዳንን ወታደር ህግ አለው እርሱ ይዳኘዋል። ፖለቲካ ላይ የምንፈልጋቸው ሰላሳ አርባ ሰው አይበልጡም፤ ቁልፎቹ። ሰላሳ አርባ ሰው እጅ ላለመስጠት ብሎ ወጣት ማስፈጀት የለበትም፤ አይገደልም በህግ ይጠየቃል።

ለሰላሳ ሰው ተብሎ የሚፈርስ ክልል እንዳይኖር ሰፊ ሥራ መስራት አለብን። የወደፊት ሥራችን መገንባት፣ ማረጋጋት፣ ሰላምን ማምጣት ነው። ከዚህ ውጪ የሚቀጥለውን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ማድረግ ነው። የተከበረው ምክር ቤት ማወቅ ያለበት ነገር ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ፍቱን መድሃኒት ነው። ምርጫው ተአማኒ መሆን አለበት ፤ዴሞክራሲያዊ መሆን አለበት፤ ምርጫ ቦርድ በሚያስቀምጠው መርሐግብር መሰረት መፈጸም አለበት። ለዚህ የምንገዛና ዝግጁ መሆን አለብን።


ይህ ምክር ቤት ብዙ ድምጾች የሚሰሙበት መሆን አለበት። ዋስትናችን እሱ ነው። ይህ ለትግራይም ለኢትዮጵያም ይሰራል። ከውጭ አንጻር ጎረቤታችንን ማስቀደማችን

> "ይህ ምክር ቤት ብዙ ድምጾች የሚሰሙበት መሆን አለበት። ዋስትናችን እሱ ነው። ይህ ለትግራይም ለኢትዮጵያም ይሰራል። ከውጭ አንጻር ጎረቤታችንን ማስቀደማችን ጠቅሞናል። ወደፊትም ይቀጥላል። አጠናክረን መቀጠል አለብን። የኢትዮጵያ ህዝብም በትብብር ትግራይን መልሶ መገንባት አለበት..."

ጠቅሞናል። ወደፊትም ይቀጥላል። አጠናክረን መቀጠል አለብን። የኢትዮጵያ ህዝብም በትብብር ትግራይን መልሶ መገንባት አለበት። ጉዳቱን ካየን በኋላ በመንግሥት የሚሰራውን በመንግሥት እንሰራለን፤ ህዝባችን ተባብሮ ክልሉን መገንባት አለበት።

ጁንታውን በሚመለከት በግል ከከበደም ፤ከተሰማም ጥላቻ የለኝም። እናንተም እንዳይኖራችሁ። ጥላቻችን ከእሳቤው ነው፤ ከስራው ነው። አንደኛውን ጁንታ አባረን ሌላኛው ጁንታ እንዳንሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ይሄ ጁንታ ነው እያልን አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ብለን በዘር የምንጣላ ከሆንን እኛም ጁንታዎች ነን ማለት ነው። ስለዚህም የትግራይ ተወላጆች በትግራይም ይሁን ከትግራይ ውጪ ያሉ ከጁንታው ጋር ትስስር የሌላቸው ከሆኑ በኢትዮጵያዊነታቸው መውደድና ማክበር አለብን። ይህንን ካላደረግን ቦታው ይለዋወጣል እንጂ የሚመጣ ለውጥ የለም። ይህ እንዳይሆን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

በመከላከያ፣ በፖሊስና በሲቪል ተቋማት የሚሰሩ የትግራይ ተወላጆችን በተመለከተ አስፈላጊው ጥበቃ ማድረግ ይገባል። ባለፉት ጊዜያት የተወሰኑት ከስራ እንዲወጡ ተደርጓል። እነሱ መገንዘብ ማሰብ ያለባቸው ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛ እዛ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ተካሂዷል። ስለዚህ ያን የሚያክል ሠራዊት እዚህ በብስጭት ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። እነርሱን መጠበቅ ያስፈልጋል። ሁለተኛ ምንም ጥርጥር የለውም ብዙ የተገዛ ነበር እዚህ። ቤቱ ፈንጂ ያለ፤ ቦንብ ያለ ለማፈንዳት የተዘጋጀ። ከማይካድራ መማር አለብን። በሁለቱ ምክንያት የተሰራ ስራ አለ። እየተጣራ ግን ሁሉም ቦታውን መያዝ ይገባዋል።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የህግ ማስከበር ዘመቻው በድል ከተጠናቀቀ በኋላ በመቀሌ አየር ማረፊያ ጦርነቱን ከመሩት መኮንኖች ጋር፤

ሌላው ጦርነትን ማሸነፍ እንደመሸነፍ የራሱ ድካም አለበት። ጦርነቱን በከፍተኛ ጀግንነት በብቃት አሸንፈናል። ነገር ግን ይሄ ነገር ወደ ትዕቢትና እብሪት ከወሰደን ጥፋት ነው። የድል አድራጊ ዘፈን ማቆም አለብን። በእኔ እምነት ያሸነፈው እውነት ነው። ያሸነፈው የኢትዮጵያ እናቶች እንባና ጸሎት ነው። ሌላው ሰው ትሁት መሆን አለበት። ትሁት መሆን ማለት ላለመጥላት ስለአሸናፊነት ላለመዘመር፤ ወደ ዋናው ውጊያ መግባት አለብን። ዋናው ውጊያ ገና አልተነካም። ከድህነት ያልወጡ ሀገራት ቢያንስ በአሥር ዓመት አንድ ጊዜ ውጊያ ይገጥማሉ። ቢያንስ ከውጊያ ካልወጣን ወደ ብልጽግና ካልሄድን አትጠራጠሩ ከጁንታ ኤክስ ይቅርና ከጁንታ ዋይ እንዋጋለን። እንደዚህ ከሚሆን በፍጥነት ከውጊያ ታሪክ እንድንወጣ በፍጥነት ወደ ብልጽግና መሄድ አለብን። ወደ ልማት መሄድ አለብን። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ያሳየውን ቁርጠኝነት ፤አሁን ያሳየውን ተባባሪነት ልማት ላይ መድገም አለበት። ከልመና ያልወጣ ሀገር የተሟላ ነጻነት የለውም። አዛዡ አለቃው ብዙ ነው።

ከልመና ለመውጣት ጨክነን ልንሰራ እንችላለን። መቀየር እንችላለን ይሄን ሀገር። ብቃቱ አለ። በእርሻ በኢንዱስትሪ በከተሞች የጀመርናቸውን ስራዎች አጠናክረን መቀጠል አለብን። እድገት በአንድ ሌሊት አይመጣም። እድገት የሚያመጡት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ሌላው አጋዥ ነው። በልመና ዕድገት አይመጣም። በዜጎች ጥረትና ሥራ ብቻ ነው ዕድገት የሚመጣው። ወደ ብልጽግና እንድንሄድ ተጨማሪ ውጊያ እንዳይኖር፣ ግጭት እንዳይኖር በብሄር መከፋፈል እንዳይኖር፣ ድል መናጠቅ እንዳይኖር፣ ከዚህ ዜና ወጥተን በተባበረ ክንድ ወደ ልማታችን ፤ወደ ሰላማችን ፤ወደ ህጋዊ ምርጫችን እንድንሄድ ከሁላችንም ብዙ ይጠበቃል። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን በማድረግ እንዲተባበር አደራ እላለሁ። ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ በልጆቿ ደም ህልውናዋን ጠብቃ ትቀጥላለች። አመሠግናለሁ !

> ጦርነቱን በከፍተኛ ጀግንነት በብቃት አሸንፈናል። ነገር ግን ይሄ ነገር ወደ ትዕቢትና እብሪት ከወሰደን ጥፋት ነው። የድል አድራጊ ዘፈን ማቆም አለብን። በእኔ እምነት ያሸነፈው እውነት ነው። ያሸነፈው የኢትዮጵያ እናቶች እንባና ጸሎት ነው..."





# እንጽ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ከ2010 ለውጥ ዋዜማ ጀምሮ ያለፈችበት ጠመዝማዛ መንገድ በህዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም የምክር ቤት ውሎ በወፍ በረር ተዘርዝሯል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሰጡት ማብራሪያ የህወሓት ጁንታ በለውጡ ዋዜማ ስልጣንን በበላይነት ለመቆጣጠር ሲያደርግ የነበረውን ጥረት፤ የመረጃና ጸጥታ ተቋማትን ሙያዊ አበርክቶ በማሳነስ የጥቅሙ ማስጠበቂያ ያደረገበትን መንገድ፤ ይህም ያስከተለውን መዘዝ ጠቅሰዋል።

የሀገሪቱ ፖለቲካዊ ቀውስ የደህንነት ስጋትን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያደረገ በመምጣቱ ለውጥ እውን ሆኗል። ይህ ያልተዋጠለት ጁንታው ሀገራዊ ትርምስ በመፍጠር ለውጡን ለመቀልበስ ያደረጋቸው መፍጨርጨሮች በስተመጨረሻም በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት፤ የለውጥ ሃይሉ ያከናወናቸው የሪፎርም ስራዎች እንዲሁም የኢትዮጵያውያን ጀግንነትና አንድነት ሀገሪቱን እንዴት እንደታደጋት በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተብራርቷል። የሀገርን ህልውና ቀጣይ ለማድረግ እስከ ሞት ዋጋ በሚያስከፍለው ክቡር የወታደርነት ሙያ መሰማራት እንደሚገባ፣ ህዝቡም ለሙያው ባለቤቶች የሚኖረውን ክብርና እንክብካቤ ማጎልበት እንደሚጠበቅበት አስገንዝበዋል።

በምክር ቤቱ ለአመታት ታምቀው የቆዩ ስሜቶች ተንፍሰዋል። ኢትዮጵያም መበደሏን ለታሪክ ምስክርነት ትታ ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላ መሸጋገሯን አውጃለች። ምንም እንኳን አዳዲስ ፈተናዎች ማጋጠማቸው ባይቀርም፤ ዜጎቿ በተባበረ ክንዳቸው በሰላም፣ በፍቅርና በእኩልነት የሚኖሩባትን ቤታቸውን በአዲስ መንፈስ መገንባታቸውን ይቀጥላሉ።

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትም እንደ አንድ ሀገራዊ አደራ እንደተጣለበት ተቋም ተለዋዋጭ ከሆነው ዓለማዊ፣ አካባቢያዊና ብሔራዊ ደህንነትና ጥቅም አንጻር መረጃዎችን ሰብስቦና ተንትኖ ለመንግሥት ማቅረብ ሲገባው፤ በዜጎች ብሎም በመንግሥት ከፍተኛ አመራሮችም ጭምር አፈና ሲፈፅም እንደነበር በክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ ተብራርቷል። ኢትዮጵያን በሚወክሉ ዜጎች ከመዋቀር ይልቅ የቤተሰብ ማህበር ይዘት ተላብሶ መቆየቱም የተጠቀሰ ህጸጽ ነው።

አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ከለውጡ ማግስት በጀመረው ሪፎርም ያለፈውን ስህተት በማረም በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ብቻ በመወጣት አዲስ ገጽታ የሚያላብሰውን አቅጣጫ ተልሟል። በህግ የሚመራ፤ ከፓርቲ ውግንናና ተፅእኖ ነፃ የሆነ እንዲሁም ስርዓት በተለዋወጠ ቁጥር የማይዋዥቅ ዘላቂነት ያለው ተቋም በመገንባት የህዝቡን ሰላምና የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት ለመጠበቅም የሚያስችለውን ጉዞ አጠናክሮ ይቀጥላል።

# በምስል

ከመጋቢት 2010 - ታህሳስ 2013 ዓ.ም



አደራ





ዲፕሎማሲ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የዩናይትድ ስቴትስ ስቴት ሴክሬታሪ ማይክ ፖምፔዮ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የጀርመን መራሂተ መንግሥት አንጌላ ሜርክል




ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የኢጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጁሴፔ ኮንቴ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሼክ አብዱላህ ቢን ዛይድ አል ናህያን



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንጃሚን ኔታንያሁ




ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚደንት ሲሪል ራማፎሳ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና
የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ














## በምስል









NOBEL


መደመር









ክቡር አቶ ተመስገን ጥሩነህ
የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል

# እንዳያጸገም !

ኢትዮጵያ ለዘመናት የዘለቀ የመንግስት አወቃቀር፣የዳበረ ፖለቲካዊ ስርዓት፣ታሪክና ባህል ያላት ሀገር ስለመሆኗ ድርሳናት፣ የሚጨበጡና የማይጨበጡ ቅርሶቿ ይመሰክራሉ። በየጊዜው የሚያጋጥማትን ፈተናዎች እየተሻገረች ዛሬ ላይ የደረሰችውም በዘመን ሂደት ያካበተቻቸው መልካም እሴቶች ህዝቦቿን አስተሳስሮ እንዳይነጣጠሉ አድርጎ ስላሰናሰለ እና ስለ ሀገር ህልውና መስዋዕትነት መክፈል መታደል መሆኑን በደም በሚያሰርጹ ተከታታይ ትውልዶች ስለተገነባች ነው።

ኢትዮጵያ ዛሬም በፈተና ተከባለች፤ ይሁንና ኢትዮጵያ ዛሬም የተደቀኑባትን ፈተናዎች የሚያሻግሩ ጀግኖችን አፍርታለች !

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ህዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመገኘት ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ እንደ ሀገር ያጋጠሙትን ፈተናዎች እንዲሁም የታለፈባቸውን በጥበብ የተሞሉ አካሄዶች አብራርተዋል። ችግሮች በርትተው ሀገር ፈረሰች በተባለበት ዋዜማ ሩቅ የሚያደርስ ራዕይ ያነገቡ ትውልዶች መጸነሳቸውን፣ ዛሬም ሀገርን የሚያሻግሩ ጀግኖች መኖራቸውን አረጋግጠዋል።

በተለይ የህወሓት ጁንታ በሀገሪቱ የፈጠረው ፖለቲካዊ ምስቅልቅል የብሔራዊ ደህንነት ስጋት በማስከተል፤ ዜጎችም <<ነገ ምን ይመጣ ይሆን?>> በሚል ኢተገማች ሁኔታ በስጋት እንዲኖሩ አስገድዶ ነበር። <<በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ>> ከፓርቲ ውግንና ነፃ ሆነውና በገለልተኝት መርህ ለሀገር ብሔራዊ ደህንነትና ለህዝብ ጥቅም እንዲቆሙ የተመሰረቱት ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንዲሁም ሌሎችም የጸጥታና የመረጃ ተቋማት ሙያዊ ተልዕኳቸውን ብቻ አለመወጣታቸውና ኢትዮጵያን በሚወክል ተዋጽዖ አለመደራጀታቸው ችግሩን ውስብስብ ማድረጉ ይታወሳል።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ የመረጃና የደህንነት ተቋሙ የአመታት ህጸጾች ተነቅሰው ወጥተዋል። ይሁንና ጉድለቶችን ለማረም የተከናወኑ የሪፎርም ስራዎች ጁንታው የከፈተውን ጥቃት ለመመከት አስችሏል፤ የሀገርንም ህልውና አስቀጥሏል።

ተቋማችን ክፍተቶችን በመዝጋት የጀመረውን ለውጥ አጠናክሮ ይቀጥላል። ከፓርቲ ውግንና ነጻ በመሆን ሙያዊ ተልዕኮውን ብቻ ለመወጣት የጀመረው ሪፎርም የፖለቲካ ስርዓቱ ፈተና ቢያጋጥመው እንኳን ሀገርን የሚያሻግሩ ተቋማት እውን እንዲሆኑ ለተያዘው ውጥን ጉልህ ሚና ስለሚያበረክት፤ ያለፈውን ስህተት ባለመድገም በጀመረው አዲስ መንገድ ወደ ስኬት ይጓዛል !